

# "እመኑን!"

## የለውጥ ሃይሉ ጥያቄ ወይስ አዲሱ የፖለቲካ መንገድ ?


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን


በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 51 ሚያዚያ 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99




እስክንድር የጠ/ሚ/ር ዐቢይን ግብዣ ሰርዞ፣ ከታከለ ኡማ ጋር ለምን ተገናኙ?



## እንዴት ያቅተናል?

ደበበ እሸቱ (አርቲስት)




## በመንገጫገጭ ውስጥም ደማቅ ለውጥ አለ!

ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና

## የረቂቅ አዋጁ ነገር

በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር



# "ዐቢይን ተጠያቂ አላደርገውም"

## "በዴሞክራሲ ራሱን አስተዳድሮ የማያውቅ ሕዝብ ነው"

ፕ/ር መሣይ ከበደ (ከአሜሪካ)



## "የህዳሴውን ግድብ ጎጃም ላይ በአነስተኛ ወጪ መስራት ይቻል ነበር"

ኢ/ር አበበ አያሌው

ግዮን

# “ዐቢይን ተጠያቂ አላደርገውም”

## “በዴሞክራሲ ራሱን አስተዳድሮ የማያውቅ ህዝብ ነው”

*ፕ/ር መሣይ ከበደ(ከአሜሪካ)*



14


7 ሰውየው ሲስተካከል ዓለሟ ትስተካከላለች
ብሩክ አስቻለው

8 ከ”ጥላቻ ንግግር” ረቂቅ ሕጉ ጀርባ ምን አለ?

11 አንደበትና ቅምሻ

12 እስክንድር የጠ/ሚ/ር ዐቢይን ግብዣ ሰርዞ፣ ከታከለ ኡማ ጋር ለምን ተገናኙ?

13 የረቂቅ አዋጁ ነገር
በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

17 በመንገጫገጭ ውስጥም ደማቅ ለውጥ አለ!
ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና

19 እንዴት ያቅተናል?
ደበበ እሸቱ (አርቲስት)

20 ስርአተ - አልበኞችን ማን ያስታግሳቸዉ !
ኢዮብ ሳለሞት

21 ኑ መንግስትን እና የሕግ የበላይነትን እንፈልግ!
ገበያው ይታየው





ቁጥር 50 ዕትም

ግዮን

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ሚያዚያ 13
ይጠብቁን!

# “እመኑን!”

የለውጥ ሃይሉ ጥያቄ ወይስ አዲሱ የፖለቲካ መንገድ ?

**መላክ ቢ.** 4

## ከከሚሴ፣ አጣዬና ማጀቴ፣ ዕልቂት ጀርባ ተጠያቂው ማነው? 3


23 ጠንቋይና ሐይማኖተኛ ፖለቲከኛ ሊሆኑ አይችሉም
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

25 ዳግም ጥሪ ከጌዴኦ
<<ፓርክ ውስጥ እንዳለ እንስሳ ነው የጎበኙን >>

26 ከፖለቲካው በፊት ሠላም ይቅደም
ከሽዋፈራሁ ኩራቱ ዶ/ር




“የህዳሴውን ግድብ ጎጃም ላይ በአነስተኛ ወጪ መስራት ይቻል ነበር”

*ኢ/ር አበበ አያሌው* 9

# የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የፅዳት ዘመቻ ጥሪ

ቆሻሻን ከአካባቢ መጥረግ እንደሚገባ ሁሉ ከአዕምሮም መጥፎና ክፉ ሀሳብን በመጥረግ በመልካም አስተሳሰብ መተካት እንደሚያስፈልግ ያስተምራል የተባለለት ታላቅ የአከባቢ የፅዳት ዘመቻ በመላው የአገሪቱ ክፍሎች ነገ እሁድ ሚያዚያ 6 ቀን 2011 ዓ.ም እንደሚካሄድ ተነገረ፡፡

መልካም አስተሳሳብን ለመስበክ ያግዛል የተባለውን የፅዳት ዘመቻ ያወጁት የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠ/ሚ ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ በዚህ የፅዳት ዘመቻ ላይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የመንግስት ሠራተኞችና መላው የአገሪቱ ህዝብ በመሳተፍ መጥፎ ስሜትን በመልካም ስሜት ለመተካትና መልካም ለማሰብ እንዲነሳሱ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የፅዳት ዘመቻው እሁድ ከንጋት 12፡30 እስከ ጠዋት ሁለት ሠዓት ባለው ጊዜ እንደሚከናወን የተነገረ ሲሆን፤ ሁሉም ተሽከርካሪዎች ከእንቅስቃሴ ተገድበው የግብሩ ተባባሪ እንዲሆኑና በተለይም ቋንቋን መሠረት ያደረጉ ልዩነቶች በህብር ውስጥ ያሉ ጌጦች እንጂ መለያያ ነጥቦች መሆን እንደሌለባቸው በተግባር ማሳየት ይኖርብናል ተብሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የሚታዩ ችግሮችን ለመሻገር እርስ በርስ ተጋግዞ ማለፍ ይገባናል የሚል መልዕክት በጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ተላልፏል፡፡

# የህፃናት ሬፈራል ሆስፒታል ሊገነባ ነው

ከ300 በላይ ልዩ የህፃናት መኝታ ክፍሎች ይኖሩታል የተባለ "አዲስ የህፃናት ሪፈራል ሆስፒታል" በ55 ሚሊዮን ዩሮ ወጪ በአዲስ አበባ ማዕከል ሊገነባ መሆኑ ተገለፀ፡፡ ለግንባታው ከሚያስፈልገው ወጪ ውስጥም 27.44 ሚሊዮን ዩሮ የኔዘርላንድስ መንግስት በሰጠው ዕርዳታ የሚሸፈን ነው ተብሏል፡፡

በሚቀጥለው አመት ግንባታው የሚጀምረው የህፃናት ሪፈራል ሆስፒታል ተጠናቆ ስራውን ሲጀምር በኢትዮጵያ የሚሰጠውን የህክምና ጥራትና ቀልጣፋ አገልግሎት ችግር ያሻሽላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የእርዳታ ስምምነቱ በተፈረመበት ወቅት እንደተገለፀው የሆስፒታሉ ግንባታ ከመንግስት በተጨማሪ የግል ኩባንያዎች በገንዘብና በቴክኒክ ድጋፍ ይሳተፉበታል፡፡

ኔዘርላንድስ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር የተለያዩ ድጋፎችን እንደምታደርግና በተለይ በጤናው ዘርፍ ትኩረት ሰጥታ እንደምንትንቀሳቀስ አምባሳደር ቫን ሉስድሬክት ገልፀዋል፡፡

ስምምነቱን በኢትዮጵያ በኩል የፈረሙት የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ አድማሱ ሲሆኑ ለግንባታው የኢትዮጵያ መንግስት 20 ሚሊዮን ዩሮ እንደመደበ ተናግረዋል፡፡

# የሶማሌ ክልል በለውጡ ጎዳና



በሶማሌ ክልል ዘላቂ ሠላምን በማስፈን ህዝብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ሲሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፋ መሀመድ ተናግረዋል፡፡

በክልሉ ባለፉት ወራት በርካታ ለውጦች እንዲመጡ የመንግስት መዋቅሮች ማደራጀት፣ ሠላምና ፀጥታን ማስከበር፣ የህዝቡን ደህንነት ማስጠበቅ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንደተሰራ ያወሱት አቶ ሙስጠፋ መሀመድ በዚህ ሂደት ከአጎራባች ክልሎች ጋር ይስተዋሉ የነበሩ ችግሮችን ማቃለል ተችሏል ብለዋል፡፡

የክልሉ ህዝብ ለውጡን ተከትሎ ያለገደብ በነፃነት የመንቀሳቀስ መብቱን በመጠቀም ማህበራዊ ግንኙነቱን ከክልሉ አልፎ ጎረቤት አገራት ድረስ ማሳደጉንና በተወሰኑ የክልሉ አመራሮች በበላይነት ተይዞ በነበረው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ እየሆነ መምጣቱን አስረድተዋል፡፡

የሠብዓዊ መብት ጥሰት እና ሙስና ፈፅመው ወደ ውጭ የወጡ ሠዎችን ወደ ሕግ ማቅረብ ባይቻልም፤ በግጭት ምክንያት ከአካባቢው ተፈናቅለው የነበሩ ሰዎችን ወደ ቀድሞ ቀዬአቸው መመለስ ተችሏል ያሉት ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ይህንን ለማስፈፀም አቅም ያላቸውን አመራሮች ወደፊት እንዲመጡ ማድረጋቸውን ገልፀዋል፡፡


# ሰለ አሠብ አዲስ መፅሐፍ ታተመ



"አሰብ ቀይ ባህርና ወደባችን በዚያን ግዜ" በሚል ርዕስ በደራሲ ዮሐንስ ተፈራ የተፃፈው መፅሀፍ መጋቢት 28 ቀን 2011 ዓ.ም በኢቫንጀሊካል ድህረ ምረቃ ኮሌጅ አድራሻ በድምቀት ተመረቀ፡፡

በቀደሙት ዘመናት የነበረውን የአሠብ ቀይ ባህር ወደብን አጠቃላይ ህይወት የሚተርከው ይህ መፅሐፍ የቀድሞ የባህር ትራንስፖርት ባለስልጣናት፣ የቀድሞ የአሠብ ከተማ ነዋሪዎችና በወደቡ በተለያየ ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ሠራተኞች በተገኙበት ነው የተመረቀው፡፡ መፅሀፉ 380 ገፆች ሲኖሩት ዋጋው 150.00 የኢትዮጵያ ብር ነው፡፡

# "ሰውየው" መፅሐፍ ለንባብ በቃ




በዶ/ር ዐቢይ አህመድ ህይወት፣ ፍልስፍናና ሥኬት ላይ የሚያጠነጥነው ሰውየው የተሰኘ መፅሀፍ ለንባብ በቅቷል፡፡ በአራት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ገፆች የተጠረዘው ይህ መፅሐፍ የዶ/ር ዐቢይን የልጅነት፣ የወጣትነት እና የጠ/ሚኒስትርነት ደጃፍ የሚዳስስ ሲሆን፤ በአዳዲስና ያልታዩ ፎቶግራፎች፣ በአብሮ አደግና በወዳጅ ዘመድ እንዲሁም አብረዋቸው በሰሩ ሰዎች የምስክርነት ታሪኮች የተሞላ ዶሴ ነው፡፡

ፀሀፊው መሐመድ ሐሰን በፋና ሬዲዮና በሌሎች የህትመት ሚዲያዎች ላይ የሰራ ከመሆኑ ባሻገር፤ ከጠ/ሚሩ ጋር ለአምስት ዓመታት በቅርበት የመስራት አጋጣሚው እንደበረው ይገልፃል፡፡ በሀያ ምዕራፎችና ከመቶ ሀምሳ በላይ ርዕሶች የተከፋለውን ይህን መፅሀፍ እንድናነብ ተጋብዘናል፡፡

# ከከሚሴ፣ አጣዬና ማጀቴ፣ ዕልቂት ጀርባ ተጠያቂው ማነው?

ባሳለፍነው ሳምንት መገባደጃ በከሚሴ፣ በማጀቴ፣ በአጣዬና ካራ ቆሬ ከተሞች የተፈጠረው የንፁሃን ሕይወት የተቀጠፈበት አሳዛኝ ክስተት ነበር። የእነዚህ ከተማ ሕዝቦች ለዘመናት ሰላማቸውን ጠብቀው፣ በስራና በእምነታቸው ተግተው፣ ማንነትን በተመረኮዘ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያዊነትን ባስቀደመ መልኩ ተጋብተውና ተዋልደው፣ ኑሮአቸውን ሲገፉ ቆይተዋል።

በርግጥ በእነዚህ ቦታዎች በተለይ በከሚሴ አካባቢ ከዓመታት በፊት አንዳንድ ግጭቶች ቢኖሩም እንዲህ ሕዝብን ባሳዘነና ብዙዎችን አንገት ባስደፋ መልኩ፣ የሰው ልጅ ሳይተላለቅባቸው የሚቆሙ፣ በሀገር ሽማግሌ ዕርቅ የሚከስሙ፣ በይቅርታና በምህረት የሚፈቱ ነበሩ። ሰሞነኛው የታጣቂዎቹ ጦር እንቅስቃሴ ግን ለእነዚህ አከባቢዎች "መአትን" ይዞባቸው መጥቷል ማለት ይቻላል። በተረጋጋ ሕይወትና በመልካም ተስፋ ውስጥ የነበሩት የከሚሴና የአጣዬ ነዋሪዎች ቅዳሜ ዕለት ማለዳ የገጠማቸው ዱብ ዕዳ የሕይወታቸው መጥፎ ጠባሳ ሆኖ ቀርቷል።

በተደራጀና በተጠና መልኩ ወደ ከተሞች የዘለቁት የታጠቁ ኃይሎች ሙሉ ለሙሉ ኦሮምኛ ተናጋሪዎችና የኦነግ ጦር መሆናቸውን ከማሳወቅ ባሻገር፣ የድርጅቱን አርማ በአንገትና በእጃቸው ላይ ያሰሩ በርካታ ታጣቂዎችን እንደተመለከቱ ለዝግጅት ክፍላችን የገለፁልን የአጣዬና የከሚሴ ነዋሪዎች፤ በዕለቱ የነበረው ሁኔታ እጅግ በጣም አስደንጋጭ እንደነበር ጠቁመውናል፡ ፡ "ያገኙት ሰው ላይ ቀጥታ ጥይት በመተኮ ቤት ለቤት እየገቡ ዘረፋ ፈፅመውብናል" ያለን የአጣዬ ነዋሪ "እነዚህ የኦነግ ጦር አባላት ፈፅሞ ከሰው የተፈጠሩ አይመስሉም፡ ፡ ጭካኔያቸው በእጅጉ የከፋ ነው ማለት ይቻላል። ለሁለት ቀናት ባልተቋረጠ ሁኔታ በየሰው ቤት እየገቡ ግልፅ የሆነ ግድያና ዘረፋ ይፈፅሙ ነበር፤ ወረራውና ጥቃቱ ድንገተኛ ስለነበር፣ ራሳችንን ለመከላከል ቀርቶ ሕይወታችንን እንኳን ለማትረፍ በጣም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነበርን" በማለት አስከፊውን ቀን ይገልፀዋል።

በከሚሴና በአጣዬ በርካታ ሰዎች በኦነግ ጦር ታጣቂዎች እንደተገደሉ እየተገለፀ ባለበት ወቅት ከተለያዩ የመንግስት አካላት የሚሰጡት መግለጫዎች የተለያየ ይዘት ቢኖራቸውም፤ ዞሮ ዞሮ ጥቃቱ በተደራጀ ኃይልና ቡድን የተፈፀመ መሆኑን አረጋግጠዋል። በተለያዩ ከተሞች ውስጥ በአኩል ሰዓትና ቀን የሽብር ጥቃት ለመፈፀም፣ እንዲህ ዓይነቱን ዘግናኝ ዕርምጃ ለመውሰድ አቅምም ፍላጎትም ያለው ጦር ከኦነግ ሠራዊት ውጭ በዚህች ሀገር ላይ ፈፅሞ እንደሌለ፣ ተጨባጭ እውነታዎችን በማንሳት አስተያየታቸውን የሚሰጡ በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች እንዳሉ ሁሉ፤ ጥቃቱን በአካል የተመለከቱና ሠራዊቱ ከተማዋን







ሲያሸብር በቦታው የነበሩ የአጣዬና የከሚሴ ነዋሪዎችም፣ ድርጊቱን የኦነግ ሠራዊት እንደፈፀመው ያምናሉ።

"ታጣቂዎቹ ሲበዛ አረመኔና ጨካኞች ናቸው፣ ለዘመናት ከሰው ልጅ ርቀው ጫካ የቆዩ መሆናቸውን ፀጉራቸውና ፊታቸው፣ ከዛም ባሻገር ዘግናኝ ድርጊታቸው ይመሰክራል። አንዳንዶቹ የሚሊሺያ፣ ቀሪዎቹ የመከላከያ ልብስ፣ ሌሎቹ ደግሞ ምንነቱ በውል ያልለየ የወታደር ዩኒፎርም ለብሰዋል። በየቤቱ እየገቡ ሴቶችን ሲያስቃዩ ነበር፣ በጥይት የተገደሉ እንዳሉ ሁሉ አንገታቸው የታረደ ሴቶችና ሕፃናትም ነበሩ። በአጠቃላይ እነዚህ ታጣቂዎች ይህን ለማድረጋቸው ምክንያት አልነበራቸውም። እኛ ሕይወትን የምንመራ፣ ሰላምን የምንናፍቅ፣ ንፁህ ዜጎች ስለሆንን" በማለት ተጠቂዎቹ ሀዘናቸውን በምሬት ይገልፃሉ።

በገምዛ ማጀቴ እሁድ መጋቢት 29 ቀን 2011 ዓ.ም ማለዳ የሆነው ይኸው ነው። በእርሻ የሚተዳደሩት የማጀቴ ህብረተሰብ አባላት ቅዳሜ ማምሻውን በከተማዋ አንዳንድ ቦታዎች ያልተለመደ እንቅስቃሴን ቢያስተውሉም፣ በማግስቱ የሆነውን "የከፋ" ዓይነት ዕልቂት ይፈጠራል ብለው ግን ፈፅሞ አልገመቱም። ለዛም ይመስላል "ሰላም አሳድረኝ" ብለው ከመኝታቸው ጋደም ያሉት፡ ፡ የጥፋት ቡድኑ ግን ሌሊቱን በሚጠቀምበት የመከለካያ ኦራል መኪና ተጭኖ፣ ወደ ከተማዋ በመግባት ወሳኝ የሆነውንና ቁልቁለቱን ቦታ ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር እስኪነጋ ድረስ አድፍጦ ይጠብቅ ጀመር።

ማለዳ የተነሱ የማጀቴ ነዋሪዎች ዕለቱ ሰንበት በመሆኑ ገሚሱ ቤ/ክርስቲያን ለመሳም፣ ሌላውም ወዳጅ ዘመዱን ለመጠየቅ ከየቤቱ ብቅ ከማለቱ ርህራሄ የለሾቹ ታጣቂዎቹ የተኩስ ውርጅብኝ አስከተሉባቸው። ከማለዳው አንድ ሰዓት የተጀመረው የታጣቂዎቹ ጥቃት እስከ ቀን አስራ አንድ ሰዓት እንደዘለቀ ለዝግጅት ክፍላችን የገለፁት በስልክ ያነጋገርናቸው የገምዛ ማጀቴ ተወላጆች "የኦነግ ታጣቂዎቹ ሌሊት መጥተው ወሳኙን ቦታ ስለያዙትና ያለንበት ቦታ አቀበት ስለሆነ፣ እነርሱ በርቀት ሆነው የፈለጉትን ጥቃት መፈፀም ችለዋል፡ ፡ መጀመሪያ ሁኔታው አስደንጋጭና ድንገተኛ ስለሆነ ሁሉም ራሱን ለማዳን ሲሯሯጥ ነበር፡ ፡ በኋላ ግን እኛም ራሳችንን ለመከላከል ዕርምጃ ለመውሰድ ተገደናል" ብለዋል።

በዕለቱ በገምዛ ማጀቴ በታጣቂ ሰራዊቱ አስራ ሰባት ሰዎች የተገደሉ ሲሆን፣ በአጎራባች ትናንሽ ከተሞች አጣዬ፣ ቆሪሜዳ፣ ጃራ አካባቢዎች ሶስትና አራት ሰዎች ሕይወታቸውን እንዳጡ የጠቆሙን፣ መረጃውን ለዝግጅት ክፍላችን ያደረሱ የማጀቴ ነዋሪዎች "ታጣቂ ቡድኑ ሙሉ ለሙሉ የሚንቀሳቀሰው በኦራል መኪና ነው። ሰዎቹ ጫካ የኖሩ፣ ብዙ ዓመት በትግል ውስጥ የቆዩ ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ ሙሉ ለሙሉ የሚናገሩት በኦሮምኛ ነው። በእርግጥ እንደእነሱ ብዙ ባይሆኑም አልፎ አልፎ የተቀላቀሏቸውና በጫካ ትግል ውስጥ ያለፉ የማይመስሉ ጥቂት የኦሮሞ ተወላጆችንም ተመልክተናል። እነዚህ ሰዎች አለባበሳቸውና ሁኔታቸው የአካባቢው ሚሊሺያ ነው የሚመስሉት። በጣም ግራ የሚያጋባ ነገር ነው የተመለከትነው። በእጅጉ አዝነናል፤ ይህን ያህል ጦር ተደራጅቶ በመላ ሀገሪቱ እንደልብ ሲንቀሳቀስ፣ እስከ ዛሬ ዝም የተባለበት ምክንያት ፈፅሞ ሊገባን አልቻለም" ሲሉም ቅሬታቸውን ገልፀዋል።

በማጀቴ እስከ 12 ሰዓት ድረስ የዘለቀው ውጊያ የቀመው ፣ የሰሜን ጎንደር ዞን ህዝቡን የሚያግዝ የልዩ ኃይል አባላት ወደ ቦታው መላኩ በመስማቱና ጦሩም በመድረሱ፣ ታጣቂው ኃይል ፈርቶ ቦታውን በመልቀቁ እንደሆነ የሚናገሩት የዜና ምንጮች፤ ቀኑን ሙሉ በነበረው ውጊያ የቆሰሉ ታጣቂዎችን ካሉበት አቀበት ስር "አምቡላንስ" በተደጋጋሚ እየመጣ ይወስዳቸው ስለነበር፣ የደረሰውን ትክክለኛ ጉዳት በቁጥር ለማስቀመጥ አዳጋች እንደሆነ ገልፀዋል። በተጠቃሱት ቦታዎች የደረሰውን ጥቃትና አጥፊውን ኃይል በተመለከተ የአማራ ክልል መንግስትና የፀጥታ ክፍሉ "የተደራጀ የጦር ቡድን" እንደፈፀመው በመግለፅ ጉዳዩን ለጊዜው ድፍንፍን ቢያደርጉትም፣ በፌደራል መንግስቱ በኩልም ተመሳሳይ መግለጫ ቢወጣም፤ በርካቶች ግን በቅርቡ በተጠቀሱት ቦታዎች ለደረሰው የንብረት መውደምና የሰው ሕይወት መጥፋት "አዲስ አበባ ያለው የድርጅቱ አመራር አያዘኝም፣ ከአመራሩ ተለይቻለሁ" የሚለው የኦነግ ሠራዊት እንደሆነ ቅድመ ግምታቸውን በርግጠኝነት አስቀምጠዋል።

# "እመኑን!"

## የለውጥ ሃይሉ ጥያቄ ወይስ አዲሱ የፖለቲካ መንገድ?

መላክ ቢ.

"በፖለቲካ ደጃፍ እምነት ድርሽ አትልም" የሚል አንድ ምንጩ የማይታወቅ አባባል አለ። በፖለቲካ ቋሚ ወዳጅ እና ቋሚ ጠላት የሚባል የለም ከሚለው የኖረ አባባል ጋር ተያይዞ የሚነሳው የእምነት (trust) ጉዳይ ብዙ ጊዜ ፖለቲከኞችም የማይታመኑ ሰዎች ናቸው ወደሚል ጠቅላይ አስተሳሰብ መርቷል።

እምነት ለፖለቲካ ምኑ ነው ብሎ የሚጠይቅ ሰው አስቀድሞ የቶም ቫንደርሜርን Political Trust and the "Crisis of Democracy" የሚል ጽሁፍ እንዲያነብ ይመከራል።

ቶም በዚህ ጽሁፉ የጠቀሰው አልሞንድ እና ቨርባ የተባሉ ምሁራን ስራ እንደሚያብራራው " ዴሞክራሲ ራሱ ያለእንከን ተግባራዊ እንዲሆን ህዝብ በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እና በገነባቸው ተቋማት ላይ ያለው እምነት ከፍ ያለ መሆን ይኖርበታል " A high level of public trust in democratic governance and its institutions is integral to the functioning of democracy itself .

ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ስርጸት ስኬት የህዝብ አመኔታ ወሳኝ ሆኖ የሚወጣባቸው ምክንያቶች ብዙ ናቸው። ቀዳሚው ጉዳይ ተዘረጋ የሚባለው ዴሞክራሲም ይሁን የዴሞክራሲ ተቋማት ሊያገለግሉ የተቋቋሙት ህዝቡን እንደመሆኑ በህዝብ ዘንድ አመኔታ ከተነፈጋቸው በዚያው መጠን የመኖራቸው ጉዳይ ትርጉም አልባ ስለሚሆን ነው። ሁለተኛው ጉዳይ ዴሞክራሲ ከስርወቃሉ ትርጉም ስንነሳ "የህዝብ አገዛዝ" ማለት በመሆኑ የህዝብ እምነት የሌለው ስርዓትም ይሁን ተቋም በዚያው መጠን የህዝብ አይደለም ወደሚል ድምዳሜ የሚመራ መሆኑ ነው።

በነዚህ ሁለት ምክንያቶች በአንድ ስርዓት ውስጥ በተለይም ዴሞክራሲን ለማምጣት እሰራለሁ በሚል ወይም ዴሞክራሲያዊ በሆነ ስርዓት ውስጥ የህዝብ እምነት ብቻ ሳይሆን ከፍ ያለ እምነት እጅግ አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን።

የህዝብ እምነት ማጣት በብዙ ሃገራት ከፍ ያለ የፖለቲካ ኪሳራ አስከትሏል። የአንድ አገዛዝ ወይም አስተዳደር መናጋት ምክንያት ሊሆን የሚችልበትም እድል ብዙ ነው። በዚህ ሳቢያም በሃገራት ውስጥ በተፈጠሩ የህዝብ እምነት ማጣት ምክንያቶች የየሃገራቱ መሪዎች ችግሩን ለመቅረፍ ጥያቄ ያቀረቡበት ጊዜ ጥቂት አይደለም።ለምሳሌም እያደገ በሄደ የህዝብ እምነት መሸርሸር ሳቢያ በ1974 የጃፓኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ታኪዮ ሚኪ፣ በ2002 የኔዘርላንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጃን ፒተር ባልከኔንዴ እና በ2010 የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሮን በሃገራቸው ፖለቲካ ውስጥ የህዝብ እምነትን መልሶ ስለማግኘት ወይም ዳግም ስለመገንባት ይፋ ጥያቄ እንዲያቀርቡ አነሳስቷቸዋል።

ለብዙ አስርተ አመታት ምሁራን የፖለቲካ እምነትን ጥያቄ ውስጥ እንዲከቱ የሚያነሳሳቸው ዋና ጉዳይ በፖለቲካው ውስጥ የህዝብ እምነት እያሽቆለቆለ በመሄዱ ሳቢያ ነበር። ምክንያቱም ለአንድ የዴሞክራሲ አገዛዝ የፖለቲካ እምነት ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ስለሚታሰብ ነው። በእምነት ላይ ያለ ማሽቆልቆል ወይም በኛው አማርኛ እምነት መጉደል የውክልና ዴሞክራሲን በጽኑ የሚገዳደር ጉዳይ ሆኖ ይቀርባል።

የፖለቲካ እምነት ለብዙዎች በዋናነት ውድቀት የሚመስል ነገር በመጣ ጊዜ እና የተረጋጋ ሁኔታ በሌለበት ወቅት ዜጎች ለፖለቲካ ተቋማት ወይም መሪዎች የሚሰጡት ድጋፍ ነው የሚል ትርጉም አለው።

### የፖለቲካ እምነት በኢትዮጵያ

የፖለቲካ እምነት እና የህዝብ እምነት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ቢመስሉም ሁለቱም የሚሰናሰሉበት አንድ ነጥብ የፖለቲካ ተቋማት በሚመሩት መንግስት ወይም የፖለቲካ ተቋማቱን በሚመሩት ግለሰቦች ላይ የሚያነጣጥሩ መሆናቸው ነው። በተለይ እንደኢትዮጵያ ላለች ሃገር በቀላል መንገድ የፖለቲካ እምነትን ማምጣት አይቻልም።

የዚህ ምክንያቱ ብዙ ሊሆን ይችላል። ሃገሪቱ ለብዙ ዘመናት ካለፈችበት ኢ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ስርዓት ፣ ወይም ሃገሪቱንና ህዝቡን አስጨነቀውና ደፍጥጠው በገዙ አምባገነን መንግስታት እና መሪዎች ፣ ወይም ዴሞክራሲያዊ ስም የዘው ነገር ግን የዴሞክራሲ መገለጫ የሆኑትን ተቋማት በማፈን እና ህዝቡን መተንፈኛ እና መላወሻ በማሳጣት የመሩ የፖለቲካ ተቋማት በመኖራቸው በነዚህና በሌሎችም ብዙ ምክንያቶች ህዝብ የፖለቲካ እምነትን እንዲላበስ መጠበቅ ከባድ ይሆናል።

በኢትዮጵያ ውስጥ እናውቅልሃለን በማለት የመጡ ብዙ መንግስታት ፣ ያንንም ደግፎ ያውቁልኛል ብሎ ስልጣን መንበር ላይ ያስቀመጣቸው ብዙ መሪዎች በመጨረሻ ህዝቡን በሌላ መንገድ ሲጎዱት ስለኖሩ ይህም አንድ ለመተማመን በር የዘጋ ምክንያት ሆኖ ኖሯል ።

በዚህ ሳቢያ ህዝብና መንግስት የማይግባቡ አካላት ሆነው ኖረዋል ። መንግስት የሚናገረው በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው ምናልባት አዋጅ ሲወጣ ወይም ዴሞክራሲን የሚያቅብ ተግባር ለመፈጸም መግለጫ ሲያወጣ ብቻ ነበር። በሌላ አባባል መንግስት እውነት የሚናገረው ህዝብን ለማፈን ሲዘጋጅ ብቻ በሚሰጣቸው ማስጠንቀቂያዎች አንጂ ህዝብ የሚያስፈልገውን ነገር ለመስራት በሚሰጣቸው ተስፋዎች ላይ አልነበረም እውነተኝነቱ።

ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ የሄደ ያለመተማመን እና መንግስትም በቃሉ ያለመገኘቱ ነገር (በቀላል አማርኛ "የመንግስት ዋሾነት") በብዙሃኑ ህዝብ ዘንድ ስለመንግስት ያለው ግምት የወረደ እንዲሆንና የማይታመን መንግስት እንደሚመራው በማሰብ ተስፋ ወደመቁረጥ ያደረሰው አካሄድ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል።

ይህ መንግስትንና ስርዓቱን ያለማመን ችግር የተፈጠረው መንግስት በግልጽም ይሁን በድብቅ የሚሰራቸው ተግባራት ከፋፋይ፣ ለአንድ ወገን ያጋደሉ፣ ህዝብን ጥቅም የሚጻረሩ እና በሁሉም መልክ ሃገርን በማሳደግ ወደዴሞክራሲ መንገድ ከመምራት ይልቅ የዴሞክራሲ ተቋማትን በማቀጨጭ ወደማይገባ መንገድ የሚመሩ ሆነው በመገኘታቸው ነው።

ያ አካሄድ ለዘመናት ከመቀጠሉ ጋር ተያይዞ ►

ህዝብ ያለማመኑ ስሜት ወደቅሬታ ቅሬታው ደግሞ ወደብሶት እና ብሶቱ በጊዜ ሂደት ወደተቃውሞ እንዲያመራ ምክንያት ሆኗል። ለበዙ ጊዜ ታምቆ የቆየው የህዝብ ብሶት ታፍኖ በመኖሩ ሳቢያ ኢህአዴግ ሊያብላላው እና ሊያተነፍሰው የሚችልበት መንገድ አልነበረም። ኢህአዴግ በጊዜ ሂደት ቁጥጥር እና ክትትሉን እያጠበቀ እና የዴሞክራሲ ጭላንጭል የሆኑ ተግባራትን እያቀጨጨ ወደጠቅላይነት ሲያመራ በዚያው ልክ ህዝቡም ከኢህአዴግ ጋር ያለው ግጭት እና አለመተማመን እየሰፋ መጥቷል። ይህ ውጥረት ከውጭ ኢህአዴግን በጽኑ ሲፈታተነው የህዝብ ጥያቄን መመለስ አለብን የሚለው የኢህአዴግ የውስጥ ንቅናቄ ሃይል ሆኖት ዛሬ የተፈጠረው ለውጥ እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል። ከዚያ በኂላስ ህዝብ በመንግስት እና በአስተዳደሩ ላይ ያጣውን እምነት ዳግም አደሰ ወይስ ባለበት ቀጠለ?


## ጽህረ ለውጥ እና የህዝብ የፖለቲካ እምነት

ኢህአዴግ እንደፓርቲ የለውጡን ሂደት ከራሱ ሲጀምር አስቀድሞ ያካሄደው ጥልቅ ተሃድሶ እና እሱን በተመለከተ በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ መሪነት በአራቱም እህት ደርጅቶች አማካኝነት የሰጠው መግለጫ በራሱ የህዝብን እምነት አላስገኘለትም። በዚያ ረገድ የአብዛኛው ማህበረሰብ ምላሽ ኢህአዴግ እንደገና "ፈተናን የምናልፍበት ጥበብ" በሚለው የማሞኘት ዘዴ ተከሰተ የሚል ጥርጣሬ ላይ የተንጠለጠለ ነበር። ኢህአዴግ ለሁለት ወራት በየብሄራዊ ድርጅቶቹ ጥልቅ ተሃድሶ ላይ ከከረመ እና በውስጡ በተለይም የህወሃት የበላይነትን ለማስወገድ ከፍ ያለ ትግዕል ሲያካሂድ ከሰነበተ በኂላ ምስጢራዊ አካሄዱን እንደያዘ ለ 17ቱ ቀን ዳግም ስብሰባ ተቀመጠ። እየሾለኩ የሚወጡ አንዳንድ መረጃዎች ኢህአዴግ እየተሰነጣጠቀ መሆኑን እና የለውጥ ሃይሎች በዚያ ስንጥቅ ወስጥ እየመጡ መሆኑን የሚጠቁሙ ስለነበሩ ህዝቡ ከወትሮው የኢህአዴግ ስብሰባ በተለየ መልኩ ነበር ያንን ውጤት የጠበቀው። ኢህአዴግ የገጠመውን ከፍ ያለ የህዝብ ተጋድሎ ለመቀልበስ የወጠናቸው ውሳኔዎች በተለይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሁሉንም ነገር በቁጥጥር ስር አውሎ የቀደመ አገዛዙን ለመመለስ ያደረጋቸው ተግሎች ሁሉ ከሽፈው ተገፍቶ በመጣ የህዝብ ጥያቄ መሰረት ራሱን ማደሱ ገድ ሆነና ከዚያ ፖለቲካ ውስጥ እነ አቶ ለማ መገርሳ እና እነዶክተር አብይ አህመድ ተወደሉ።

በግልጽ እንደሚነገረው የህወሃትን የበላይነት ለመገርሰስ በተለይም ኦሮሞ እና አማራ ያደረጉት ጥምረት አሁን ለታየው ለውጥ ምክንያት ሆኗል። ከዚያ በኂላ በነበረው ሂደት



ጠ/ሚ ዐቢይ አህመድ



አቶ ለማ መገርሳ



ኢ/ር ታከለ ኡማ

ዶክተር አብይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው እንዲመጡ ለማድረግ የለውጥ ቡድኑ ያደረጋቸው ጉዞዎች እንደአጠቃላይ በህዝቡ ዘንድ ከፍ ያለ ድጋፍ እና ከበሬታ አንዲያገኝ ምክንያት ሆኖታል።

ዶክተር አበይ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው መምጣታቸው ብቻ ሳይሆን በበዓለ ሲመታቸው ወቅት ያደረጉት ንግግር የኢትዮጵያን ህዝብ የረጅም አመታት ተስፋ መቁረጥ በአንድ ጊዜ ወደተስፈኝነት እና ደጋፊነት የቀየረ ነበር ማለት ይቻላል።

በይቅርታ፣ በሰላም እና በፍቅር ላይ ያተኮረው እና ያለፈ ታሪካችን ያስከተለብንን መጥፎ ስሜት በጋራ የምናክምበት ዘመን ነው የተባለበት የዶክተር አብይ ንግግር በብዙሃኑ ዘነድ ካሳደረው ከፍ ያለ ተስፋ ባሻገር በዚያው መጠን ያልተገመተ የህዝብ ድጋፍም አስገኝቷል። ከዚያ በኂላ በነበሩት እያንዳንዶቹ ቀናት ህዝቡ በዶክተር አብይ አህመድ ላይ የነበረው እምነት ከፍ እያለ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን ይህ ለውጥ በኢትዪጵያ የፖለቲካ ታሪክ ቀዳሚ መሆኑ ፣ ህዝቡም የዘመናት ጥያቄዎቹ የሚመለሱበት እና በዴሞክራሲ ስም የታፈነው ዴሞክራሲ ዳግም ወደህዝብ ጎራ ገብቶ የሚያገለግልበት ወቅት እንደደረሰ በጽኑ ቃል የሚያረጋግጥበትም ጊዜ ሆኖ ነበር የተሳለው።

ዶክተር አብይ ገና በተሾሙ በጥቂት ቀናት ውስጥ የነበራቸው አቀራረብ፣ ያደረጓቸው ንግግሮች፣ የወሰዷቸው እርምጃዎች፣ ከዚያም ከጠርዘኛው የኢህአዴግ ጫፍ የጠሚቸው ፈተናዎች ሁሉ በህዝቡ ዘነድ ንቁ ክትትል እየተደረገባቸው ቆይተዋል። እያንዳንዷ ቀን ለለውጥ ሃይሉ ህዝብ ድጋፉን የሚያሳይበት ከዚያም አልፎ ለዘመናት በተቃዋሚነት እና ዋልታ ረገጥ በሆነ ጥላቻ ላይ የኖረው ዳያስፖራም ራሱን ለአዲሱ ፖለቲካ ደጋፊ አድርጎ ለማቅረብ ያቆበቆበበት ጊዜም መጥቷል። ይህም ዶክተር አብይ በጥያቄ እና ፍቃድ ወደአሜሪካ ባቀኑበት ወቅት ተገልጧል። በኢትዪጵያ ፖለቲካ ላይ ከፍ ያለ ድርሻ የነበረው የዳያስፖራው እንቅስቃሴ ዶክተር አበይ ከመጡ ወዲህ ትግሉ ውጤት ማስገኘቱን ነበር ሁሉም ያመነው።

## ተግባር ለሙሉ እምነት ምክንያት ሲሆን

የለውጥ ሃይሉ መንግስት ሲሆን ኢህአዴግ እንደፓርቲ ባይቀየርም ስሙ በተግባር ግን ሌላ አካል የመጣ አስኪመሰል ድረስ ኢህአዴግ ባህሪውን አጥቷል። አፋኝነቱን እስረኛ በመፍታት ቀይሯል። ቂመኝነቱን ላሰራቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆን በአገዛዝ ዘመኑ በፈጸማቸው ያልተገቡ ደርጊቶች ህዝብን ይቅርታ በመጠየቅ ሽሯል። የተሰደዱ ►

ኢትዮጵያውያን የነጻነት ታጋዮች እና የህሊና ተጋገሮች ያለአንዳች ቀድመ ሁኔታ ሃገራቸው እንዲገቡ ፣ የተከሰሱባቸው ወንጀሎችም እንዲሰረዙ በማድረግ ከህዝብ ጎን መቆሙን አረጋግጧል። በዚህ ሳቢያም ይህ መንግስት የኔ መንግስት ነው፣ ዶክተር አብይም የኔ ጠቅላይ ሚኒስትር ናቸው የሚል ህዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ ተፈጠረ። ይህ ታላቅ እምነት ማሳያ እና አለሁ ከጎናችሁ ነኝ የሚል ማረጋገጫ ቃል መስጫ ፕሮግራም የተካሄደው ሰኔ 16 ቀን 2010 በመስቀል አደባባይ በተደረገው ፕሮግራም ላይ ነው። ህዝብ በዚያ የድጋፍ ሰልፍ ላይ ከለውጥ ሃይሉ ጋር አብሮ መቆሙንና ይህንን ሃይል ማመኑን በቦምብ ሞቶ እና ቆስሎ በደሙ አረጋግጦ ተመልሷል። ከዚያ በኋላ እምነቱ የዘለቀው ግን ለ7 ወራት ብቻ ነው። የለውጥ ሃይሉ ከ 7ኛ ወሩ በኋላ በብዙሃን ዘንድ እምነት እያጣ እንዲሄድ ምክንያቶች እዚህም እዚያም ተፈጥረዋል። አሁን ለውጡ አንድ አመት ሲሞላው የዛሬ አመት ቅንጣት ሳያስቀር ሙሉ እምነቱን የሰጠ ህዝብ ዛሬ በሶስት ስሜቶች ላይ ቆሞ ይታያል።

## "ለውጡ ውሸትና ጽራጣ ነው"

የቲም ለማን ወይም በአሁን አጠራሩ የለውጡን ቡድን ከመሰረቱ እየተፈታተነው ያለው የህዝብ አስተያየት ይህ "ድራማ ተሰርቶብናል፣ ተጭበርብረናል" የሚለው የህዝብ ቡድን ነው። ይህ በአዲሱ ለውጥ ላይ ሙሉ እምነቱን ያጣው ቡድን በሃገሪቱ ውስጥ የሚከሰቱ የርስ በርስ ግጭቶች ፣ የህዝብ መፈናቀሎች፣ እንዲሁም የፖለቲካ አለመረጋጋቶች መንግስታዊ ያልሆኑ የጎበዝ አለቆች እና አክቲቪስቶች ሃገርን እያሽከረከሩ ከመምጣታቸው ጋር ተያይዞ ሙሉ ጥፋቱን በለውጥ ሃይሉ ላይ ያላክካል። የለውጥ ሃይሉ በተለይም የኦዴፓው ክንፍ በኢትዮጵያ ላይ የኦሮሞ የበላይነትን ለማስፈን ሆን ብሎ የሚሰራ እና ቀስ በቀስ የተሸፈነበትን ማስክ አውልቆ ቅልጥ ባለ የኦሮሞ ብሄርተኝነት የመጣ ቡድን ብሎ ያስባል። ከውጭ የኦሮሞ አክቲቪስቶች ሃገርን የሚያስተዳድር ሃይል እንደሆኑ እስኪሰማቸው ድረስ ያሻቸውን እርምጃ ሲወስዱ፣ ቄሮ የተባለው የወጣቶች ቡድን በየትኛውም የኦሮሚያ አካባቢ የሚካሄድ እንቅስቃሴ ከረሱ ፍቃድ ውጪ መደረግ እንደሌለበት ሲደነግግ መገዳደር ያለመቻላቸው፣ በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች የሌላ ብሄር ዜጎች ሲፈናቀሉም ሆነ ሲገደሉ አጥፊዎችን ለህግ ለማቅረብ ያልቻለ አመራር በመሆኑ እና በሌሎችም በዙ ምከንያቶች ሳቢያ የለውጥ ሃይሉ በጥርጣሬ እና በአይነ ቁራኛ ምልከታ ውስጥ ወድቋል-በዚህ የህዝብ ቡድን። ዶክተር አብይም ይሁኑ አቶ ለማ ኦሮሚያ ውስጥ ለሚከናወነው ብቻ ሳይሆን ከዚያ ተሻግሮ አዲስ አበባ ላይ ፓርቲያቸቸው ለያዘው "ኬኛ" አቋም ደጋፊ ናቸው ብሎ ያምናል። አዲስ አበባ የኦሮሚያ ዋና ከተማ ናት ሌሎች ብሄሮች ሊኖሩባት መብታቸው ቢሆንም በየዞታነት ረገድ ገን የኦሮሞ ናት የሚለው አስተሳሰብ በአዲስ አበባ የሚኖሩ ነዋሪዎችን ማስቆጣቱን እያወቀ ቃል ሳይተነፍስ ቆይቷል ብለው ከስሰውታል። ጀዋር አህመድ አንድ መንግስት ሆኖ የፈለገውን ነገር ሲተገብር እና ሲያዘዝ ይህ የኦዴፓ አካል ዝምታን የመረጠበተን ምክንያት ከዘር ፖለቲካ እና ከኦሮሞ ከልክ ያለፈ ብሄርተኝነት ጋር አያይዞም ይመለከታል። በዚህ በሽር በለዘበ ፖለቲካ እንኳን ፖለቲከ ቀንም ሌሊትም አይታመንም የሚለው የለውጥ ሃይሉ የማይታመን እና የራሱን "ህወሃትን በኦዴፓ" የመተካት ዓላማ ይዞ የመጣ በመሆኑ እምነት ቀርቶ ተቃውሞ ሁሉ ማቀጣጠል ላይ መሰረት ተደርጎ ሊሰራ ይገባል የሚል እምነትም ያለው ይመስላል። በዚህ ቡድን ግምገማ መሰረት የለውጥ ሃይሉ የሚያራምደው ፖለቲካ እምነት ጎድሎታል።

## በጣመኒ እና ባለጣመኒ መሃል

ሁለተኛው የህዝብ ቡድን በለውጥ ሃይሉ ላይ ያለው ምልከታ ለዘብተኛ ይመስላል። ሙሉ እምነቱን ነፍጎታል ነገር ግን እምነትም አልከለከለውም። የነዶክተር አብይ ሩጫ፣ የነአቶ ለማ ኢትዮጵያዊነት ቃል፣ የነአቶ ገዱ አብረን እንዝለው የሚል ጥያቂ ሙሉ በሙሉ ከዚህ አካል ልብ ውስጥ አልወጣም። ነገር ግን በፖለቲካ ሽግግር ሂደት ላይ ሊገጥም የሚችል መንገራገጭ ነውና ሁኔታው ጠርቶ እስኪወጣ ጊዜ እንስጥ የሚል ይመስላል። በብዙ የማይስማማባቸው ጉዳዮች ላይ "ትንሽ ጊዜ አንያቸው" እያለ ፣ በሌላ በኩል በነዶክተር አብይ አመራር እና በአዲሱ የለውጥ ሃይል ላይ የተከፈተ ዘመቻ መኖሩን በማመን ሳያስበው በዚህ ጎራ ውስጥ ተሰልፎ የአጥፊዎች መሳሪያ እንዳይሆን ከፍ ያለ ጥንቃቄ እያደረገም እንዳለ ያሳያል። ጥፋቶቸን እና ወቀሳዎቸን በአብዛኛው ኦልድ ጋርድ በሚባሉት የህወሃት የፖለቲካ ቀመር ሴረኞች ላይ አድርጎ በሌላ በኩል በንዝህላልነት እና ህግ በማስከበር ረገድ በሚያሳየው ክፍተት የዶክተር አብይ አስተዳደረን እየነቀፈና አላማውን እየጠየቀ አሁነም "ጥቂት ጊዜ እንስጣቸው" የሙል ቡድን ነው።

## "አሁኑም ለኢትዮጵያ ካቲም ለማ በላይ አማራጭ የለም"

ሶስተኛው ቡድን አሁንም ቲም ለማ ገና ገሃድ ሲወጣ የነበረውን አቋም እንደያዘ ተስፋውን በሚያያቸው እና የቲሙ አባላት በሚናገሯቸው መልካም ወሬዎች እያደሰ በደጋፊነቱ የቀጠለ ቡድን ነው። ይህ ቡድን ጽንፍ የረገጠ ነው በሚለው የጭፍን ተቃዋሚነት ወነዝ ላይ ሳይንሳፈፍ፣ እንደመሃለኞቹም ሳይወላውል በድጋፉ የቀጠለበት ምክንያት በዚህ የለውጥ ሃይል ላይ ያለው አምነት እንዳልተሸረሸረ በመግለጽ ነው። ይህ የፖለቲካም የአመራርም ጽኑ አምነት በየትኛውም ሁኔታ ፈተናን ተጋፍጦ ከመቀጠል ጋር የተሰናሰለ መሆኑን በመግለጽ የለውጡን ሃይል አስከመጨረሻው ድረስ ደግፎ ከመሄድ የተሻለ አማራጭ የለም ብሎም ያምናል። የለውጥ ሃይሉ በህዝብ አመኔታ ማጣት ተገፍቶ በተግዳሮት ብዛት ቢሰነጠቅ በዚያ ስነጥቅ ገብተው ኢትዮጵያን ወደማያባራ ቀውስ ለመምራት የተዘጋጁ አካላት መኖራቸውን ስለሚያምን ለነዚያ አካላት በር ላለመክፈት የለውጥ ሃይሉ ከጥፋቱ እየታረመ እና እየተገሰጸ እንዲሄድ በዚያውም የጉዞው አነቅፋቶች እየጠሩ ወደፊት በሃገሪቱ ለሚኖረው የተረጋጋ መንግስት እና የተረጋጋ ፖለቲካ መሰረት እንዲጣል አበዝቶ የሚወተውት ነው። በዚህም ሳቢያ ሳይታክት በሶሻል ሚዲያው ላይ ወየም በተገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ የዶክተር አበይ ደጋፊነቱን ማሳየቱን አላቆመም። በዚህ አካል ምልከታ መሰረት አምነት ያጣ ፖለቲካ በተለይ የህዝብ እምነት ያጣ ፖለቲካ የሚያምር መጨረሻ የለውምና በዚያው መጠን የለውጥ ሃይሉ በዚህ ችግር እንዳይጎዳ እምነትን ገንብቶ ድጋፍን አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ነው ብሎም ያምናል።

## እመኑኝ!

## የለውጥ ሃይሉ እሮሮ

"የብሔር ፖለቲካ ሁልጊዜ ጥርጣሬን እንጂ መተማመንን አያመጣም" ይላል የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ አባንግ ሜቶ። ያለመተማመን ምክንያቱ፣ የህዝብ መጠራጠር መነሻው ሃገሪቱ ስትዋቀር በኢህአዴግ የተሰመረባት የብሄር ፖለቲካ ጦስ ነው። የብሄር ፖለቲካ እንደኢትዮጵያ ባለ ከ80 በላይ ቋንቋ የሚናገሩ ሰባ ምናምን ብሄሮች ባሉበት ሃገር በቀላሉ ለማስወገድ የሚቻል የፖለቲካ አይነት አይደለም። ይህ ፖለቲካ ለዘመናት መብታችን ተረግጧል ብለው የተቆጩ ብሄሮች እኩልነታቸውን እና በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡበት ስለሆነ በአንድ ቀን ሊታጠፍ የሚችል አስተሳስብም አይደለም። ከዚህ አንጻር በዘዴ ሊያዝ እንደሚገባው ነው የፖለቲካ አዋቂዎች የሚስማሙበት።

ያም ሆኖ የብሄር ፖለቲካ የጠነነ ሆኖ ሲወጣ እና ሃገርን በዜግነት ፖለቲካ የመመልከቻውን መነጽር ሲሰበር፣ ዜግነት በብሄር ስር ሲደፈጠጥ እና የግለሰብ መብት ተመልካች ሲያጣ በዚያው ልክ በአንድ ሃገር ውስጥ የሚኖረው የፖለቲካ ቅረቴታ እና አለመተማመን እንዲሁም እምቢ ባይነት እየጎላ ይመጣና የመፍረስ እና የመፍረክረክ ችግር ሊገጥም ይችላል። የብሄር ፖለቲካ የሚያራምዱ ሃገራት መጨረሻቸው ወርደው ወደዘር መቋጠር እና ከዚያም ሲያልፍ ወደ ንጹህ ዘር ቆጠራ መሸጋገር ከፍ ሲልም የዘር ማጽዳት ግጭት ውስጥ መግባት ነው። ይህ በብዙ የዓለማችን ሃገራት የታየ ሃቅ ነው። ለዚህም ነው የብሄር ፖለቲካ በሚራመድባት ሃገር ላይ መተማመን ከባድ ነው የሚባለው።

በግለሰብ ደረጃ ለውጡን ከሚመሩት ውስጥ የዚህ አለመታመን ትልቁ ጦስ ያረፈው በኦዴፓ ላይ ነው። የይህ አለመታመን የገጠማቸው አቶ ለማ ፣ ዶክተር አብይ እና ኢንጂነር ታከለ ናቸው። ከአዴፓ ወገን የዚህ ግለሰባዊ አለመታመን ምልክት በአቶ ደመቀ ላይ የከስቶ የነበረ ቢሆንም በሂደት አሁን ወደ ዶክተር አምባቸው የተሸጋገረ ይመስላል። በአብዛኛው ገን የህዝቡ እምነት መሸርሸር የተንጸባረቀው

አዴፓ ላይ አንጂ መሪዎቹ ላይ አይደለም። በዚህ ረገድ አዴፓ በደርጅትም በግለሰብም ደረጃ ያለመታመን ችግር ላይ ወድቋል ማለት ይቻላል።

አቶ ለማ መገርሳ በቅርቡ ባለሃብቶቸን ሰበስበው ባናገሩበት ወቅት እጅግ የተማረረ የሚመስል "እመኑን" አይነት ነገር አድርገዋል። በኢትዮጵያዊነት አቋማቸው፣ አዲስ አበባን ዴሞግራፊ ለመቀየር አስበዋል መባላቸው ፣ የኦሮሞን ተፈናቃዮች አዲስ አበባ ለማስፈር መፈለጋቸው፣ መታወቂያ ከአዲስ አበባ ለኦሮሞዎች መታደሉን እና የመሳሰሉትን ክሶች በመደመር አሉባልታዎች ብለዋቸዋል። ይህ ሁሉ እንደማይመለከታቸው እና ዛሬም ነገም የሁሉንም ኢትዮጲያዊ እና ኢትዮጵያዊነት ጉዳይ ላይ አትኩረው እንደሚታገሉ በመናገር ሰፊ እና ረጅም ንግግር አድርገዋል። ሁሉንም ተባልኩ የሚሉትን ነገር ከፌስ ቡክ አመጥተው ዘረግፈውታል። በዚህ መጠን ለፌስ ቡክ መልስ መስጠት ነበረባቸው ወይ የሚለው ጉዳይ ጥያቄ ቢሆንም አቶ ለማ ግን ዳግም ህዝብ በለውጥ ሃይሉ ላይ አምነት ሊያሳድር እንደሚገባ ፣ እንደሚባለው ማጭበርበር እና ድራማ የሚባል ነገር አለመኖሩን ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ ታከለ ዑማም በተመሳሳይ አዳማ የከተማውን አስተዳደር አካላት ገምገማ ሲመሩ ስለራሳቸው የተጠና የሚመስል "በአሉባልታዎች ዙሪያ የተሰጠ ምላሽ" አቅርበዋል። እንደ ከንቲባው አባባል "ታከለ ከተራ አክቲቪስት ጋር ተደምሮ የሚታይ ሰው አይደለም" ። ኢህአዴግን አንካን ያልፈሩ ሰው መሆናቸውን ታጋይ እና የአቃም ሰው አንደሆኑ ፣ ሌላ አጀንዳ ይዘው እንዳልመጡ፣ ኦሮሞን የመጥቀም እና ሌላውን የመጉዳት ሃሳብ አንደሌላቸው፣ በአጠቃላይ በሰብዕናቸው እና በድርጅታቸው እንዲሁም በአስተዳደራቸው የሚወራው ሁሉ ተራ ፕሮፓጋንዳ መሆኑን ቁጭ ብድግ እያሉ ተናግረዋል። ማጠቃለያቸውንም ህዝብ ይህንን ተግባር ማመን አንጂ ለአሉባልታ ጆሮውን መስጠት የሌለበት መሆኑ ላይ አድርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ በተለያዩ መድረኮች የተናገሩት ይህንኑ ነው። ሰም ማጥፋት አንዳለ ነገር ግን የለወጥ ሃይሉ የጀመረውን መንገድ አንደማያቃርጥ እና ለማንም ስም አጥፊ መንገድ አንደማይታጠፍ ነው አስምረው የተናገሩት። የርሳቸውም ማጠቃለያ ቃል በቃል ባይሆንም ያው "እመኑን" ነው ። ዶክተር አምባቸው በደሴ ከከተማው ህዝብ ጋር ባደረጉት ውይይት በገለጽ ቃል "እኛን ደግፉ፣ ከኛ ጋር ተጓዙ፣ እመኑን፣ ምንም አጀንዳ የለንም፣ ህይወታችነን ጥለን የመጣነው ለናንተ ለመስራት ነው" ብለዋል።

እመኑን ባለመታመን ውስጥ የሚመጣ ነው ካልን ይህ የለውጥ ሃይል አለመታመንን በመታመን ለመለወጥ ምን ማድረግ አለበት የሙል ጥያቄ ይነሳል። በቀላል ቋንቋ የህዝቡን ጥያቄ መመለስ። የተደበቁ የሚመስሉ ነገሮችን ይፋ ማውጣት። የብሄር ስሜት ላለመጉዳት ተብሎ የሚታለፉ ወንጀሎችን መጋፈጥ፤ከዚያም ሀግን እያስከበሩ መጓዝ። የአዲስ አበባንም ሆነ ሌላ ማናቸውንም ጥያቄ በግልጽ ቋንቋ በማያሻማ መንገድ መመለስ መቻል። ይህ እምነትን ዳግም መልሶ ለመቀዳጀት ብቸኛው አማራጭ ነው። ብዙዎች ደጋግመው የሚተቹት "መሪዎች ለፌስ ቡክ ትችት ምላሽ እየሰጡ የሚቀጥሉት መቼ ድረስ ነው? " የሚለው ጥያቄ ግን ከዚህ በኂላ በስራ ብቻ ምላሽ ሊሰጥ እንደሚገባ የሚጠቁም ነው።





ብሩክ አስቻለው

# ሰውየው ሲስተካከል ዓለሟ ትስተካከላለች

የአለምን ካርታ በአንድ ገፅታ፣ የሰውን ምስል በግልባጩ ገጽ የያዘ ወረቀት የተቀደደባቸው አባትና ልጅ ወረቀቶቹን ለመቀጣጠል የሚጥሩት የአለምን ካርታ እንደነበረው ለማስተካከል ነበር። ይህንንም ለመገጣጠም የአህጉሮችን ትክክለኛ ቦታ የማወቅ ሒደትን ይጠይቃልና አባቱ ካርታውን ለማምጣት ሲጣጣር ያየው ብልህ ልጅ አባዬ በጀርባ ገፅ ያለውን የሰውዬውን ምስል አስተካክለው ሰውዬው ሲስተካከል አለሟ ትስተካከላለች አለው ይባላል። እኛ ስንስተካከል አለም ትስተካከላለች፤ እኛ ስንስተካከል ኢትዮጵያ ትስተካከላለች። ሐገር የሰዎች ነፀብራቅ ደማቅ ጥላ ነች፤ እያንዳንዳችን ሐገራችንን የምንወድ ሁሉ ኢትዮጵያ ሆና ከምንፈልገው ከፍታ እና ማማ ደርሳ ልናያት የምንችለው እኛ በምንሰጣት ክብር፤ በምናለብሳት በምናጎናፀፋት ሸማ፤ በምንመግባት ህብስት፣ በምንገነባላት ቁመና እንጅ ከሰማይ መና በመጠበቅ አይደለም። እኛ ከተስካከልን ያልተስተካከለች ሐገር አትኖርም። ያጣነው ይህንን ነው። ግለሰባዊ፣ ቤተሰባዊ፣ ማህበረሰባዊ ስብዕናችን ካልተገነባ፤ በሰው ኃይል ልማትና ግንባታ ላይ ካልተሰራ በተገቢው መንገድ የተሰራች አገር አትኖርም። በዚህ ወቅት ሐገራችን ውስጥ የምናየው ተስፋ ከስጋት እንዳይርቅ የሚያደርጉ ሳንካዎች ይኖሩታል። እልባት ማግኘታቸው ግን አይቀርም። የምናስተውለው  የምሁራን፣ የአክቲቪስቶች፣ የኤሊቶች ተሳትፎ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም፤ የራሱን እምነትና ሐሳብ ለመጫንና ለማጥመቅ የሚራወጠው አካል ምክንያታዊ ትውልድ ለመቅረፅ/ በምክንያት በሚነቅፍ በምክንያት የሚደግፍ / ለማፍራት የሚታገለውን ኃይል ለማሽመድመድ ላይ ታች ማለቱ አልቀረም።

የብሔር ክፍፍሉ፣ የማህበራዊ ሚዲያው አሉታዊ መልዕክት /በጎ ጎኑ እንዳለ ሆኖ/ የመንግስት ግልፀኝነት የጎደለው አንዳንድ አካሄዶችና ፍትህ አለማስፈን ባመጣው ውጤት መሪዎቻችን በተለያዩ መድረኮች ብቅ እያሉ አንዳንዴ በፍጥጫ ከፍ ሲል ደግሞ በመግለጫ ማየታችን ያልተከወነ ብዙ የቤት ስራ ስላለብን ነው፡፡ ለውጥ ላይ ባለች ሀገር እንዲህ አይነት ነገሮች የሚታዩበትም ይሆናልና አያስከፋም። ለተለያዩ መሠረታዊ ችግሮች መፍትሔ ለማበጀት ኮሚቴ ማወቀሩ ይህ ጉዳይ በእነዚህ ይታይ መባሉም ውጤቱ ፍትሐዊ እስከሆነ ድረስ በምክክር የተወሰነ ነገር ሁሉ መልካም ነው "ተማክረው የፈሱት ፈስ አይሸትም" እንዲሉ።

ዛሬ ይህን ፅሁፍ እንድፅፍ ያነሳሳኝ ሰሞኑን ህግ ይወጣለታል/ ይፀድቅለታል የተባለው hate speech በአማርኛው የጥላቻ ንግግር ጉዳይ ወዴ ወዴት እንድል አድርጎኛል። እንዴት ቢሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ባልተፈቱበት ሰፊ ቋት ውስጥ ተቀምጠን ይህን ማሰብ ጊዜው ነውን?

እንዲህ አይነት ንግግሮችን ለማምከን የሌሎች ችግሮች መፈታት በራሱ ትልቅ መልስ አለው። ዋነኛ ችግር የሆነው የብሔር ፖለቲካ ምንጩ ሳይደርቅ ይህን ተከትሎም ይህ ክልል የኔ ነው ከዚህ ውጣ፤ እኔ ከዚች ከተማ ልዩ ጥቅም ከፍ ሲልም ባለቤትነት ይገባኛል የሚሉ የተለያዩ ችግሮችን በሐሳብ ልዕልና ሳናስታርቅ በዚህ እየተቋሰልን ባለንበት ሁኔታ የጥላቻ ንግግር የህግ ማዕቀፍ ማውጣት ከፈረሱ ጋሪው ቀድሞ አይሆንምን?  ከዚህ ባሻገር ግን እንደ ፀረ ሽብር ህጉ በፈለግነው መንገድ እየተረጎምን የመናገር የመፃፍ የመተቸት ዲሞክራሲያዊ ነፃነትን አይጋፋም የሚል እምነት የለኝም። ለነገሩስ ምን መናገር ነው ጥላቻ? ማንን መናገር? ለምን መናገር ነው ጥላቻ ? እንደ ህገ መንግስት በአንቀጽና በንዑስ አንቀጽ መዘርዘር ሳይፈልግ አይቀርም።

እንዲህ ዓይነት ህግን ሌሎች ሐገሮችም እየተጠቀሙበት ነው እንል ይሆናል። ሁሉንም ነገር እንደወረደ መቀበል  የማንችልበት የሐገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እና የዴሞክራሲ ባህላችን ገና ዳዴ እያለ ያለ በመሆኑ መነሻ ማድረግም ተገቢ አይሆንም። በንግግር አለመታረምን የማረሚያ ህግ በማውጣት አንፈታውም ሰውየው ሲስተካከል አለሟ ትስተካከላለች።

# ከ"ጥላቻ ንግግር" ረቂቅ ሕጉ ጀርባ ምን አለ?

የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ መንግስት በአስራ ሁለት ወራት እድሜው በርካታ ቀውሶችን አስተናግዷል፡፡ የለውጡ ቡድን ብልጠት በተሞላበት መንገድ "አይነኬ" የተባለውን የስልጣን ባለቤት ገፍቶ በመጣል፣ ኃላፊነቱን ከጨበጠ በኂላ ሀገሪቱ ብሩህ ብርሃን እንደምታይ ተስፋ ቢጣልበትም፤ ይህንን የብዙዎች ምኞት የሚያቀጭጭና የሚያደበዝዝ እንቅስቃሰሴ ከየአቅጣጫው በስፋት መታየት ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡

በተለይም ከተደላደለ የምቾት ወንበራቸው ለመነሳት ግድ የሆነባቸው፣ የእዚህች ሀገር እስትንፋስ "እኛ ብቻ ነን" ያሉት ወገኖች ከጅምሩ የጠነሰሱት ለውጡን የመቀልበስ ጅማሮ፤ በእስካሁኑ ቆይታው ግቡን መምታት ባይችልም፣ በየክልሎቹ ዜጎች እንዲፈናቀሉ፣ የብሔር ግጭቶች በተደጋጋሚ እንዲከሰቱ በር ከፍቷል፡፡ ሕወሓት መራሹ መንግስት ስልጣኑን አራዝሞ፣ ለዘመናት ሀገርን ሲመዘብር የቆየበት የብሔር ፖለቲካ፤ ድርጅቱንና ሎሌዎቹን ከቤተ መንግስት አርቆ፣ በአንድ ቦታ ተሸሽገው እንዲቀመጡ ከማስገደድ ባሻገር ለሕዝቦች "የሰላም ነቀርሳ" በመሆን አላስፈላጊ ውጤት አምጥቷል፡፡

በተለይም ጽንፍ የያዘ የዘረኝነት ፖለቲካን የሚያራምዱ ፖለቲካኞች፣ የፓርቲ አመራሮችና አክቲቪስቶች በሚሰጧቸው አስተያየቶች፤ በሚያደርጓቸው ውይይቶች፣ ማህበረሰቦች ለዘመናት ተዋልዶ፣ ተግባብቶና ተፋቅሮ ከኖረ ባህላቸው አፈንግጠው፤ ወደ ግጭትና ጦርነት በማምራት፣ በጠላትነት እንዲፈራረጁ ዓይነተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተካረረ የመጣውን የብሔር ግጭት ከማስቆም ባሻገር፣ በሀገሪቱ እውን ይሆናል ተብሎ የተጣለበትን ተስፋ ካለበት በተሻለ ሁኔታ ለማራመድ የጥላቻ ንግግርን መሰረት ያደረገ የሕግ ረቂቅ ማዘጋጀት አማራጭ የሌለው መፍትሄ ተደርጎ መወሰዱን ከሰማን ሰነባብተናል፡፡

የጥላቻ ንግግር የሕግ ረቂቅ መዘጋጀቱ አግባብ ቢሆንም፤ ረቂቅ ሕጉ የያዘው አጠቃላይ ነጥብ በመሰል ንግግሮችና ፅሁፎች የሚመጣውን ችግር ለመቅረፍ ከማስቻል በዘለለ መልኩ፣ መንግስት አጥብቀው የሚተቹትን፣ በሀሳብ ልዩነት የሚጎትቱትን ቡድኖች፣ ግለሰቦችና የሚዲያ ተቋማት በሰበቡ ለመምታትና ለማጥፋት ቢጠቀምበትስ? የሚለው ነጥብም እግረ መንገድ ሊታሰብበት ይገባል፡፡

የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታን ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ ጋር በማዛመድና በማጥናት፤ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ቀውስ ከመቼውም ጊዜ በላይ እያፈጠነ የሚገኘውን የጥላቻ ንግግር ለመቆጣጠር ረቂቅ ሕጉን እንዳዘጋጀ ቢገልፅም፤ የረባ ያልረባ ወሬ እየለጠፉ፣ በሰዎች ተመሳሳይ ስም ሀሰተኛ አካውንት በሚከፈቱ የፌስቡክ ፅሁፎችና አስተያየቶች የተማረረው መንግስታችን፤ ህግና ስርዓትን ጠብቀው እየሰሩ ያሉ፣ አምባገነኑ ስርዓት አክስሟቸው የቆዩና ዳግም በመመለሱ ሂደት ውስጥ ሆነው ባለፉት አስራ ሁለት ወራት በርካታ መረጃዎችን ለሕዝብ ሲያደርሱ የቆዩ የነፃው ፕሬስ ውጤቶች በዚሁ ሕግ ተጠልፈው እንዳይወድቁ የሚመለከተው አካል ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ኢህአዴግ ከጅምሩ ትችትን የማይወድ፣ አቅጣጫ የሚያመላክቱትን ጋዜጠኛና ጦማሪያን በተቃዋሚነት የሚፈረጅ መሆኑን ስናስብ፤ እንዲሁም የለውጥ ቡድኑ ወደ ስልጣን ከመጣበት ዋዜማና ማግስት ጀምሮ አዲሱን መንገድ በማበረታት ረገድ ጫንቃችን መሸከም ከሚችለው በላይ የሆነውን የወረቀት ዋጋ ተቋቁመን፣ ለሀገራችን የበኩላችንን አስተዋፅኦ ስናደርግ የነበርን የነፃው ፕሬስ ውጤቶች ፣ ለችግሮቻችን መፍቻ የሚሆኑ መፍትሄዎች ባይበጁልን እንኳ፤ ነፃው ፕሬ ለሩብ ክፍለ ዘመን ያበረከተው አስተዋፅኦ በጠ/ሚሩ ዘንድ "ግምት" ባልተሰጠበት ሁኔታ፤ ይህ ዓይነቱ ሕግ አፋኝ ሆኖ ወደ እኛ ፊቱን እንዳያዞርብን እንሰጋለን፡፡ የስጋታችን ምንጭ ሙያችንን በነፃነትና በእውነት ላይ ተመርኩዘን መስራት ስለምንሻ መሆኑም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ከዚህ በኂላ መንግስት የጥላቻ ንግግርን መሰረት አድርጎ ያረቀቀው ሕግ፣ የሰዎችን ዴሞክራሲያዊ መብት (ፈር የለቀቀ ባልሆነ መልኩ) እስካልተገፋ ድረስ ተግባር ላይ ቢውል ጉዳቱ የከፋ አይሆንም፡፡ ከምንም በላይ ግን በጉዳዩ ላይ ሕዝብ በግልፅ ቢመክርበት መልካም እንደሚሆን ሳንጠቁም አናልፍም፡፡


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**

**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(**ከአሜሪካ**)

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
መለስ ሽኔ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ (**ከሲውዘርላንድ**)
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
መስፍን ጌታቸው
አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ(**ከአሜሪካ**)
ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
ታምራት መርጊያ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ባሳዝነው ወንድምነህ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



# "የህዳሴውን ግድብ ጎጃም ላይ በአነስተኛ ወጪ መስራት ይቻል ነበር!!!"

ኢ./ር አበበ አያሌው

*ኢ./ር አበበ አያሌው በደርግ የስልጣን ዘመን፣ እንዲሁም ሕወሓት መራሹ መንግስት ሀገሪቱን በተቆጣጠረበት ወቅት ለስምንት ዓመታት በመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ በበላይ ኃላፊነትና የመለስ ዜናዊ የኢኮኖሚ አማካሪ በመሆን አገልግለዋል። የዘር ፖለቲካ፣የጎጠኝነት መንፈስ ለኢትዮጵያ አንድነት አደጋ መሆኑን በመግለፃቸው ከቀድሞው ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ ጋር ውዝግብ ውስጥ በመግባት ስራቸውን ለመልቀቅ ከመገደዳቸው በተጨማሪ እስካሁን ድረስ ባልተነሳ እግድ፤ ከሀገር ለመውጣትና ለመግባት በኢሚግሬሽን የይለፍ ወረቀት እንዲንቀሳቀሱ ተደርገዋል። በሕይወትና በስራ ገጠመኞቻቸው ዙሪያ ከኢ./ር አበበ አያሌው ጋር ሰፋ ያለ ቆይታ ያደረገው የግዮን ጋዜጠኛ ሮቤል ምትኩ ከአንጋፋው ባለሙያና የሀገር ባለውለተኛ ጋር የነበረውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርቦታል። መልካም ቆይታ።*

**ግዮን፦ በደርግ የስልጣን ዘመን እናንተ ያቋቋማችሁት የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ አሁን ካለው የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱን እንዴት ይገልፁታል?**

ኢ/ር አበበ፦ በጣም ይለያያል ልዩነቱ ሰፊ ነው። በዛ ወቅት የሚሰራው በንፅህና ነው፤ የሀገር ሀብት አይመዘበርም። የደርግን እንተወውና በጃንሆይ ጊዜ የህዝብና የሀገር ሀብት አይዘረፍም። በንጉሱ የስልጣን ዘመን "የአምስት ብር የመንግስት ነዳጅ ቀድተው የግል እርሻቸውን ለማየት በመኪና ሄደዋል" ተብለው ስለተወነጀሉ ብቻ ከስራ የተባረሩ፣ የጃንሆይ የሀገር አስተዳደር ምክትል የነበሩ ሰው አውቃለሁ። በፊት እዚህ ድረስ ጥብቅ ስርዓት ነበር።

በእኛ ጊዜ (በደርግ ዘመን) ከአምስት ሺኅ ብር በላይ ገንዘብ በቼክ እንጂ በካሽ አይንቀሳቀስም። የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን ስርዓት አውጥተን ስናቋቁመው፣ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ነው። ሲቪል መ/ቤት ነው ፣መከላከያ አልያዘውም። እንደውም አንዳንድ ጊዜ "ከጨረታ ውጭ እንግዛ፣እንስራ" ብለው መከላከያዎች እኔን ከሰውኝ ሁሉ ያውቃሉ፣ ከጎድ መንግስቱ ጋርም አጋፍጠውኛል።

**ግዮን፦ ክሱ ምን ነበር?**

ኢ/ር አበበ፦ "አምስት ሺኅ ወታደር በየቀኑ እየሞተብን፣ አንተ አምስት ሺኅ ብር፣ አስር ሺኅ ብር ጠፋ እያልክ፣ ዕቃ እንዳይገዛ፣ ስራ እንዳይፋጠን ታጓትታለህ" የሚል ክስ ነው። በጊዜው ምንም ዓይነት ግዢ ሲፈፀም በተጠናና ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ እንዲካሄድ ጥብቅ ቁጥጥር ከማድረግ ባሻገር፣ ያንን የሚያስፈፅሙ ጠንከር ያሉ ግብረ ኃይሎች በተለያየ ጊዜ ይቋቋሙ ነበር። በዚህ መልክ በንፅህና ነበር በደርግ የስልጣን ዘመን የሚሰራው፣ አንድ ብር የሚነካ ሰው የለም። አሁን የምንሰማው የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ሀገር ከሚሸከመው በላይ "ጉድ" እንደያዘ ነው።

**ግዮን፦ ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያምን ከስልጣን ለማውረድ ከተደረገው መፈንቅለ መንግስት ጋር ተያይዞ እርስዎ እጅዎ በተዘዋዋሪ እንደነበረበትና የጄነራል ፋንታ በላይ የቅርብ ዘመድም እንደሆኑ ሲነገር ነበርና እስኪ ይሄንን ጉዳይ ወደ ኋላ መለስ ብለው ያጫውቱን?**

ኢ/ር አበበ፦ እሱ የሚገርም አጋጣሚ ነው። እኔ በጊዜው ኩዴታው (መፈንቅለ መንግስቱ) እንዳለ አላውቅም። ከላይ በጠቀስኩልህ መንገድ በመከላከያ ኢንዱስትሪ ውስጥ ጥብቅ ቁጥጥር ከሚያደርጉ የተለያዩ ግብረ ሃይሎች ውስጥ በአንዱ እኔና ጄነራል ፋንታ በላይ አብረን እንሰራለን፤ (በርግጥ በሌሎቹ ቡድኖች ውስጥም አለሁበት) በ1980 ዓ.ም የተቋቋመውና በጀነራሉ የሚመራው የዚህ ግብረ ኃይል ላይ አባል ሆኜ በሳምንት አንድ ቀን እንሰበሰባለን፣ ግን ስለ መፈንቅለ መንግስቱ ፈፅሞ አላውቅም።

ኩዴታው ሲካሄድ እንደ አጋጣሚ ሆኖ አንዳንድ ነገሮች ተፈጠሩ፤ በዛን ወቅት "ከፋንታ በላይ ጋር የነበረ ሰው ነው" ብለው ብዙ ሊጎዱኝ ፈልገው ነበር። ግን ኮ/ል መንግስቱ በቅርበት ያውቁኛል፤ እንደማልዋሽና እንዲህ ዓይነት ነገር ውስጥ እንደማልገባ ስለተረዱ ብቻ ነው የከፋ ችግር ላይ ሳልወድቅ የቀረሁት እንጂ፣ "ጄነራል ፋንታ በላይ የእናቱ ልጅ፣ ወንድሙ ነው" ተብዬም ታምቻለሁ። በርግጥ የጄነራል ፋንታና የእኔ እናት ስማቸው አንድ ነው፤ በትውልድም የአንድ አካባቢ ሰዎች ነን፡ ፡ የጎንደር ተወላጆች ከመሆናችን ሌላ የሩቅ ዘመዴ ነው። አንድ ወቅት በስራ አጋጣሚ ለአለቃዬ ኮ/ል ነሲቡ ታዬ "ኢ/ር አበበ ወንድሜ ነውና በደንብ ጠብቁት" ብሎ ተናግሮ ነበር። እርሱ ወንድሜ ሲል የገለፀበት መንገድ የአንድ አካባቢ ልጅነታችንን ለመግለፅ እንጂ የአንድ እናት ►

ልጆች መሆናችንን አልነበረም፡፡ እንደውም የቅርብ ዘመዴም አይደለም፡፡

**ግዮን፡- እነ ጄነራል ፋንታ በላይ መፈንቅለ መንግስቱን ባካሄዱበት ቀን እርስዎ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ነበሩ፤ ምክንያትዎ ምን ነበር?**

ኢ/ር አበበ፡- በዛን ዕለት ጄነራል ፋንታ በላይ የሚሰበስበው አንድ ኮሚቴ ነበር፤ ግን ያኔ እሱ "አልገኝም" ስላለ እነ አቶ ዮሴፍ ሙለታ፣ አቶ ሽመልስ አዱኛ፣ አቶ ተከዘሸዋ አይተንፍሱ፣ ካፒቴን ኤልያስና ጀነራል ባዩን (የመኮድ ኃላፊ) የመሳሰሉ ሰባት ሚኒስትሮችን ይገኔ እንድሄድና ጋፋት ኢንጅነሪንግን እንዳስገመግም የታዘዝኩት በአለቃዬ በኮ/ል ነሲቡ ታዬ ነው፡፡ መፈንቅለ መንግስቱ በተካሄደ በሳምንቱ "ጋፋት" ኢንጂነሪንግ ይመረቅ ስለነበር ለእሱ ዝግጅት ግምገማ ልናካሂድ ነበር የተጓዝነው፡፡

ስንመለስ ሆራ አረፍን፣ ወደ ዘጠኝ ሰዓት አከባባቢ ስለሆነ የተመለስነው ምሳ ስንበላ፣ ስንጫወት ስላረፈድን የሚጠጣ ይምጣ ተባለ፡፡ ሚኒስትሮች ስለሆኑ "ውስኪ ይቅረብ፣ ኮኛክ ይቀዳ" እያልኩ የማዘው እኔ ስለሆንኩ በደንብ ሳስተናግድ ቆየሁ፡፡ በዛን ሰዓት አውሮፕላን በላያችን ላይ ይበራል፣ ለካስ ኩዴታው እየተካሄደ ነው፤ እኔ ግን ምንም አላውቅም፡፡ በኂላ "እሱ የደስ ደስ ሚኒስትሮቹን ውስኪ እየጋበዘ፣ ደብረዘይት ይዝናና ነበር" ነው የተባልኩት፡፡ ሁኔታውን ያወቅኩት አዲስ አበባ ስገባ ነው፡፡

**ግዮን፡- ከመፈንቅለ መንግስቱ ጋር በተያያዘ ጋፋት ኢንጅነሪንግ ሲመረቅ በቦታው እንዳይገኙ፣ ብዙ የለፉለትና የደከሙለት፣ ዕውን እንዲሆን ያስቻሉትን ፋብሪካ በወሳኙ ቀን እንዳያዩ ተደርገዋል፡፡ ምክንያቱ ምን ነበር?**

ኢ/ር አበበ፡- የሚገርምህ ጋፋት ሲመረቅ ንግግር የማደርገው እኔ ነበርኩ፡፡ አስቀድሞ በተያዘው ፕሮግራም መሰረትና የፕሮጀክቱ የበላይ ጠባቂም እኔ ስለሆንኩ፡፡ ግን እሱ ቀርቶ በቦታው አልተገኘሁም፤ በእኔ ምክንያት ም/ጠ/ሚ/ር ኃይሉ ይመኑ ሁሉ እንዳይገኙ ተደረገ፡፡ በምረቃው ቀን "ኤርፖርት ከሮሚኒያ የሚመጣ ም/ጠ/ሚኒስትር ስላለ ሄደህ ተቀበል" ነው የተባልኩት፡፡ ም/ጠ/ሚኒስትር የእኔ የስልጣን ፖዚሽን እንዳልሆነ በመግለፅ ስከራከር፤ "ኃይሉ ይመኑ ስለሚቀበሉ፣ ከእርሳቸው ጋር ሄደህ ተቀበል" ተብዬ ነው በቀጥታ የታዘዝኩት፡፡ ጓድ ኃይሉ ይመኑ ኤርፖርት አልመጡም፤ ቢሮአቸው ናቸው፣ ጋፋትንም አልመረቁም፣ የበላይ ሃላፊ ግን እርሳቸው ነበሩ፡፡

ኤርፖርት ቪ. አይ ፒ ቁጭ ብዬ ቡና እየጠጣሁ እስከ አምስት ሰዓት ቆየሁ፣ በኂላ ተጠርቼ "የሚመጣ እንግዳ የለም" ተባልኩ፡፡ "ያዘጋጀኸውን ንግግር ለሌላ ሰው እንድታስረክብ፣ አንተ እንግዳ ትቀበላለህ" ብሎ ሌሊት የደወለልኝ፤ የቤተ መንግስቱ ልዩ ጥበቃ ኃላፊ አስር አለቃ መንግስቱ ገመቹ ነው፡፡ እኔም " አንተ አይደለህም የምታዘኝ፣ አለቃዬ ይንገረኝ" ስለው ከአስር ደቂቃ በኂላ ኮ/ል ነሲቡ ታዬ ደወለና ያንኑ ቃል ደገመልኝ፡፡ ጧት የቤተ መንግስት መኪና መጥቶልኝ ነው ኤርፖርት ድረስ የሄድኩት፡፡ ለካስ "የጀነራል ፋንታ በላይ ወንድም ነውና አደጋ ሊያደርስ ይችላል" ተብዬ ፕሬዝዳንት መንግስቱን እንዳልጠጋ፣ በምረቃው ቀን እንዳልገኝ ሆን ተብሎ የተሸረበ ሴራ ነበር፡፡ መጀመሪያ ግን ይሄን ሁሉ አላውቅኩም፡፡ በኂላ ጠ/ሚ/ር ቢሮ ሄጄ ም/ጠ/ሚኒስትሩ ኃይሉ ይመኑን "ጉዳዩ እንዴት ነው" ስላቸው "እኔም በአንተ ምክንያት ቀርቻለሁ" ብለው ምስጢሩን ቢሮአቸው መናገር ፈርተው፣ ውጭ ይዘውኝ ወጥተው ነው ያጫወቱኝ፡፡

**ግዮን፡- ታዲያ ሀቁ እንዴትና በምን ዓይነት አጋጣሚ ሊወጣ ቻለ?**

ኢ/ር አበበ፡- አንድ ዓመት ያህል ስራዬን እየሰራሁ፣ የፕሮጀክቱ ኃላፊ ሆኜ በስልጣን ከፍ ሳልል በእግድ መልኩ ቆየሁ፡፡ እግዱ ሲነሳልኝ ከሊ/መንበር መንግስቱ ኃ/ማርያም ጋር እንደ ልብ አብሮ የመንቀሳቀስና የመሄድ ዕድል አገኘሁ፡፡ በፊት በሄሊኮፕተር አብሬያቸው የትም ቦታ እሄድ ነበር፤ በዛ አንድ ዓመት ጊዜ ግን "አንተ በመኪና ቀድመህ ሂድ" ተብዬ ለብቻዬ እጓዛለሁ፤ እሳቸውን እንዳላገኝ አንዳንድ ችግሮች ነበሩ፡፡ ግን ይሄም ሆኖ አልተሰማኝም፣ ስራዬን ነበር የምሰራው፡፡

ከአንድ ዓመት በኂላ በሆነ ቀን "ስምንት ሰዓት ወደ ሰሜን ኮርያ ከፕሬዝዳንት መንግስቱ ጋር ስለምትሄድ ተዘጋጅ" ተብዬ ሰባት ሰዓት ላይ ነው ተነገረኝ፡፡ "እንዴት ሳታውቅ እንዲህ በፍጥነት እንድትሄድ ይደረጋል?" በሚል ከባቤቱ ጋር ሁሉ ሊያጣሉኝ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ "ጉዳዩን የምታውቀው አንተ ስለሆንክ ፣በአንድ ሰዓት ውስጥ ለመሄድ ተዘጋጅ፤ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ተዘጋጅቶልሃል" ነው የተባልኩት፡፡ በዛ ወቅት የወ/ሮ ውባንቺ (የመንግስቱ ኃ/ማሪያም ሚስት) ወንድም የሆነ ሻምበል ታዬ ተሰማ የሚባል የኢሰፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የፓርቲ ፀሐፊ የሆነ ሰው ነበር፤ "የፋንታ በላይ ወንድም ነህ ተብለህ ነው እስከዛሬ ድረስ እግድ የተደረገብህ፡፡ ወንድም አለመሆንህን እኔ አውቃለሁ፤ በዚህ አጋጣሚ ለጓድ መንግስቱ ንገራቸው" ብሎ ምስጢሩን ያጫወተኝ እሱ ነው፡፡ ያኔ እኔም ዕድሉን ላለማባከን ትንሽ መጠጧን ወሰድሰድ አድርጌ ስለነበር በድፍረት ሀቁን አሳውቂያቸዋለሁ፡፡

**ግዮን፡- እስኪ ከሊ/መንበር መንግስቱ ጋር የነበራችሁ ውይይት ምን ይመስል እንደነበር ወደ ኂላ መለስ ብለው ያጫውቱን?**

ኢ/ር አበበ፡- በሰዓቱ እሳቸው በጨዋታ መሀል "በሰላም እንቅልፍ ተኝቼ አደርኩ" ብለው ሲናገሩ፤ "ምን ኢትዮጵያም ቢሆን እኮ መተኛት ይችሉ ነበር፤ የሆነ ያልሆነ ወሬ እየሰሙ ነው እርስዎ እንቅልፍ የሚያጡት እንጂ፣ አይሰርቁ፣ አይዘርፉ እርስዎ ምን ችግር ነበረብዎት? የሰው ወሬ ሰምተው ያልሆነ ዕርምጃ ስለሚወስዱ ነው ችግር የሚፈጠረው" ብዬ ስለፈልፍ፤ ጓድ መንግስቱ "እስኪ ያልሆነና በሰው ወሬ የወሰድኩት ዕርምጃ ምንድን ነው?" ብለው ጥያቄ አቀረቡልኝ፡፡ "አሁን ለምሳሌ እኔ የፋንታ በላይ ወንድም ተብዬ ብዙ ነገር ደርሶብኛል" ስላቸው "ታዲያ ወንድምህ አይደለም እንዴ?" ብለው በግርምታ ጠየቁኝ፣ ያኔ ተስፋዬ ዲንቃ ነበር በቦታው፡፡ እርሱም "እንዴ ወንድምህ ነው አሉ?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡

"ፋንታ በላይ ወንድሜ አይደለም፡፡ የእኔ እናት በ1976 ዓ.ም የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ ስራ አስኪያጅ ሆኜ ነው የሞተችው፡፡ መላኩ ተፈራ ባለበት ሀገር አልቀብርም ብላ፣ እዚህ አዲስ አበባ አስታምሜያት ደብረሊባኖስ ገዳም ነው የቀበርኳት፡፡ ታናሽ ወንድሜን የገደለው መላኩ ነው ስለተባለ ጎንደር እንዳንቀብራት ተናዛ ነበር፡፡ እናቴ በሞተችበት ወቅት ጓድ ተስፋዬ ዲንቃ ደብረሊባኖስ ሄዶ ቀብሯል፡፡ የእርስዎ ረዳቶች የነበሩ ሁሉ ቀብር ተገኝተዋል፡፡ የጄነራል ፋንታ በላይ እናት ግን አሁንም ጎንደር በህይወት አሉ፤ እንዴት ወንድሜ ይሆናል?" አልኳቸው፡፡ በጣም ገረማቸው፤ በጣምም አዘኑ፡፡ ለሆነው ነገርም ይቅርታ ጠየቁኝ፡፡ በመሪ ደረጃ ይቅርታ መጠየቅ ቀላል አይደለም፡፡ ከዛ በኂላ ኮ/ል ነሲቡ ታዬ አፍ አልነበረውም፤ ስለ እኔ ያልሆነ ነገር እንደተናገረ በድንጋጤው አወኩ፡፡ በዛ መልክ ነው ነገሮች የተለወጡትና ሀቁ ገሃድ ሊወጣ የቻለው፡፡

**ግዮን፡- ቀደም ሲል "ደጀን" በሚል ስያሜ ያቋቋማችሁት ድርጅትና ሕወሓት መራሹ መንግስት "ሜቴክ" ብለው አሁን ስላመጡት አስገራሚውም፣ አሳፋሪውም ተቋም አንዳንድ ነጥቦችን ቢገልፁልን?**

ኢ/ር አበበ፡- እኔ እስከማውቀው ድረስ አንድ ብር የማይበላበት፣ ንፁህ ስራ የሚሰራበት፣ ለሀገር የሚሰራበት መ/ቤት ቢኖር ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ወይም መከላከያ ኢንዱስትሪ ኮሚሽን ነበር፡፡ ይህ ተቋም በጣም ጨዋ ሰዎች የተሰባሰቡበት ነበር፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፡፡ በ1992 ዓ.ም ነው እኔ ከእዛ የለቀቅሁት፡፡ አንድ ፍጡርዘአብ አስገዶም የሚባል ኃላፊ አላሉት፣ ምን አላሉት ዝም ብለው አምጥተው አስቀመጡ፡፡ በዛ ወቅት "ደጀን" የሚባል ብራንች ተቋቁሞ ነበር፤ በነገራችን ላይ ደጀንን ነው ወደ ሜቴክ የቀየሩት፡፡

ሜቴክ እኮ መከላከያ ኢንዱስትሪ ኮሚሽን አይደለም፤ መከላከያ ኢንዱትሪ ኮሚሽን ሰፊ ነው፡፡ ከዛ ውስጥ አንዱ ዩኒት ነው ሜቴክ፣ ግን አንበሳ አደረጉት፣ የሀገሪቱን ሀብት ያለ ተቀናቃኝ ለመዋጥ እንዲያመቻቸው፡፡ የሚያሳዝነው ይሄ ነው፤ ደጀን በመከላከያ ስር ይሁን ተባለ ከእኛ ቁጥጥር እንዲወጣ፡፡ መጀመሪያ በእኛ ስር ነበር፡፡ ይሄን መሰሉ እንቅስቃሴ እኔ ስራ ላይ እያለሁ ነው የተጀመረው፡፡ በኂላ በመከለከያ ስር እንዲሆን መደረጉ ብቻ አይደለም "የመንግስሰት በጀት እየተመደበለት፣ በመከላከያ ስር የሚተዳደር ስለሆነ ኦዲት እንዳይደረግ!" የሚል ውሳኔ አስወሰኑ፡፡ ያኔ በጣም ይገርመኝ ነበር፤ በዛ ሁኔታ ለመስራት ፍቃደኛ የሚሆን ሰው የለም፡፡

ሜቴክ እነ ጋፋትን፣ ሆርማትን አይጨምርም፡፡መከላከያ ኢንዱስትሪ ግን ሜክሲኮ አደባባይ ያለው አማቱፋ የሚባለውን ጥይት ፋብሪካ፣ ብረታ ብረት ኮርፖሬሽንን ሁሉ ጠቅልሎ የያዘ ነበር፤ የእኛ ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮሚሽን፡፡ እነዚህን ሁሉ ባልጠቀለለ መልኩ "ደጀን" ወደ "ሜቴክ" ተቀይሮ አንዷ ድርጅት አንበሳ ሆና ወጥታ፤ ከሌሎቹ ሰላሳና አርባ እጥፍ አድጎ፣ የእዚህ የብልሹ አሰራርና የሌብነት ምንጭ፣ የዘራፊዎች መናኸሪያ እንዲሆን የተደረገው በእዚህ መልክ ነው፡፡

**ግዮን፡- ደርግ ከስልጣን ከተናበተ በኂላ እርስዎ በኢህአዴግ ዘመን እስከ 1992 ዓ.ም ድረስ በመከላከያ ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ውስጥ**

ቀሪውን በገጽ 22 ይመልከቱ



“እንግዲህ የቱን ከየቱ ልበልሽ? በክብት ስም በእንጨት ስም የሚጠራ አክቲቪስት ሞልቷል። እኔ ጋዜጠኞችም ኢንቨስትጌት እንድታደርጉ የምፈልገው ይህን ጉዳይ ነው። ከዚያ ይሄ አጀንዳ ተገፍቶ መጣና ከጦዘ በኋላ ጃዋር ምናለ ... እንደዚህ ከሆነ በእርግጫም፣ በጡጫም በዱላም በሜንጫም ዝግጁ ነን ወደሚል ሀሳብ ሄደ። እሱ ‹‹ እንዲህ ከሆነማ ›› ብሎ ነው የተነሳው። ይሄ ማለት መጀመሪያ አጀንዳውን እሱ አላነሳውም ማለት ነው። ከዚያ እስክንድር ነጋም እንደዚህ ከሆነ በምርጫ ካርድ በድምፃችን እንቀጣለን አለ። ማነው ይሄን አጀንዳ ያለ ጊዜው የገፋብን የሚለው ጥያቄ ሆነ። ያለ ጊዜው ስልሽ ባለፈው ውይይታችን እንደ ወልቃይት፣ እንደ ራያ ኮንሶና ሌሎች የውጥረት መነሻ የሆኑትን አሁን ላይ ላናናሳ ተስማምተን ነበር”

**አቶ የሺዋስ አሰፋ (ሸገር ታይምስ መጽሔት መጋቢት 2011 ዓ.ም)**



“ተመልከት በየመንደሩ ስንት ከነአቅማቸው የተደበቁ ልጆች አሉ፤ መጫወት እየቻሉ እድሉን ያላገኙ። እኛምኮ እድለኛ ሆነን እንጂ ታች ካሉት ልጆች በልጠንም አይደለም፤ በጣም ብዙ ታለንት ያላቸው ልጆች አሉ.. የሀገራችንን ኳስ ጥግ የሚያደርሱ ልጆች በሩ ተዘግቶባቸዋል... እንዴትስ ይደጉ... ለሌላ ዜጋ እምነት ተሰጥቶ የሀገር ልጅ እየተረሳ ለውጥ የለም። ከወጣት ቡድን አደገ ይባላል.... ስንት ክለቦች ናቸው ይህን እድል የሰጡት...? ስንቱስ አለፈ .....? አደጉ ከተባሉትስ ፕሪሚየር ሊግ ገብተው የሚጫወቱ ስንት ናቸው፤ በቃ እውነቱ ይሄ ነው ከየትኛውም ሊግና ሀገር ይምጡ ኢትዮጵያ ውስጥ የመጡት ስለማይችሉ ብቻ ነው”

**አህመድ ረሺድ (ሀትሪክ ጋዜጣ ሚያዚያ 2 ቀን 2011 ዓ.ም)**



“ሕገ መንግስቱ እስካልተሻሻለ ድረስ የማንነት ጥያቄዎች መቋጫ አይኖራቸውም። አንቀፅ 39 ማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መገንጠል ይችላል ይላል። ስለዚህ እራስን በራስ ማስተዳደር ትንሹ መብት ሲሆን የሚያሳዝነው ግን ቅድሚያ የሚሰጠው ለመገንጠል መሆኑ ነው። ይህ ማለት ሕገ መንግስቱ ለመብት ሳይሆን ቅድሚያ የሰጠው ለመገንጠል ነው። ስለዚህ አንቀፅ 39 ለመብት ቅድሚያ የሚሰጥ ሆኖ መስተካከል ወይም መሻሻል አለበት። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ችግሩ ይፈታል የሚል እምነት የለኝም።

**ሊሳይ መንግስቴ (ዶ/ር) (አዲስ ማለዳ ጋዜጣ መጋቢት 28 ቀን 2011 ዓ.ም)**



“የግብር ከፋዮቻችንን ፋይል ጥራት በተመለከተ በሃርድ ኮፒ እና ሲስተም ፋይል የማመሳከር ስራ እየተሰራ ነው። እንደገና እየመዘገብን እያጠራን ነው፡ ፡ የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ብዙም ቅሬታ የለብንም። ለዚህ ስራ ስንጀምር ለሰራተኞቻችን ስለሚሰሩት ስራ እና ስለደንበኛ አያያዝ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረጋችን ብዙ ረድቶናል። ይህን ስንል ምንም ቅሬታ አልቀረበብንም እያልን አይደለም። በተለይ ሥራ በምንጀምርበት ወቅት ከግብዓት አለመሟላት ጋር በተያያዘ አገልግሎት አሰጣጣችን መንተት ታይቶበታል”

**ወ/ት ብርቱካን ግርማ (ገቢያችን ህልውናችን ጋዜጣ የካቲት 2011)**



“ሌላው ጋር ያለ፤ እኛ ጋር የሌለ ሌላው ነገር በፀጥታና ደኅንነት ኃይል ትብብር መንግሥትን በአመጽ እገለብጣለሁ ብሎ ማሰብ በጣም ከባድ ነገር ነው። እኛ ያለን ነገር ኦሮሚያ ውስጥ ያለው የፖለቲካ ሀይል ሰዎቹን አንቀ እንደዲይዝ ማድረግ መቻል ነው። ኢሕአዴግ አንድ ባህሪ አለው በማዕከል ነው ውሳኔዎቹን የሚወስነው፤ ይህንን ውሳኔ እንኳ እንዲዘገይ ማስደረግ ለአመፅ ሀይል ትሰጠዋለህ ማለት ነው፤ ከነን መቆም ማለት ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ይሄ በእኛ እምነትና ሂሳባዊ ስሌት ግልፅ ነበር። ወደ አመፅ ስንመጣ በተግባር ተሳትፎ ነበረን። ውጪ ሆነው አመፁን የሚመሩትም ጓደኞቻችን ነበሩ፡ እኔ በተግባር እነሱንም ለመገምገም ሞክሬያለሁ።

**ዶ/ር ደረጀ ገረፋ ቱሉ (ቢሌ ታይምስ ጋዜጣ መጋቢት 28 ቀን 2011 ዓ.ም)**



“ለአምስት ዓመታት የመለዋወጫ ግዥ ሳይፈፀም ቆይቷል። በለስም ጊዜም ሌሎቹም መለዋወጫ ሳያገኙ ቆይተዋል። የማመንጫ ጣቢያዎቹ አንዴ ከተሰሩ በኋላ ዞር ብሎ የማየት ችግር ነበር። በአሁኑ ወቅት የመለዋወጫ ቀጥተኛ ግዥ ለመፈፀም የሚያስችለንን ስምምነት ግድቦችን በመገንባት ከተሳተፉትና ኃይል ማመንጫዎቹን ከተከሉ መለዋወጫ አቅራቢዎች ጋር ስምምነት በማድረግ፣ በቀጥታ መለዋወጫዎቹን ማግኘት የምንችልበት ዕድል ይኖራል።”

**አብርሃም በላይ (ዶ/ር) (ሪፖርተር ጋዜጣ መጋቢት 29 ቀን 2011)**

# እኛነት

አንድ አካል እያለን . . .

እኛ ሁለት ነን።

በእርግጥ!. . .

ነውር የለብትም አንዱ አንዱን ባይመስል፤

ሐሳብ ቢከፋፈል ተግባር ቢሆን ለቅል።

ግን አንድ አካል ሆኖ ሁለት ማንነት፤

ውሣኔ ወይ ሀሳብ የተለያዩበት፤

መደብም የለውም እንዲህ ነው የሚሰኝ፤

አንዱ ከወዲያ ጫፍ አንዱ ከዚህ ሲገኝ።

አዎን ወዳጆቹ! እኛ እንዲህ ሆነናል፤

ሁለት የምንሆን ተውጠን ባንድ አካል!!

(አደፍርስ - ዘኬላ መ.ሽ.ት)

## ፍቅር ማለት

-እሱን እሱን እያሰብሽ ከእንቅልፍሽ ስትነቂ።

-ልብሽ ሲጠፋብሽ . . . በምትኩ የሠረቀሽን ሰው ግን አጠገብሽ ስታገኚው።

-ከሚዋሽሽ እያንዳንዱ ነገር ጀርባ ያለውን እውነት ስትረጂ።

-ስልክሽ በጮኸ ቁጥር ልብሽ ስንጥቅ ሲል።

-ስታይው ለራስሽ “እውድሃለሁ!” ብለሽ ስታጉተመትሚ።

-ከሠዎች መካከል ስታይው አይኖችሽ በደስታ ሲያበሩ።

(ምንጭ፡- ወርቃማ የፍቅር ጥቅሶችና አባባሎች ቁ.2)

## ይህን ያውቁ ኖራል?

-የባንዲራ ወይም የሠንደቅ አላማ ሣይንሳዊ ጥናት ቬክሲሎሎጂ ይባላል።

-እስከ 1889 ዓ.ም ድረስ የአለም ብቸኛ የአልማዝ ማዕድን አቅራቢ አገር ህንድ ነበረች።

-አንድ የግብፅ ፒራሚድ ያረፈበት ሥፍራ ሁለት ኢንተርናሽናል የእግር ኳስ ሜዳ ያህል ስፋት አለው።

-የመጀመሪያውን ይፋዊ የቀን መቁጠሪያ ሠነድ የሠራው ጁልየስ ቄሳር ሲሆን ዘመኑም የዛሬ 2040 ዓመት ገደማ ነበር።

-ወንድና ሴት የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚያደርጉበት ወቅት ከሁለቱ የሚወጣው የሙቀት መጠን አምስት ሲ.ሲ ውሃን በሚገባ ያፈላል።

(ምንጭ፡- የዕውቀት ማህደር ቅፅ 1)

## ነፎቢያ አይነቶቹ ጥቂቶቹ

መብረቅ መፍራት - ኃይሮ ፎቢያ

ነጭ ቀለም መፍራት - ሊኮ ፎቢያ

ደን መፍራት - ሀይሎ ፎቢያ

ውሃን መፍራት - ሀይድሮ ፎቢያ

ዕንቅልፍን መፍራት - ሶምኒ ፎቢያ

እርግዝናን መፍራት - ቶኮ ፎቢያ

ፍቅርን መፍራት - ራሴሮ ፎቢያ

ስጋን መፍራት - ካርኖ ፎቢያ

ሠይጣንን መፍራት - ዴሞ ፎቢያ

መጠጥ መፍራት - ዲፕስ ፎቢያ

# እስክንድር የጠ/ሚ/ር ዐቢይን ግብዣ ሰርዞ፣ ከታከለ ኡማ ጋር ለምን ተገናኙ?



*በአዲስ አበባ ጉዳይ የሚንቀሳቀስ የባለ አደራ ም/ቤት እየመሰረተ እንዳለ የሚናገረው ጋዜጠኛና አክቲቪስት እስክንድር ነጋ በያዝነው ሳምንት መጀመሪያ ከም/ከንቲባ ታከለ ኡማ ጋር ተገናኝተው ተወያይተዋል:: ጉዳዩን አስመልክተን እስክንድርን አነጋግረን ያገኘነውን ምላሽ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።*

**ግዮን፡- ሰኞ መጋቢት 30 ቀን 2011 ዓ.ም በአዲስ አባባ ጉዳይ ከም/ከንቲባ ታከለ ኡማ ጋር ተገናኝታችሁ በልዩነቶቻችሁ ዙሪያ ተነጋግራችኋል። አስቀድሞ የመወያየቱን ዕድል የፈጠረው ማነው?**

እስክንድር፡- ከኢ/ር ታከለ ኡማ ጋር ያደረግነው ውይይት እውን የሆነው በሁለተኛው ቀጠሮ ነው። ከአንድ ሳምንት በፊት ከእሳቸው ጋር ለመወያየት ቀጠሮ ነበረን፣ ሆኖም ቅዳሜ ዕለት በራስ ሆቴል ልናደርግ ዕቅድ ተይዞለት የነበረው ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰረዝብን፣ ከዚህ በመነሳት እኛም የመጀመሪያውን ቀጠሮ ሰርዘነዋል።

“ጋዜጣዊ መግለጫ የመስጠት መብታችን መከበር አለበት” የሚል አቋም በመውሰዳችን ከከንቲባ ታከለ ኡማ ጋር ልናደርግ የነበረውን የመጀመሪያውን ቀጠሮ ከሰረዝን በኋላ፣ እሮብ እለት ግን ጋዜጣዊ መግለጫውን እንድንሰጥ ተደረገ፤ በዚሁ ቀን ከሰዓት በኋላ ስልክ ተደውሎ ከንቲባው ለመነጋገር ቀጠሮ መያዝ እንደሚፈልጉ ተገለፀልን። በእዛ መሰረት ለሰኞ መጋቢት 30 ቀን ቀጠሮ ይዘን ተገናኝተናል። መሀል ላይ ሆነው ይሄ ውይይት እንዲሳካ መስተዳድሩ ውስጥ ያለ አንድ የቢሮ ኃላፊ፣ አክቲቪስት ይድነቃቸው ከበደ (የቀድሞ የሰማያዊ ፓርቲ አመራር አባል) እንደ ድልድይ ሆነው ግንኙነቱን አመቻችተዋል።

**ግዮን፡- በቀጠሮው መሰረት ከከንቲባው ጋር ከተገናኛችሁ በኋላ በምን በምን ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተነጋገራችሁ?**

እስክንድር፡- ከተገናኘን በኋላ ውይይቱ የተጀመረው በጣም በቀና መንፈስ ነው። የሀገሪቷን ወቅታዊ ሁኔታ ቃኝተን፣ አሁን ያለው የሽግግር ሂደት መሳካት እንዳለበት፣ የሀሳብ ልዩነቶች ቢኖሩም እነሱ በሰላማዊ መንገድ መፈታት እንዳለባቸው ተወያይተን ተስማምተናል። ይሄንን እንደ መሰረት ነው ያስቀመጥነው። እኔ ወደ ስብሰባው አራት አጀንዳዎችን ይዤ ነበር የሄድኩት። የመጀመሪያው በባልደራሱ ስብሰባ ህዝቡ የወሰደውን አቋም በፅሁፍ አዘጋጅቼ ስለነበር እሱን ለመስጠት፣ በሁለተኛ ደረጃ ህዝባዊ ስብሰባዎችን መከልከላችን አስመልክቶ እንድንነጋገር፣ ሶስተኛ በፖሊስ አመላመልና ምደባ ዙሪያ (በአዲስ አበባ) አሁን ህብረተሰቡ እያነሳቸው ያሉ ጥያቄዎች፣ በአራተኛነት በአዲስ አበባ መስተዳድር ውስጥ በተለይ ቁልፍ በሆኑ የኃላፊነት ዕርከኖች (ቦታዎች) ላይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተደረጉ ያሉት ምደባዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ትልቅ ጥያቄ እያነሱ ስለመሆኑ እንድንነጋገር ነበር ፍላጎቴ።

**ግዮን፡- ከእሳቸው ምን ምላሽ አገኘህ?**

እስክንድር፡- በባልደራስ ህዝብ ያወጣውን የአቋም መግለጫ በፅሁፍ የያዘውን ወረቀት እንዲቀበሉኝ ስጠይቃቸው ከንቲባው ያንን የአቋም መግለጫ ለመቀበል ፍቃደኛ እንዳልሆኑ ገለፀውልኛል። እንዲህ ሲሉኝ እኔ ፈፅሞ ምንም ነገር አላልኳቸውም፤ ያንን መልስ በግል እየመለሱልኝ ሳይሆን፣ እንደ መስተዳድርና ኦዴፓ አባልነታቸው ቀደም ብለው ከጓደኞቻቸው ጋር የተነጋገሩበትና የማልቀይረው አቋም ስለሆነ ምላሻቸውን ተቀብያለሁ። የህዝቡን ጥያቄ እንዳልተቀበሉና ያለውን ሁኔታ ለህዝብ እንደምንገልፅ ግን አሳውቄያቸዋለሁ።

በቀጣይነት ያነሳሁት ሕዝባዊ ስብሰባዎችን የሚመለከተው አጀንዳ ላይ ግን ተስማምተናል። “ህዝባዊ ስብሰባዎች መከልከል የለባችሁም፣ መብታችሁ ነው” በሚል እዛው በተቀመጥኩበት የከተማዋ የፀጥታ ኃላፊ ለኮሚሽነሩ ደውለው፣ ሕዝባዊ ስብሰባዎች እንድናካሂድና አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግልን መመሪያ ሰጥተዋቸዋል። እኔም ኮሚሽነሩን በስልክ እንዳገኝና በጉዳዩ ላይ እንድንነጋገር አድርገዋል። ስለዚህ ሁለተኛው አጀንዳ ላይ ከከንቲባው ጋር ፍፁም ስምምነት ነበረን። በሶስተኛና አራተኛነት የያዝኳቸውን አጀንዳዎች ግን ከዛ በኋላ አልገፋሁባቸውም።

**ግዮን፡- ለምን?**

እስክንድር፡- በመጀመሪያው አጀንዳ “የአቋም መግለጫውን አልቀበልም” ስላሉ ሶስተኛና አራተኛው አጀንዳ ላይ የምንነጋገርበት መንገድ የለምና በዛው ስብሰባውን ቋጭተነዋል። ስንቋጨው ግን ልዩነቶች እንዳሉ ሁለታችንም ተማምነናል፤ በግል ብቻ ሳይሆን እንደ ድርጅት አቋም፣ እንደ ኦዴፓ አባልነታቸው አዲስ አበባ ላይ ድርጅቱ የያዘው አቋም፣ እንዲሁም እኛ ስለ አዲስ አበባ የያዝነው አቋም መካከል ግልፅ የሆነ ልዩነት እንዳለ ተማምነናል። ይሄ ልዩነት በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ እንጂ ለጠላትነት በር እንዳይከፍት፣ የግጭትና የመለያየት ምክንያት መሆን እንደሌለበትም ተግባብተናል። ኢትዮጵያዊነትና ሰላም ያስተሳስረናል፣ ዲሞክራሲ ያስተሳስረናል በሚለው ላይ ተስማምተናል።

**ግዮን፡- ም/ከንቲባ ታከለ ኡማ የሕዝቡን የአቋም መግለጫ ካልተቀበሉ፣ አሁንም የአዲስ አበባ ፈላጭ ቆራጭ ነኝ ብለው ድርድሩንም ሆነ ሁሉን ነገር በበላይነት ከያዙት በቀጣይ የሚኖረው ሂደት፣ ካለፈው ምን ልዩነት ይኖረዋል?**

እስክንድር፡- ኦዴፓ በአዲስ አበባ ላይ የኦሮሚያን ባለቤትነት ለማረጋገጥ እንሰራለን ሲል ነው የነበረው። ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ባለፈው ሳምንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ልዩ ጥቅም የሚለውን በህገ - መንግስቱ ውስጥ የተቀመጠውን ሐረግ የኦሮሞ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊደግፈው ይገባልም ብለዋል። እኛ ደግሞ በተቃራኒው “ልዩ ጥቅም” የሚለውን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የኦሮሞን ህዝብ ጨምሮ ማለት ነው ሊቀበለው የማይገባ ሀሳብ ነው የሚል አቋም ይዘናል።

የሀሳብ ልዩነት መብት ነው፣ የጠላትነት ምክንያት አይደለም። “ይሄኛው መስመር ትክክል ነው፣ ይሄኛው መስመር ደግሞ የተሳሳተ ነው” ብሎ የሚፈታልን ደግሞ በነፃ ምርጫ ሕዝብ ነው። ስለዚህ ቀጣዩ ምርጫ እስኪደርስ ድረስ ያንን መንገድ አብረን እያስተካከልን እንቆያለን ማለት ነው። በነገራችን ላይ ከንቲባ ታከለ ኡማ በባልደራሱ የሕዝብ ስብሰባ የተላለፈውን የአቋም መግለጫ አሁን አልቀበልም አሉ ማለት ወደ ፊትም አይቀበሉትም ማለት አይደለም። በቀጣይ ሊቀበሉ ወይም ሀሳባቸውን ሊቀይሩ የሚችሉበት ዕድል አለ። የህዝብን ጥያቄ መቀበል እንዳለባቸው በመግለፅ ደግመን ደጋግመን በራቸውን እናንኳኳለን ኃላፊነትም እንዳለባቸው እንገልፃለን።

**ግዮን፡- ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ በአዲስ አበባ ጉዳይ ላይ መነጋገር እንደሚፈልጉ እየገለፁልህ፣ የእሳቸውን ጥያቄ ገፍተህ እንዴት የከንቲባውን ግብዣ ተቀበልክ?**

እስክንድር፡- ይሄ ጥሩ ጥያቄ ነው። የዛሬ አስራ አምስት ቀን ቅዳሜ ራስ ሆቴል ጋዜጣዊ መግለጫ ስንከለከል ከሰዓት በኋላ ከጠ/ሚ/ሩ ጋር ቀጠሮ ነበረን። ከሁለት ቀን በኋላ ደግሞ ከኢ/ር ታከለ ኡማ ጋር ቀጠሮ ነበረን። ግን ጋዜጣዊ መግለጫውን እንዳንሰጥ ቅዳሜ ጠዋት ስንከለከል፣ አስቸኳይ ስብሰባ አድርገን “ዴሞክራሲያዊ መብታችን በተጣሰበት ሁኔታ ግንኙነት ሊኖር አይገባም፣ መጀመሪያ የሰዎች መብት መከበር አለበት” የሚል አቋም በመያዛችን ከሰዓት በኋላ ከጠ/ሚሩ ጋር የነበረንን ቀጠሮ ሰርዘን፣ ወደ እሳቸው ሳንሄድ ቀርተናል።

ከዛ በኋላ ጋዜጣዊ መግለጫ የመስጠት መብታችን ስለተከበረ ነው በሁለተኛው ቀጠሮ ከንቲባውን ያገኘነው እንጂ የእሳቸውንም የመጀመሪያ ቀጠሮ ሰርዘናል። ጠ/ሚሩ ብዙ ስራ ስለሚበዛባቸውና በቂ ጊዜ ስለሌላቸው እስካሁን ሌላ ቀጠሮ አልቀረበልንም። ግን እሳቸው ጋር ከዚህ በኋላ ፕሮግራም ከተያዘልን በጣም በደስታ ተቀብለን እናገኛቸዋለን፤ በጉዳዩ ላይ ያለውንም የህዝብ ዕይታ እናስረዳቸዋለን። እሱ ለኛ ትልቅ ዕድል ነው የሚሆነው።

**ግዮን፡- እናመሰግናለን።**



# የረቂቅ አዋጁ ነገር

በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

"መንግሥት የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃ መቆጣጠሪያ ረቂቅ አዋጅ ያዘጋጀው የሕዝቡን ሰላም፣ ደኅንነቱንና በፍቅር አብሮ የመኖር እሴቶቹን ለመጠበቅ ነው፡፡" በማለት መጠጥ ባመጣው ሞቅታ ጮኽ ብዬ እየተናገርኩ ነው፤ "ሰላማዊ ዜጎች በምንም መልኩ ረቂቅ አዋጁን በሥጋት ማየት የለባቸውም፡፡ ..."

ስጠጣ ፊኛዬ አይችልም አይደል? መተርተሬን ቀጠልኩ፤ "መንግሥት እንደ ሁልጊዜው የዜጎቹን ሰላም፣ መብትና ነፃነት ለመጠበቅ በርትቶ ይሠራል! ስለዚህ..." ብዬ በሞራል ዲስኩሬን ልቀጥል ስል ፊት ለፊቴ የተቀመጠ አንድ ጠጪ ወደኔ እየጠቆመ፤

"በሕግ አምላክ ይኼን አፍራሽ ኃይል ዝም አሰኙልኝ! ...በሕግ አምላክ!" ብሎ ጮኸ፡፡

"ለምን?" አሉት ሌሎች ጠጪዎች ግራ ተጋብተው፤ "እኮ ለምን?"

"በመንግሥት ላይ ሐሰተኛ መረጃ እያሰራጨ ነው!"

"ምን!?"

"መንግሥትን ያለስሙ ስም በመስጠት ሐሰተኛ መረጃ እያሰራጨ ነው!"

...ዋዘኛ በዛ እኮ ጎበዝ፤ (ለነገሩ ያቀበጠን ራሱ ረቂቅ አዋጁን ያዘጋጁት ወገኖች ናቸው፡፡ ረቂቅ አዋጁ ላይ፣ "ንግግሩ ቀልድ፣ ስላቅ ወይም ልብወለድ መሆኑ ግልፅ ከሆነ በወንጀል አያስጠይቅም " የምትል ሐረግ ማን አስገቡ አላቸው? ...ይኼኔ አንዳንዶች ረቂቅ አዋጁን ያሰናዳው ኮሚቴ ውስጥ እኔ ያለኹበት ይመስላቸዋል፡፡)

አሁን ላይ ሆኜ፣ በባዶ ሆዴ ሳስበው የዚኽ ዋዘኛ ሰው ንግግር ልክ ሳይሆን አይቀርም፡፡ አዎ! የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃን ማሰራጨት ወንጀል ከሆነ፣ መንግሥትን ከሠራው በላይ ማሞገስ፤ ለውጡን ከሚገባው በላይ አግንኖ መተረክ እና ማሳየት፣ ሐሰተኛ መረጃ ማስተላለፍ ነውና እኔው ራሴ በወንጀል ልጠየቅ ይገባል፡፡

(...እያንዳንድሽ ግን ጉድሽ ፈላ፤ "ስዩመ እግዚአብሔር፤ ከላይ የተላከ ነብይ፤ ሙሴ፣ አሮን፣ ሳኦል..." ወዘተ እያልሽ ሹማምንቱን የምትጠሪ ሁላ አወዳደቅሽ ሊከፋ ነው፡፡ ...እህ! ከዚህ በላይ ሐሰተኛ መረጃ የለማ፡፡ "ለቤተ መንግሥቱ ቅርብ የኾንኩ ባለጊዜ ነኝ" ብሎ እንደልብ መቀደድ በወንጀል ከመጠየቅ አያድንም፡፡ ...የምር እኔን ግን ምን ነካኝ? ከመንግሥት ካዝና ጥቂት ዳረጎት እንዳገኘ ሰው፤ ስካሬን መንግሥት ስፖንሰር ያደረገኝ ይመስል ምን አቅመደመደኝ!? "መንግሥት የዜጎቹን ሰላም፣ መብትና ነፃነት ለመጠበቅ በርትቶ ይሠራል!" ብዬ ምን አስወራኝ!? እንዲህ ያለስ ማኪሸት የት ነው የተማርኩት!? ...ሳሳዝን! ...ጎበዝ፤ ለመሆኑ በስካር መንፈስ ስለሚነገር ንግግር ረቂቅ አዋጁ የኾነ ነገር ብሎ ይኾን!? ...ማለትማ አለበት!)

...ለማንኛውም በዚች አጭር የመጠጥ ቤት ጨዋታ ምንድን ነው ማስተላለፍ የፈለግነው!? እንደሚከተለው እናብራራለን፡፡

በማኅበራዊ ድረ ገፅም ሆነ፤ በተለያዩ የብዙኃን መገናኛዎች ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጭ የጥላቻ ንግግር ከሚያስተላለፉ ወገኖች መካከል ጥቂት የማይባሉ የመንግሥት ሹመኞች እና ቀለብተኞች ይገኙበታል፡፡

ለምሳሌ አንዳንድ የፌዴራልና የክልል ባለሥልጣናትን፤ የመንግሥት የሚዲያ ባለሙያዎችን፤ "በተፎካካሪ ፓርቲም ሆነ በነፃነት ተሟጋች" ስም ራሱ መንግሥት ያቀረባቸውን ኃይሎችን ብንወስድ ተንኳሽ እና ለግጭት የሚያነሳሱ የጥላቻ ንግግሮችንና ሐሰተኛ መረጃዎችን ባገኙት መድረክ ሁሉ የሚያቀርቡበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም፡፡ (እስኪ ሹማምንቱ፣ መንግሥት አቅፎ ደግፎ ወደ አገር ቤት ያመጣቸውን ግለሰቦች የሚሰጧቸውን ቃለ ምልልሶችና ጋዜጣዊ መግለጫዎች ተመልከቱ፤ በግል የማኅበራዊ ገፆቻቸው የሚያስተላልፏቸውን መልዕክቶችንም አስተውሉ)

ስለዚህ መንግሥት "አፍራሽ ኃይሎች፤ ተላላኪዎች" እያለ ጣቱን ወደ ሌላ ከመቀሰሩ በፊት ውስጡን ይመርምር፤ ይፈትሽ፤ ከዚያ አደብ ያስገዛ፡፡ በራሱ በጀት የሚተዳደሩ የክልል መገናኛ ብዙኃን ምን ዓይነት መልዕክት እንደሚያስተላልፉ ይመልከት፡፡ (መንግሥት ሆይ፤ "ተንኮልን የሚፈቅድ ተባባሪ ነው" እንዲሉ አባቶች በቅድሚያ ወደ ራስኽ ሰዎች ተመልከት! ...ጉያኽ ሥር ያሉትን ተባዮች ካራገፍክ በኋላ፣ እኛን እግዚሃር የሰው መውደድ ሰጥቶን፣ ከአምስት ሺህ በላይ ወዳጆች ያፈራነውን ሰካራም ግለሰቦች ጠይቅ፡፡)

"ተባለ እንዴ" ቅፅል ስሙ ነው፡፡ ቀን ከሌሊት አልክሆል የሚጠጣ፣ በዚህ አመሉም በብዙዎች ዘንድ የሚታወቅ የመንደራችን ነዋሪ ነው፡፡ ያደግንበት ትህትና ይዞን፣ "ጠጪ ነው" ብለን ብቻ እንለፈው እንጂ የእርሱ አጠጣጥ እጅግ በጣም የተጋነነ ነው፤ "እንደ ጉድ ይጋተዋል" ብለው የሚገልፁት ዓይነት፡፡

"ጋሽ ተባለ እንዴ!"

"አቤት!"

"ለምን ይኼን ያኽል ትጠጣለህ!?"

"ምን አገባኽ? ባንተ ጉሮሮ አልጠጣኹ!" ይላል ልምከርህ ብሎ የሚመጣውን ሰው ሁሉ፡፡

"ጋሽ ተባለ እንዴ" በመጠጥ ሱሰኝነቱ ምክንያት በጉልበት ሠራተኝነት ከተቀጠረበት የመንግሥት መስሪያ ቤት ተባርሯል፤ በመጠጥ ፍቅሩ ምክንያት ትዳሩን አጥቷል፤ በመጠጥ ወዳጅነቱ ምክንያት ሄደት መጣ በሚሉ ብዙ በሽታዎች እየተሰቃየ ነው፡፡

"ተባለ እንዴ" ሁልጊዜ አመሻሽ ላይ ታዲያ ንፋስ እንደሚያንገላታው ሸንበቆ ከወዲያ ወዲህ እየተወዛወዘ፣ ሞቅታ ያዝ ባደረገው አንደበት፣ እንዲህ እያንጎራጎረ ወደ መንደራችን ይዘልቃል፤

"ተባለ እንዴ ተባለ፤
ሰካራም ተባለ አዳሙ፤
የጠላት ወሬ እየሰሙ፤
ተባለ እንዴ! ተባለ፤
ሰካራም ተባለ አዳሙ፤
የፀረ ሰላም ወሬ እየሰሙ!
ተባለ እንዴ! ተባለ!"

...(አዳሙ የራሱ ስም ሲሆን ዜማው የተወሰደው፣ ከፀሐዬ ዮሐንስ "ተባለ እንዴ" ከሚለው ሙዚቃ ነው)

አንዳንዴ ያለ ልክ መስከር ባመጣው አቅም ማነስ፣ ትቦ ውስጥም ሆነ በየአጥሩ ጥግ ወድቆ የሚገኝበት ሁኔታም አለ፡፡ እዚያው ስርቻ ውስጥ ሆኖ ታዲያ ይኽቺው እንጉርጉሮ አትቀርም፡፡

"ሰካራም ተባለ አዳሙ፤
አፍራሽ ኃይሎችን እየሰሙ፤
ተባለ እንዴ! ተባለ"

(አዝናኙ ነገር፣ "አፍራሽ ኃይል"፤ "ፀረ ሰላም"፤ "ፀረ ምናምን" የመሳሰሉ ቃላትን መጠቀሙ ነው፡፡ እነዚኽን ቃላት ይዞ የሚመጣው አነስተኛ አበል ከሚያገኝባቸው ከወረዳ ስብሰባዎች ነው ብለን እንጠረጥራለን፡፡ ወትሮስ ወረዳ የኼደ ሌላ ምን ይዞ ሊመጣ ይችላል!?)

"ተባለ እንዴ ተባለ!"

አንደምታ፡- መንግሥት ኾይ ራስህ ባመጣኽው በሽታ ሌላውን አትውቀስ! ...ስላዳመጥከኝ አመሠግናለኹ!


## ማረሚያ እንደ መዝናኛ

ለውድ አንባቢያን በባለፈው ሣምንት ዕትማችን በገፅ ሁለት ላይ ባሰፈርነው ርዕሰ አንቀፅ፣ "መንግሥት በፍቅር እና በመተሳሰብ ለመኖር ያስቻሉንን ሴቶች ያስጠብቅልን!" ያልነው በስህተት ስለሆነ፣ "መንግሥት በፍቅር እና በመተሳሰብ ለመኖር ያስቻሉንን እሴቶች ያስጠብቅልን!" ተብሎ እንዲነበብ ከይቅርታ ጋር እንጠይቃለን፡፡

# “ዐቢይን ተጠያቂ አላደርገውም”

## “በዴሞክራሲ ራሱን አስተዳድሮ የማያውቅ ህዝብ ነው”

*ፕ/ር መሣይ ከበደ*



*እንግዳችን ፕ/ር መሣይ ከበደ ለረጅም አመታት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና መምህርና የዲፓርትመንት ኃላፊ በመሆን ያገለገሉ ሲሆን፤ በኢህአዴግ መንግስት ከተባረሩት 42 ምሁራንም አንዱ ናቸው። በደርግ ዘመነ መንግስትም በአዲስ አበባ መምህራን ማህበር በሊ/መንበርነት አገልግለዋል። በደርግ ታትሞ የነበረውን የማሌ (ማርክሲስት ሌኒኒስት) መዝገበ ቃላትም የፍልስፍናውን ዘርፍ መስራታቸው ይነገራል፡ ፡ ፕ/ር መሣይ በአገራቸው የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ በስፋት በመሳተፍም ይታወቃሉ። ለአገር ዕድገት ጠቃሚ ናቸው የሚሏቸውን ሀሳቦችም በፅሁፍ በማንሳት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል። በአሁኑ ሠዓት በአሜሪካ ኦሃዮ ግዛት ውስጥ በሚገኘው ዳይተን ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና መምህር ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ፡ ፡ ሦስት በጥናት ላይ የተመሰረቱ መፃህፍትንም አዘጋጅተዋል። ፕ/ር መሣይ ከበደን በአገራችን ወቅታዊና ቀደምት ጉዳዮች ላይ በሰፊው ከግዮን መጽሔት ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅ እንዲህ ባለ መልኩ አነጋግሮቸዋል። መልካም ንባብ!*

**ግዮን፡- ስለ ተማሪነት ዘመንዎ በማንሳት እንጀምር?**

ፕ/ር መሣይ፡- እኔ ያደግኩትም የተማርኩትም አዲስ አበባ ነው:: ሀይስኩልን በተመለከተ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በሊሴ ገ/ማርያም ት/ቤት ነው የተማርኩት:: የፈረንሳይ ተማሪ ነኝ:: የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከወሰድኩ በኂላ ወደ ፈረንሳይ አገር በስኮላርሺፕ ሄጄ ፍልስፍና ተማርኩ:: እስከ ፒኤችዲ ነው የተማርኩት:: ፒኤችዲዬን እንደጀመርኩ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ አብዮት መጣ፤ ንጉሱ ከስልጣን ወረዱ፤ ደርግ ወደ ስልጣን መጣ:: ነገሮች ሁሉ መለዋወጥ ጀመሩ፤ ቢሆንም ታሪክ ሲሰራ እንዳያመልጠኝ ብዬ በመጓጓት ትምህርቴን ቶሎ ጨርሼ ወደ ኢትዮጵያ ገባሁ:: ያኔ ወቅቱ ትንሽ አስቸጋሪ ነበር:: የቀይ ሽብር እንቅስቃሴም የተጀመረበት ጊዜ ነበር:: እንደመጣሁ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተቀጠርኩና የፍልስፍና ዲፓርትመንት አባል ሆኜ መስራት ጀመርኩ:: ከዚያም የዲፓርትመንቱ ሀላፊም ሆኜ ሠርቻለሁ::

በዚያን ግዜ የትምህርቱ ሥርዓት እየተለዋወጠ ነበር:: እኛ በብዛት ወደ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም አስተምህሮት ገባን፤ ነገሩ ኢትዮጵያ ተኮር ነው:: በዚህ የተነሳ ይህንኑ የሚያስተምሩ ወጣቶች ዲፓርትመንቱ መውሰድ ጀመረ:: ማለትም በፍልስፍና ሜጀር የሚያደርጉ:: ይህ የትምህርት ስርዓት ብዙ አመት ተካሄደ:: እንደገና ደግሞ ሁለተኛ ጊዜ ለውጥ መጣ::

**ግዮን፡- የተማሪዎች አብዮት ላይ ተሳትፎ አልነበረዎትም?**

ፕ/ር መሣይ፡- እኔ እዚህ ስደርስ ደርግ ስልጣን ይዞ፤ የቀይ ሽብር እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበርና የነበረው የተማሪው እንቅስቃሴም ተበታትኗል:: ከዚያ በኂላም ምንም ሊነሳ አልቻለም:: ስለዚህ የመጣሁት ትንሽ ነገሮች ካለፉ በኂላ ነበር::

**ግዮን፡- ጥያቄውን ያነሳሁት በውጭ የነበሩ ወጣቶችም በትግሉ ላይ ተሳትፎ ያደርጉ ነበር ስለሚባል ነው::**

ፕ/ር መሣይ፡- ይሄማ እርግጥ ነው፤ ብዙም የሚያስደነቅ ነገር አይደለም:: ምክንያቱም አውቃለሁ የሚልና የተማረ ሁሉ ወደ ማርክሲስት አስተሳሰብ የተጠጋበት ሁኔታ ነበር:: ስለዚህ በዚህ መንገድ አልጓዝም የሚሉት በጣም በጣም ጥቂቶች ናቸው:: ሁሉም አክራሪ ነበር፤ ሁሉም አጠቃላይ ለውጥ ኢትዮጵያ ውስጥ መምጣት አለበት የሚል.... ሌላም ሌላም ይባል ነበር:: በነበርኩበት ፈረንሣይ አገርም ስብሰባዎች ይካሄዱ ነበር:: እዚያ ውስጥ እሳተፋለሁ፤ በወቅቱ ደግሞ በፈረንሣይ የነበሩ ብዙዎች የመኢሶን ተከታዮች ነበሩ:: እኔም ከነሱ ጋር ሙሉ ለሙሉ ባንስማማም አብሮ የመስራት አጋጣሚው ነበረኝ:: እናም አብዮቱ ሳንጠብቀው ፈነዳ:: ከዚያ በኂላ ያ ሁሉ የተማሪ እንቅስቃሴ ወደ ፓርቲ መለወጥ ጀመረ:: እኔ ወደ አገር ቤት በመጣሁበት ወቅት ኢህአፓና መኢሶን ሀይለኛ ግጭት ውስጥ ነበሩ:: ደርግም ደግሞ አለ፣ ቀይሽብርም እንደዚያው ተፋፋመ:: በዚህ የተነሳ የተማሪው እንቅስቃሴ ተበታተነ:: በትንሹም ቢሆን መኢሶን ስራውን ቀጥሎ ነበር:: ሆኖም ብዙ አልቆየም፤ ከደርግ ጋር ቅራኔ ውስጥ በመግባቱ መኢሶንም ተሰደደ:: ከዚያ በኂላ የነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ሞቷል::

**ግዮን፡- በዚያን ወቅት ከፍተኛ ተሳትፎ አደርግበት ነበር የሚሉት ፓርቲ ነበር፤ ወይም እደግፈው ነበር የሚሉት?**

ፕ/ር መሣይ፡- ይሄ ታሪክ እንኳ ብዙ ነው:: ባይሆን ወደ መጨረሻው ላይ የኢሠፓ አባል ሆኜ ነበር:: በእርግጥ ቆይቼ ነው የገባሁት:: መጀመሪያ በመምህራን ማህበር ነው የገባሁት፤ የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር ሊ/መንበር ነበርኩ፤ ለተወሰነ ግዜም ቢሆን በቀበሌም ውስጥ በሊ/መንበርነት ሠርቻለሁ:: ይሄ እንዳለ ነው ደርግ በወደቀበት ግዜ አካባቢ ►

የኢትዮጵያ ችግር ሁሌ ምንድነው? አንዱ በሚገዛበት ግዜ ያ ተገዢ የሆነው እውክላለሁ የሚለው አካል ስለ ዲሞክራሲ፣ ስለዕኩልነት ያወራል፤ ግን ደግሞ እሱ በተራው ስልጣን ላይ ሲመጣ እራሱ የገባውን ቃል በሙሉ ትቶ ወደ በላይነት ፍለጋ ያመራል። ስለዚህ የፈረቃ አገዛዝ ነው የሚያደርገው።ይህ ነው እንግዲህ የዲሞክራሲን አገዛዝ እንዳይመጣ የሚያደርገው

ሁሉን ነገር ትቼ ወደ አሜሪካ አገር በስኮላርሺፕ መጣሁ::

**ግዮን፡- ወደኋላ ልመልስዎት፤ ደርግ ከመውደቁ በፊት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምንድን ነበር የእርስዎ ሀላፊነት፤ ዲፓርትመንቱስ የተጀመረው በእርስዎ ጊዜ ነበር?**

ፕ/ር መሣይ፡- የፍልስፍና ትምህርት ዲፓርትመንት አስቀድሞም ነበረ፤ ፕ/ር ሳምነር የሚባል ብዙ አመት ያስተማረ ሠው ነበረ:: ሆኖም በአንድ ሠው ብቻ ስለነበረ የሚሠራው በጣም ውስን ነበር:: እኛ ከመጣን በኂላና ከመንግስት በመጣው ጥያቄ መሠረትም የዲግሪ ፕሮግራም እንዲጀመር ሆነ:: ከዚያ በኂላ እንግዲህ ዲፓርትመንቱ እያደገ መጣ:: ሌሎች አስተማሪዎችም ተቀጥረው እንሰራ ጀመር:: እኔ ደግሞ የዲፓርትመንቱ ሀላፊ ነበርኩ:: በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ወያኔ አዲስ አበባ እስኪደርስ እዚያው ነበርኩ:: ለመጀመሪያ ግዜ ምንም ችግር አልነበረም:: ሆኖም እኔ ወዲያው ነው ወደ አሜሪካ አገር የመጣሁት:: በስኮላርሺፕ አንድ አመት ቆየሁ:: ስመለስ ግን ነገሮች በጣም ተለዋውጠው ነው የጠበቁኝ::

በፊት ወያኔዎች ሲገቡ የነበረው ነፃነትና ሀሳብ ሁሉ በጭራሽ ሙሉ ለሙሉ ጠፍቷል:: ወዲያው እኔም ከ40ዎቹ ውስጥ ተባረሃል የሚል መልዕክት ደረሠኝ:: በዚህ ሁኔታ ነው ከዩኒቨርስቲው የወጣሁት:: ከዩኒቨርስቲ እንደወጣሁ በራሴ የፅሁፍ ስራ መፃፍ ጀምሬ ነበር:: ያንን መፅሐፍ ለመጨረስ ሞከርኩ፤ እዚያ እንዳለሁ እንደገና ስኮላርሺፕ አመልክቼ ወደ አሜሪካ አገር ተመለስኩ:: እናም ሀዋርድ ዩኒቨርስቲ አፍሪካ ዲፓርትመንት የሚባል አለ እዚያ ቆየሁ:: በቆይታዬ አሜሪካ አገር ባሉ ዩኒቨርስቲዎች ለማስተማርና ቦታ ለማግኘት ማመልከቻዎችን ማስገባት ጀመርኩ:: ያው ብዙ ጣጣ አለው፤ በመጨረሻ አሁን ያሁበት University of Dayton ጋር ተስማማን:: እነሱ ቀጠሩኝ:: ከዚያን ግዜ ጀምሮ እንግዲህ እዚሁ እያስተማርኩ ነው::

**ግዮን፡- ቀደም ብለው ከዩኒቨርስቲ ከተባረርን በኂላ በግሌ በፅሁፍ መፃፍ ጀምሬ ነበር ብለዋል መፅሀፉ ስለምን ነበር የሚያትተው?**


ፕ/ር መሣይ ፡- ስለኢትዮጵያ ነው :: በመሠረቱ ሦስት መፅሀፍ ነው የፃፍኩት ::Survival and Modernization: Ethiopia's Enigmatic Present የሚል፤እሱን ነበር በዚያን ግዜ የምሠራው:: እዚህ ከመጣሁ በኂላ የፃፍኩት ደግሞ Radicalism and Cultural Dislocation in Ethiopia: 1960-1974 የሚል ሲሆን የሚያተኩረውም በተማሪዎች እንቅስቃሴ ላይ ነው:: ለምን ተማሪ አከረረ፤ ጭራሽ ምንም አይነት አክራሪ ያልሆነ ለውጥ አልቀበልም ብሎ ይህንን ሁሉ ችግር እንዴት አመጣ? ይህስ ምን አይነት ለውጥ ነው? በሚል የተዘጋጀ በጣም ረጅም ጥናት ነው:: ጠቅላላ የአገሪቱን ሁኔታ በማገናዘብ የተፃፈ ሲሆን፤ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ የደርግ አብዮታዊ እንቅስቃሴና የተፈጠሩ ችግሮች እነሱን በማጥናት አንድ ሌላ መፅሐፍ Ideology & Elite Conflicts: Autopsy of the Ethiopian Revolution የሚል ፃፍኩ:: እንግዲህ እነዚህ ሦስት መፅሀፎች ናቸው የተፃፉት::

**ግዮን፡- እነዚህ መፅሀፎች ወደ አማርኛ ተተረጉመዋል ዜጎች እንዲያነቡት ዕድሉ ተፈጥሯል?**

ፕ/ር መሣይ፡- አልተተረጎሙም!! አንድ ሠው አንድ ግዜ ኢትዮጵያን Survival and Modernization: Ethiopia's Enigmatic Present የሚለውን ልተርጉም አለኝ:: ችግር የለም፤ ይቻላል፤ ቀጥል አልኩት፤ ተቃውሞ አልነበረብኝም:: ከአሳታሚው ጋር መነጋገር አለብኝ፤ መብቱ የሱ ነው አልኩት:: ውጤቱ ሳይታወቅ ልተርጉም ያለው ሰው ድምፁ ጠፋ:: ከዚያ በኂላ ማንም ለመተርጎም የጠየቀ የለም::

**ግዮን፡- በደርግ ዘመን ከተለያዩ ሀላፊነቶች ባለፈ የኢሰፓም አባል ሆነው እንደሰሩ ነግረውናል:: ይህንን ስራ በሙሉ ልብና ድጋፍ ነበር ሲሰሩ የነበሩት?**

ፕ/ር መሣይ፡- ሁለት ነገሮች ልናገር:: አንደኛው እኔ ጠንካራ የማርክሲስት ሌኒኒስት ዲፓርትመንት ለማቋቋም ፍላጎት ነበረኝ:: እናም ይህ ለኔ መጠቀሚያ ሆነኝና ጠንካራ ጥናቶችን የሚያዘጋጅና የሚቀርፅ ዲፓርትመንት ለመመስረት ብዬ ብዙ ታገልኩ:: በዚህ ወቅት ትልቁ ችግሬ ምንድን ነበረ? ያኔ የተማረውም፣ ያልተማረውም፣ ካድሬውም ሌላ ሌላውም፤ በተለይ ከሌሎች ሶሻሊስት አገሮች አገር ሁሉ እየመጡ ማርክሲስትን እናውቃለን፤ እናስተምራለን የሚሉ ስለነበሩ ከእንዲህ አይነት ሁኔታ ዲፓርትመንቱን መከላከል ነበረኝ:: ይኽን ደግሞ ሳደርግ የምችለው ትንሽ በየኒቨርስቲው ውስጥ ተደማጭነት ሳገኝ በመሆኑ የግድ አንድ ሃላፊነት ብይዝ ራሴንም ለመከላከል ይጠቅመኛል በሚል አስቤና አብሰልስዬ ነው የፓርቲው አባል ልሁን የሚል ድምዳሜ ላይ የደረስኩት:: ያም ሆኖ ብዙ ጊዜ ችግር ገጥሞኛል:: በተለይ ከራሺያ… ከምስራቅ ጀርመን አስተማሪዎች መጡና ብዙ ነገር በጠበጡብኝ:: ምክንያቱም እነሱ ዝም ብለው ፕሮፓጋንዳ ነው ማስተማር የሚፈልጉት ግድ የላቸውም:: እኔ ደግሞ ደንበኛ የሆኑ ፍልስፍና የሚያውቁ ሠዎችን ለማሰልጠን ነበር ፍላጎቴ:: በዚህ ልንስማማ አልቻልንም:: እኔ ግን የግድ ድጋፍና ራሴን መከላከል ያስፈልገኝ ስለነበረ በዚህ መሠረት ነው ወደዚያ የገባሁት::



ሁለተኛው ነገር ደግሞ ምንድን ነበረ? ይሄ ሁሉ ሠው አገሩን ጥሎ ሲሄድ፤ ምንድነው እየሆነ ያለው? ማን ነው ይሄን አገር የሚያቋቁመው?… ምክንያቱም ይታየኝ ነበር፤ ደርግ ቀስ በቀስ እየተዳከመ እንደሚሄድ:: በተለይ ከቀይ ኮከብ ዘመቻ በኂላ ግልፅ እየሆነ መጣ፤ እናም ለማነው አገሩ ተጥሎ የሚኬደው? የሚል ሀሳብ ነበረኝ:: ማንኛውንም ነገር እዚሁ ሆነን ብንጠጋግን አይሻልም ወይ የሚል አቋም ነበረኝ:: በሌላ በኩል ደግሞ ሌላ ነገር ውስጥ አልገባሁም ነበር፤ ግድያ…. እስር ምናምን ውስጥም የለሁም:: ቀበሌም የገባሁት ሠላም ከመጣ በኂላ ነው:: በእርግጥ ቀበሌ አንዳንድ ስራዎችን እወድ ነበር:: በተለይ መሠረተ ትምህርት የምከታተለውና የምደግፈው ስራ ነበር:: ቀጥሎ ቢሆን ኖሮም በከፍተኛ ደረጃ

ውጤት የሚያመጣ ነገር ነበር:: ግን ከሌላው የፖለቲካ ሁኔታ ተገንጥሎ ስለማይታይ ተቋረጠ:: በሌላም በኩል ስራን በተመለከተ ጠቃሚ ናቸው ብዬ ያመንኩባቸውን ስራዎች ሠርቻለሁ:: ለምሳሌ በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስር የታተመው የማሌ መዝገበ ቃላት (የማርክሲስት - ሌኒኒስት መዝገበ ቃላት) ከኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ጋር በመተባበር ሲዘጋጅ የፍልስፍናውን ክፍል የሠራሁት እኔ ነኝ::

**ግዮን፡- በወቅቱ ምንም እንኳ ራቅ ብለው ቢሆንም የሚሰሩት ችግሮች ሲከሰቱ ለፓርቲው የመጠቆም... ሀሳብ የመስጠት ነገር ነበረዎት፤ ዕድሉንስ አግኝተው ነበር?**

ፕ/ር መሣይ፡- አይይ!! እንዲህ አይነት ዕድል የለም:: መስራት ነው እንጂ ጠለቅ ብሎ ገብቶ ሀሳብ ማቅረብና ሌላም ሌላም ነገር ማድረግ አይቻልም ነበር:: ምክንያቱም ሁሉም ነገር የተወሰነና በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚሄድ ነበር:: ግን አንዳንድ ያሉኝን አላማዎች ለማስፈፀም ይረዳኛል በሚል ነው በውስጡ የቆየሁት:: በኋላ ግን እየታየኝ መጣ፤ ደርግ በጥቂት ጊዜ ውስጥ እየደከመና እየተፈረካከሰ እንደሚሄድ ግልፅ ነበር:: ይህ ሲሆን ሰው ሁሉ እየተሰደደ ወይም እንኳን ተሸነፈ እያለ ነበር:: እና በዚያ ሁኔታ ወያኔ መጥቶ አገሩ ላይ ቢጨፍርበት ምንም አይደንቅም:: ሠው ሁሉ ወጥቷል፤ ምሁራን ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ሠው መውጣት መውጣት ነበረ ስሜቱ:: የዚያኑ ያህል ኢትዮጵያዊነቱም አልደከመም ነበር:: ለምሳሌ ወጣቶች የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እንዘምታለን ሲሉ ሠው ሁሉ ተነሳባቸው፤ ተቆጣቸው:: ምን ማለታቸው ነው ተባሉ? እነሱ ግን ያውቁ ነበር፤ ብዙ ስለሚያዳምጡ ምን እንደሚመጣ... የወያኔ ማሸነፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን እንደሚያስከትል ያውቁ ነበር:: እናም ከደርግ የባሠ ነገር ነው የሚመጣው ብለው ነው የተነሱት:: ነገር ግን እኛ እናሸንፋለን ማለታቸው አልነበረም:: ሆኖም ሠው ተረባርቦ አገሩን እንዲያድን መንገድ ለመክፈት ነው ያንን ያደረጉት:: ግን መጨረሻው ጥሩ አልሆነም::

**ግዮን፡- ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘና እናንተም ከተባራራችሁ በኋላ ከባለስልጣናቱ የቀረበልዎ የ አብረን እንስራ ጥያቄ አልነበረም?**

ፕ/ር መሣይ፡- በኔ በኩል ምንም ዓይነት ጥያቄ አልቀረበልኝም:: ምክንያቱም እኔ እነሱ ጋር ምንም ቦታ የለኝም:: እነሱ የሚከተሉት የዘውግ አመለካከት ጨርሶ የማልቀበለው ነው::

**ግዮን፡- ፕ/ር እስቲ ደግሞ ወደቤተሰብ ታሪክ እንግባ::**

ፕ/ር መሣይ፡- ከባለቤቴ ጋር የተገናኘነው ፈረንሣይ አገር ነው:: እሷም የሊሴ ገ/ማርያም ተማሪ ነበረች:: ከዚያ ነው አብረን የመጣነው:: ሦስት ልጆች ወልደናል:: ይኸው ነው::

**ግዮን፡- ከ27 ዓመታት በኋላ ገዢው መንግስት የለውጥ እርምጃ ወስጃለሁ ብሎ በተናገረው መሰረት በርካታ በስደት ላይ የነበሩ ሠዎች ወደ አገር ቤት እየገቡ ነው:: እርስዎ ደግሞ ለረጅም አመታት በአሜሪካ ቆይተዋልና ለዚህ ጥሪ ምላሽ ያልሰጡት ወይም ለመግባት የዘገዩት በምን ምክንያት ይሆን?**

ፕ/ር መሣይ፡- ልክ ነው:: እንግዲህ ወደ አሜሪካ የመጣሁት በፈረንጆቹ አቆጣጠር 1996/97 አከባቢ ነው:: ስራ የተቀጠርኩት ደግሞ በ1998 ነው:: ለምን ወደ አገር ቤት አልገባህም ለተባለው በሃሣቤ አለ፤ ለመግባት ጉጉቱ አለኝ:: ግን አንደኛ አሁን በማስተማር ላይ ስለሆንኩ አቋርጬ መሄድ አልችልም:: በቅድሚያ ነገሮችን ማስተካከልና ማሳወቅ አለብኝ:: ለዚህ ሁሉ ደግሞ ግዜ አላገኘሁም:: ሁለተኛው ደግሞ መጥቼ ምን ልሠራ እንደምችል ግልፅ አይደለም:: አሁን ባለው ሁኔታ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው:: ለማንኛውም በቀጣዩ አመት የአራት የሦስት ወር እረፍት አለኝ፤ ያኔ እመጣለሁ ብዬ አስባለሁ::

ስለመጣው ለውጥ ብዙ አጠናለሁ:: በመሰረቱ አገር ቤት ደርሠው ከሚመጡ ሠዎችም ጋር እገናኛለሁ:: ብዙ አነብባለሁ ...... ጋዜጣም መጽሄትም አያለሁ:: መረጃው አለኝ:: ግን በቅርቡ ደግሞ አዲስ የመፅሀፍ ስራም ጀምሬያለሁና እሱ ስራ ላይም ተጠምጄ ነበር፤ እሱ እየተገባደደ ስለሆነ የመምጣቴን ነገር የማስብበት ጊዜ ይኖረኛል ብዬ አስባለሁ::

**ግዮን፡- አዲሱ መጽሀፍዎ በምን ዙሪያ ነው የተፃፈው?**

ፕ/ር መሣይ፡- ስለ አንድ ፈረንሣያዊ ፈላስፋ ነው የፃፍኩት፤ በርክሠን የሚባል:: ብዙ አመት ያነበብኩት፣ ብዙ ያሠብኩበት ፈላስፋ ነው:: ስለእሱ ፍልስፍና እንዲሁም ስላነሳቸው ችግሮች፤ አፈታታቸውስ እንዴት እንደሆነ የሚመረምር መፅሀፍ ነው::

**ግዮን፡- ከ27 ዓመት በኋላ ተስፋ ሠጪ የሆነ የለውጥ እንቅስቃሴ እየታየ ነው:: እርስዎ ደግሞ በአገርዎ ጉዳይ በተገኘው አጋጣሚ ከመናገር አልተቆጠቡምና አሁን የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ እንዴት ያዩታል?**

ፕ/ር መሣይ፡- እንግዲህ ለውጡን በተመለከተ ማንም በዚህ ሁኔታ ይከሰታል ብሎ የጠበቀ ሠው የለም:: ጭራሽ ተፈረካክሰው ወደለየለት ብጥብጥ ወይም ሌላ ነገር ውስጥ ይገባሉ ተብሎ እንጂ የተገመተው ዶ/ር ዐቢይ በዚህ መልኩ ወደ ስልጣን የመምጣቱ ነገር አልታሰበም:: ለውጡ ከመከሰቱ በፊት ወያኔ እንዳበቃለት ግልፅ ነበር:: ግን ከዚያ በኋላ የሚመጣው ማነው? ምንድነው? የሚለው ሁላችንንም ውዥንብርና ጥያቄ ውስጥ ከትቶን ነበረ:: ይሄ ምንም የሚያነጋግር አይደለም::

እናም አብይ ሲሾምና መጀመሪያ ያደረገው ንግግር ነው እንግዲህ እኔንም ሆነ ሁሉንም ሠው የማረከው:: ያም ደግሞ ምንድነው? ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ስለኢትዮጵያዊነት ሲያነሳ፤ አሁንስ መልካም ነገር የመጣ ይመስላል የሚል ስሜት በሁሉም ዘንድ ተፈጠረ:: ከዚያ ወዲያ ሁሉንም ነገር መከታተል ጀመርኩ:: የሚናገረውን፣ የሚሠራውን ሁሉ ለማየት ሞከርኩ:: እንዲያም ሆኖ አሁን እየተከሰቱ ያሉት ችግሮች ይፈጠራሉ የሚል ግምት ነበረኝ:: ምክንያቱም ኢትዮጵያ በብዙ ችግሮች የታጠረች ስለሆነች:: እንዲህ ዓይነት ዓላማ ያለው ለውጥ ለማምጣት ሲፈለግ በጣም ብዙ ችገሮች እንደሚገጥሙ ግልፅ ነው:: አሁን ላይ አንድ በአንድ እየተከሰቱ ነው:: እንግዲህ ምን ያህል እነዚህ ችግሮች ሊቀረፉ ይችላሉ ወይስ ወደመጨረሻው ላይ እሱ ራሱ (ዐቢይ) ችግሮችን ማሸነፍ ያቅተዋል? የሚለው ጥያቄ አሁንም ጭንቅላቴ ውስጥ አለ::

**ግዮን፡- ከዚህ በመነሳት አሁን በየክልሎቹ የሚታዩት ችግሮች በተለይም የመፈናቀሉ አደጋ መነሻው ምን ሊሆን ይችላል ይላሉ?**

ፕ/ር መሣይ፡- በዚህ ዐቢይን ተጠያቂ አላደርገውም:: ምክንያቱም እነዚህ ችግሮች በፊትም ነበሩ:: አስቀድሞ የተቋቋመው የዘውግ ስርዓት ወደ ፀብና የህዝቦች መፈናቀል እንደሚወስድ ግልፅ ነው:: የነበረው መንግስት በሀይል ስለሚጠቀም ይህንን ሁኔታ አፍኖት ነበር የቆየው:: አሁን ዐቢይ ለቀቅ ሲያደርገው ጊዜ ያ ገንፍሎ ወጣ:: የተወረሰ ችግር ነው ይሄ:: ስለ ዐብይ ስንነጋገር እኔ ትንሽ ግራ የሚገባኝና ሌሎች ያልተረዱት ካለፈው ስርዓት የተወረሱ ብዙ ችግሮች እንዳሉ ነው:: ባለው የኢኮኖሚው ሁኔታና የኢህአዴግ መዋቅር ለውጥ ማምጣት በራሱ ችግር የሚፈጥር ነው:: ይሄንን መለየት አለብን::

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የማየው ምንድን ነው? ዐቢይ በጣም ብሩህ ተስፋ አለው፤ ብዙ የሚመኝ እንደመሆኑ መጠን ደግሞ ብዙ ነገሮችን ስለቀሰቀሰና ፍላጎቶችን ስላስነሳ፤ አሁን ያነሳውን ነገር ሁላ ይችለዋል ወይ? እንቅስቃሴውን ሊመግበው ይችላል ወይ? የሚል ጥርጣሬ አለኝ:: ለምሳሌ ሕዝቡ በዴሞክራሲ ራሱን አስተዳድሮ የማያውቅ ህዝብ ነው፤ በጣም አዲስ ነገር ነው:: በአንዴ ወደ ዲሞክራሲ እንሸጋገራለን የሚለው ዓላማ ይሳካል ወይ? ዝም ብሎ ተቋማትን መዘርጋት ብቻ ሳይሆን በብዙ ትምህርትና ውጣ ውረድ የሚገኝ ባህል ነውና ይህን ሁሉ ሳናከማች ያሠብነው ለውጥ ለማምጣት ይቻላል ወይ? የሚል ጥያቄ አለኝ:: በሌላም በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ችግር ሁሌ ምንድነው? አንዱ በሚገዛበት ግዜ ያ ተገዢ የሆነው እውክላለሁ የሚለው አካል ስለ ዲሞክራሲ፣ ስለዕኩልነት ያወራል፤ ግን ደግሞ እሱ በተራው ስልጣን ላይ ሲመጣ እራሱ የገባውን ቃል በሙሉ ትቶ ወደ በላይነት ፍለጋ ያመራል:: ስለዚህ የፈረቃ አገዛዝ ነው የሚያደርገው::ይህ ነው እንግዲህ የዲሞክራሲን አገዛዝ እንዳይመጣ የሚያደርገው:: ስለዚህ ያሉት የአገሪቱ ሁኔታዎች ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማድረግ ያስችላሉ ወይ? አንዳንድ ነገሮች እስኪሟሉ ድረስ ትንሽ የሽግግር ሁኔታ መፍጠር አይሻልም ወይ? የሚሉትን በአግባቡ ማየት መልካም ይመስለኛል::

**ግዮን፡- አንዳንድ ምሁራን ብሔራዊ ዕርቅ ያስፈልጋል፤ የሽግግር መንግስትም መመስረት አለበት ይላሉ:: እርስዎ ከየትኛው ይወግናሉ?**

ፕ/ር መሣይ፡- የሽግግር መንግስት በሀሳብ ደረጃ ጥሩ ነው:: ነገር ግን የትኞቹ ፓርቲዎች ናቸው ተሰባስበው አንድ ሆነው የሚሰሩት:: አሁን

ያሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሙሉ አብረው መስራት አይችሉም:: በወያኔም ጊዜ የነበረው ችግር ይሄው ነው:: የተበታተኑ ፓርቲዎች ናቸው፤ ሁሉም የየራሱን ፕሮግራምና አመለካከት ብቻ ነው የሚያራምደው:: እና ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን ትተው ወደ አንድነት መምጣት አልቻሉም:: ይህ መሆን ካልቻለ እንዴት ነው ታዲያ አገር የሚገዙት? ለምሣሌ የቅንጅትን ታሪክ እንየው፤ አብረው ተነሱ፤ ችግር ሲመጣባቸው ተበታተኑ:: ከዚያ የምናውቀው ሁኔታ ላይ ደረስን:: ተቃዋሚ ፓርቲ የሚባለው ምናልባት ትንሽ ከግንቦት 7 በስተቀር ሌሎቹ ምንም አስተማማኝ መሰረት የላቸውም:: እንዴትስ ነው በዚህ አካሄድ አብረው የገዢ ፓርቲ ሥራ የሚሰሩት? በአንድ ፕሮግራምና አመራር ስር መሰባሰብ ያቃተው ሀይል እንዴት አንድ መንግስት ሊመራ ይችላል:: ስለዚህ ያለን አማራጭ ያው ኢህአዴግ ነው:: እና ደግሞ በኢህአዴግ በመጠቀም ለውጥ ማምጣት በጣም አስቸጋሪ ነው::

**ግዮን:- መፍትሄው ምን መሆን አለበት ይላሉ?**

ፕ/ር መሣይ:- እሱ እንግዲህ ብዙ የሚያወያይ ነገር አለው:: እንደውም ሌላ ነገር አስታወስከኝ:: የአብይ መንግስት የአንድ አመት ቆይታ በሚል እየሰራሁት ያለ ጥናት አለኝ:: ችግሮቹ ምን ምን ናቸው የሚል ይዘት አለው:: መፍትሄውስ የሚለው ግን እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው:: ግን መጀመሪያ ችግሮቹን አውቀናቸዋል ወይ የሚለው ነው ትልቁ ነጥብ:: መፍትሄ ከመፈለግ በፊት ችግሮቹን መለየት አለብን:: ምክንያቱም እውነተኛና ዝም ብሎ የተፈጠረ ችግር አለ:: ለምሣሌ ሁሉም አማራጭ የለንም ይላል:: ሌላ አማራጭ ከሌለን እኮ መሰባሰብ አለብን:: ተሰባስበህ አንድ ስምምነት ላይ እየተደረሰ ነው ወይ? እኔ ደሞ ይህን አይደለም የማየው:: ትክክለኛው ግንዛቤ ላይ ተደርሷል ወይ ብለን መጠየቅ ወይም ደግሞ ውስብስቡን ሁኔታ መፍቻ መፈለግ አለብን ነው:: ግን የሽግግር መንግስት ይቋቋም ስላልን ችግሮቹ ይጠፋሉ ማለት አይደለም:: የሽግግር መንግስቱ ምንድ ነው የሚያደርገው? ምንድነው የሚሰራው:: አሁን ካለው የተሻለ ምንድነው የሚያመጣው? ለማንኛውም ለውጡ ቀላል አይደለም:: ችግሮች አሉ፤ ግን ይህንን መገንዘብ ነበረብን፤ ዝም ብለን እንደሚፈስ ውሃ መሄድ እንዳልሆነ ሁላችንም መገንዘብ አለብን:: አንዳንዱ ገና አሁን ይነቃል፤ ይሄ ችግር እንዴት መጣ ይላል:: የአዲስ አበባን ነገር ብንጠቅስ ጥያቄው አክራሪዎች የሚያነሱት ጥያቄ ነው:: ለነሱ ደግሞ ህዝቡን ማዋከብና ማጋጨት ለፖለቲካቸው ድጋፍ ያስገኝላቸዋል:: የሚሰሩትም ለዚሁ ነውና በእርጋታ መታየት ይኖርበታል::

**ግዮን:- የአዲስ አበባው ጥያቄ ተገቢ አይደለም እያሉኝ ነው? ከፕሮፌሰር መሣይ ከበደ ጋር በዚህና ወቅታዊ በሆኑ የአገራችን ጉዳይ ላይ ያደረግነውን ሰፊ ውይይት በቀጣዩ ሳምንት ቀሪውን ክፍል ይዘን እንቀርባለን::**



ሲሳይ አጌና

# በመንገጫገጭ ውስጥም ደማቅ ለውጥ አለ!

በኢትዮጵያ አንድ ዓመት ያስቆጠረው ለውጥ፣ በብዙ ፍላጎቶች እንዲሁም ሥልጣናቸውን በተነጠቁ ወገኖችና የፖለቲካ ንግድ ላይ በቆዩ ሃይሎች ፈተና እየገጠመው መሆኑ ግልጽ ነው::ይህ ዛሬ የሚታየው መንገጫገጭ ግን የትናንቱን የመቃብር ሕይወትና የመቃብሩን ጥልቀት በፍጹም ሊያስረሳን አይገባም::

ኢትዮጵያውያን ያለፍንበትን መከራ በማሳሰል ብቻ ሳይሆን መውጫችን ምንድነው? ብለን የተጨነቅንበትን ጊዜ መልሰን ስንቃኝ፤ ዛሬ ያለንበት ሁኔታ በጉንፋን የሚመሰል ቀላል ሕመም ሲሆን፥ በየአካባቢው ያለው ቆሻሻ ድርጊት ከቀጠለ እና የዕልህ ጉዞው "በእኛ እና እነሱ" ቅኝት ከዘለቀ ግን ጉንፋኑ "ተስቦ" ሆኖ ሁላችንንም እንደሚያጠፋ ከጥርጣሬ ባሻገር መናገር ይቻላል::መንግስት የየአካባቢው ጉልበተኞችን እንዲያስታግስ ፤ ሕዝቡም ራሱን ከጎበዝ አለቆች ስብከት እንዲጠብቅ መወተወቱ እጅግ አስፈላጊ ነው::ጨለማ መልሶ እንዳይወርሰን ከጨለማ ሰባኪዎች ራስን መጠበቅ ያስፈልጋል:: ትናንት የነበርንበትን ጨለማ ብቻ ሳይሆን፣ ከጨለማ ለመውጣት የነበረው መንገድ ሁሉ በራሱ ጽልመት የወረሰው መሆኑን በማስታወስ ዛሬን በከፍተኛ ሃላፊነት እና ጥንቃቄ እንድንጓዝ ግድ ይለናል::

መጋቢት 30 2011 ዓ.ም. "ለውጥማ አለ!?" በሚል ርዕስ በዚህ በብሄራዊ ቲያትር አዳራሽ "ብራና" ባዘጋጀው መድረክ አርዕስቱን መሰረት አድርገው የሚነሱ ጥያቄዎችን በተለይም ለውጥ የለም በሚል የሚሰሙ ድምጾችን በቀጣዮች ነጥቦች እናስልለውና (እናድክመውና) የለውጡን ትርጉም፣ ከለውጡ ዋዜማ ሁኔታ አንጻር እንፈትሸው::

አሸባሪ የተባለው ሚዲያ "ኢሳት" ጋዜጠኛ በአዲስ አበባ ብሄራዊ ቲያትር አዳራሽ ከናንተ ጋር እየታደመ ፣የሃገሪቱ ወህኒ ቤቶች ከፖለቲካ እስረኞች በጸዱበት፣ ጠመንጃ ያነሱትን ጨምሮ ሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች ወደ ሃገራቸው በተመለሱበት ፣ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ ለሁለት የተከፈለችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አንድነቷ በተረጋገጠበትና መንበራቸውን በፖለቲከኞች ውሳኔ የተነጠቁት ፓትርያርክ አቡነ መርቆሪዮስ ወደ ሥፍራቸው በተመለሱበት፣የሙብት ጥያቄ በማንሳታቸው ወህኒ የተቆለፈባቸው የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ስለዕምነታቸው በነጻነት በመስጊዳቸው በሚወያዩበት ፣ እንደ ርሥት 27 ዓመታት በሙሉ በአንድ ሰፈር ሰዎች በባሌበትነት የተያዙ የሥልጣን ቦታዎችን ሌሎችም ሲከፋፈል እያየን፣ አሳሪዎች በወንጀል ተጠርጥረው፣ እነርሱም በተራቸው ውህኒ ገብተው አቤቱታ ሲያቀርቡ እየሰማን ወዘተ "ለውጥ የታለ?" ብሎ የሚጠይቀውን ፣በግሌ "ለውጥ ምንድን ነው?" ማለቱን መርጨያለሁ::

ይህ ለውጥ ካልሆነ ምን ብለን እንጠራው ይሆን? ስያሜ ይስጡን እና እንሟገትበት::

በኢትዮጵያ የመጣው ለውጥ ትርጉም የሚኖረው መቃብር ውስጥ ለነበረው ሁሉ ቢሆንም ፣የመቃብሩን ጥልቀት ይበልጥ የሚረዳው ግን ከመቃብሩ ውስጥ ለመውጣት የተፍጨረጨረውና መውጫውን ያሰላሰለው ብቻ ነው::

ይህንን ከላይ እንደ ጠቀስኩት የራሴን አጋጣሚ በማንሳት ላብራራው::

በምኖርበት አሜሪካ ቨርጂኒያ ግዛት "ሊዝበርግ ፓይክ "በተባለ መንገድ ላይ የሚገኝ "ስታር ባክስ" የሚሉት ቡና መሸጫ አለ::ይሄ ቤት በብዛት የጎረቤት ሃገር ሶማሊያ ዜጎች ይሰባሰቡበታል::ምናልባትም ሞቃዲሾ ያላችሁ ያህል እንዳይሰማችሁ የሚያደርገው ሞቃዲሾን አለማወቃችሁ ወይንም ጥቂት ነጮች፣ እንዲሁም ስፓኒሾች እና የኤርትራ ሰዎች በማየታችሁ ሊሆን ይችላል::

ታዲያ እዚህ ቡና መጠጫ ሱቅ ውስጥ ሁልጊዜ ሶማሊያውያን ተሰብስበው ሳይ ሃገር አልባነታቸው ይመጣብኛል:: በሕይወቴ ተስፈኛ የሆንኩትን ሰው ተስፋ ቢስ ያደርገኝ እና ኢትዮጵያን መልሼ ማግኘቴ ወይንም ማየቴ፣ ከነአካቴውም ኢትዮጵያ በሕልውናዋ መቀጠሏ ያጠራጥረኛል::እናም ከዚህ ቡና መሸጫ ትኩሱን ቡና ይዤ ስወጣ በበጋ ሙቀት ብርድ ብርድ እያለኝ ፣ፊቴ ጭጋግ ለብሶ መፍትሄው ምን ይሆን ?እያልኩ ይበልጥ አሰላስላለሁ::

ሥልጣን ላይ የነበረው ቡድን እና መንግስት እንደሚወድቁ ጨርሶ ተጠራጥሬ ባላውቅም፣ የሚተካቸው ማነው? ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ ጥላቻ በተሰበከበት እና ተረት ታሪክን በተጫነበት ሃገር ፣ልዩነት ጌጥ እና ውበት መሆኑ ቀርቶ የጥላቻ እና የግጭት መንስኤ

▶ እንዲሆን መንግስታዊ እና የፓርቲ መዋቅር በሚተጋበት ሃገር ፣ አፋኙ እና ዘረኛው ሥርዓት ሲወገድ የሚተካው ማነው ? እንዴትስ ይወገዳል ? የሚለውን ብርቱ ጥያቄ እያሰላሰልኩ በዚሁ በቨርጂኒያ "ሊዝበርግ ፓይክ" ጎዳና ተመላልሺያለሁ፡፡

ብዙ ሳስብ ፣የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ ሥመረምር ከብርሃን ይልቅ ጭለማው እየበረታብኝ ፣ያለንበት የመቃብር ጥልቀትም ይበልጥ እየተገለጸልኝ መጣ ፡፡ ከሃገሬ የራቅሁት 12 ሺህ ያህል ኪሎሜትር ቢሆንም ውስጤ የገባው ሥጋት ኢትዮጵያን ጨርሶ የማልደርስባት አደረገኝ፡፡ ከማርስ በላይ በአያሌ ሚሊዮኖች ኪሎሜትር ኢትዮጵያ ራቀችብኝ፡፡ እንዴት ልድረስባት? ማን እንዴት ከዚህ መከራ ይገላግለን? መፍትሄ ፍለጋ አማተርኩኝ፡፡አማራጭ ማሰስ ጅርመርኩኝ፡፡

1ኛ/ከኤርትራ የሚነሱ አማጽያን ከዚህ መከራ ይገላግሉን ይሆን? በሚል እነርሱ ላይ በማተኮር አቅማቸውን፣ትብብራቸውን እና የኤርትራን መንግስት ድጋፍ ለመመርመር ሞከርኩኝ፡፡እነዚህ ብረት ያነሱና የኤርትራን መንግስት ከለላ ያገኙ አማጽያን አርበኞች ግንቦት 7፣ኦነግ፣አዲሃን፣ትህዴን፥ ARDUF፣ONLF ወዘተ በጋራ ቢሰሩና የትብብር ግንባር ቢፈጥሩ ሥርዓቱን በሃይል አስወግደው ሥልጣን መያዝ ይችላሉ ወይ? ለሚለው ሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ሥርዓቱን ለመጣል የሚያስችላቸው ቢሆንም ፥ሃገሪቱን ወደ ዲሞክራሲ እና መረጋጋት የሚወስድ መሆኑ ግን አጠራጣሪ ብቻ ሳይሆን አስፈሪም ነበር፡፡

ሥርዓቱ በከፍተኛ ደረጃ በመዳከሙ፣ እንዲሁም በሙሉ ልብ እና በግልጽ አማጽያኑን የሚረዳ የጎረቤት ሃገር መንግስት መኖሩ ብረት ያነሱት የኢትዮጵያ ሃይሎች በቀላሉ እና በፍጥነት የማሸነፍ ዕድል እንደሚኖራቸው በኡጋንዳ ሚልተን አቦቴ በኂላም ይዌሪ ሙሰቬኒ እንዲሁም በኮንጎ ሎራን ካቢላ በታንዛንያ እና በሩዋንዳ መንግስታት ድጋፍ በወራት እንቅስቃሴ ኢንቴቤ እና ኪንሻሳን መቆጣጠራቸውን በአስረጅነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ችግሩ ብረት ያነሱት የኢትዮጵያ ሃይሎች የተበታተኑ እና ተባብረው ለመስራት አለመፈለጋቸው ነው፡፡በተለይም የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ኢትዮጵያ ከሚሉ ሃይሎች ጋር ለመንቀሳቀስ አለመፍቀዱ፣ በኢትዮጵያ በወታደራዊ ሃይል መንግስት በመቀየር የተረጋጋ ሃገር ለመፍጠር እና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረት ያለውን ዕድል ብርቱ ጥያቄ ውስጥ አስገብቶት ቆይቷል፡፡ቡድኖቹ ተነጣጥለው ቢሄዱ እና ተሳክቶላቸው ቢያሸንፉ እንኳን ኦነግ ከኦሮሚያ ክልል ውጭ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡በሌላም በኩል አርበኞች ግንቦት 7 ቢያሸንፍ ሀገሪቱን በበከላት የዘር ፖለቲካ ሳቢያ ይህ ቡድን ቢያንስ በኦሮሚያ እና በትግራይ ክልል ተቀባይነት ማግኘቱ በእጅጉ አጠራጣሪ ነው፡፡እንደተበታተኑ በየሰፈራቸው ቢያሸንፉ ድግሞ ሃገሪቱ ባልተቋረጠ የዕርስ በርስ ጦርነት ውስጥ መዘፈቋ የማይቀር ይሆናል፡፡

ሥለሆነም በወታደራዊ ሃይል የነበረውን ሥርዓት ማፍረስ ቢቻልም፥የተረጋጋ ሃገር እና መንግስት ማምጣት እንደማይቻል ሲታየኝ ከመከራ የምንፈታበት፣ መዳኛችን ምን ይሆን? በሚል ሌላ መውጫ አሰላስላለሁ፡፡

2/ሥልጣን ላይ ያለውን መንግስት ለማስወገድ ያለው ሌላው አማራጭ ሕዝባዊ አመጽ ወይንም ሕዝባዊ ዕምቢተኝነት ነው፡፡ሕዝባዊ አመጽ ደግሞ በመጨረሻው ምዕራፍ መልክ የሚይዘውና ፍጻሜ የሚያገኘው በወታደሩ ጣልቃገብነት እና ግፊት መሆኑም ይታወቃል፡፡በኢትዮጵያ ያለው ወይንም የነበረው የሰራዊቱ አደረጃጀት እና አመራሩ ሲታይ በሕወሓት ፍላጎት የተዋቀረ እና በሕወሓት ታጋዮች ቁጥጥር ሥር የሚገኝ በመሆኑ፤ የሕወሓትን አገዛዝ ለማስወገድ የሚደረግን ትግል እንኳን ደግፈው ሊቆሙ ገለልተኛ ሆነው እንኳን እንድማይታዘቡ፣ ይልቁንም ወደ ጭፍጨፋ ሊያመሩ እንደሚችሉም ሳይታለም የተፈታ ነው፤በተግባርም ያየነው ይህንኑ ነው፡፡

ከ15 ዓመታት በፊት በዩክሬን ኬቭ እና በጆርጂያ ቲቢሊሲ ጎዳናዎች የታየው ኦሬንጅ እና ሮዝ ሪቮሉሽን(የብርቱካን እና ጽጌረዳ አብዮት) እንዲሁም በቅርብ ዓመታት እ/ኤ/አ በታህሳስ 2010 በቱኒዚያ የተነሳው እና በአረቡ ዓለም በተቀጣጠለው የሞሃመድ ቡዓዚዝ አብዮት ዙፋናቸው ላይ ሲንገታገቱ የነበሩት አምባገነኖች ወንበራቸውን የተነጠቁት በወታደሩ ጣልቃገብነት አሊያም አመጹ ባስከተለው የትጥቅ ትግል መሆኑ ይታወቃል፡፡

ሕዝባዊ አመጹ ወደ ትጥቅ ትግል ያመራባቸው ሊቢያ እና የመንን የመሳሰሉ ሃገራት ደግሞ አምባገነኖቹን ኮሎኔል ሙዓመር ጋዳፊን እና አሊ አብደላህ ሳላን ቢገላገሉም፤ ሃገራቱ አሁንም በቀውስ ውስጥ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ሕዝባዊ አመጹ ብቻውን መፍትሄ ያስገኘባቸውን ሃገራት ግብጽን እንድምሳሌ ብንወስድ እንኳን ሕዝባዊ ተቃውሞው የተገታው እና የፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ ስንብት የተከተለው በወታደሩ እና በጸጥታ ሃይሉ ጣልቃገብነት ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው በኢትዮጵያ የነበረውን የወታደሩን አወቃቀር ስንመረምር በሕዝባዊ አመጽ ለለውጥ የሚነሳውን ሃይል ወታደሩ የሚደግፍ ሳይሆን ፣የሚጨፈልቅ በመሆኑ በሕዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያ ለውጥ ማምጣትን እጅግ አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ ታዲያ እንዴት ለውጥ ሊመጣ ይችላል? ስል ቆይቺያለሁ፡፡በወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት ለውጥ እንዳይመጣ አመራሩ በሕወሓት ሰዎች በመያዙ ከላይ ግልበጣ ማድረግ የማይታሰበውን ያህል፣ከሥር የሚነሱ ዝቅተኛ መኮንኖችም በዘር በተከፋፈለ ሰራዊት ውስጥ ወታደራዊ ግልበጣ የማድረግ ዕድላቸው ዜሮ ነው ማለት ይቻላል፡፡ቢሳካለቸው እንኳን ሰራዊቱ በዘር ተከፋፍሎ ይታኮሳል እንጂ ሕወሓትን ከቤተ መንግስት ማውጣት አይቻለውም፡፡

ታዲያ ሃገሪቱ ወደ ቀውስ ከምታመራ ዘረኝነት እና ዘረፋን የአመራር ፍልስፍናቸው ያደረጉት ሕወሓቶች የጫኑብንን ባርነትን ፈቅደን፣ዘረፋውንም ይሁንላቸው ብለን ብንተዋቸውስ እንኳን ሃገሪቱን ብድር ማጥ ውስጥ ከተው የሃገሪቱን ኢኮኖሚ ፈተና ላይ የጣሉበት አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ በመውደቃችን ፣እነሱም በሥልጣን ኢትዮጵያም በሕልውናዋ መቀጠሏ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡


እንዲህ ግራ ተጋብቼ ፣እይዝ እጨብጠው ቸግሮኝ ባለሁብት እና እንደ ጎረቤት ሶማሊያ ዜጎች ሃገር አልባነት እየተሰማኝ በነበረበት ወቅት በኢትዮጵያ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመጽ ተስፋ ቢዘራብኝም መድረሻው የት ይሆን? የሚል ብርቱ ስጋትም አልተለየኝም ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አመጽ ከግብጽ እና ቱኒዚያ የተለየ፣ ከሊቢያ እና የመን የባሰ አደጋ የሚደቅን በይበልጥም ወደ ሶርያ የተጠጋ መሆኑ ይታየኝ ነበር፡፡በሶርያ በአንድ ዕምነት ተከታዮች ማለትም "የሺአ" ሙስሊሞች ውስጥ "አለዊት" የሚባለው ሴክት ወይንም ክፍል የሃገሪቱን መሪነት፣ ጸጥታ እና መከላከያ በመቆጣጠሩ ሕዝባዊውን አመጽ በጉልበት ለመጨፍለቅ ተንቀሳቀሰ፡፡ በውጤቱም ለአሸባሪዎች ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡በዚህም ዛሬ ሶሪያ በተለይም ጥንታዊቷ ከተማ አሌፖ ፈራርሳ ነዋሪዋቿም የምድር ሲኦል ውስጥ ወድቀዋል፡፡

ግጭቱ ከተፈጠረበት ኤ/አ/አ 2011 እስከ ሜይ 2013 በሁለት ዓመት ብቻ 94 ሺህ ሰዎች መሞታቸውን Syrian Observatory for human rights የተባለ መቀመጫውን ብሪታንያ ያደርገ

ተቋም ገልጿል፡፡ባለፉት 8 ዓመታት የሟቾቹ ቁጥር 400 ሺህ መድረሱን በሶርያ የተባበሩት መንግስታት እና የአረብ ሊግ መልዕክተኛ ይፋ አድርገዋል፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሃገሪቱን አንድነት የጠበቀና ዕልቂትን የቀነሰ ለውጥ እንዴት ይመጣል? ብለን ግራ በተጋባንበት አንዲት ጥይት ሳይጮህ፣ በኢትዮጵያ የተከሰተውን ለውጥ ተዓምር ብለን እንዳንጠራው ዛሬ እዚህም እዚያም የሚከሰቱ አሳዛኝ ክስተቶች የሚያግዱት አይሆንም፡፡ያን አስፈሪ የተባለውን ሁኔታ በእግዚአብሄር ርዳታ እና በለውጥ ሃይሉ ጥረት የተሻገርን ቢሆንም፤ ዛሬም ኢትዮጵያን ወደ መከራ፣ ሕዝቧንም ወደ ዕልቂት ለመክተት የሚረባረቡ ሃይሎች መኖራቸውን እያየን በመሆኑ ሁላችንም "ዕረፉ" ልንላቸው ይገባል፡፡ሥልጣን ላይ ያሉት ወገኖችም የችግሩን አሳሳቢነት እና የአደጋውን ሥፋት ይበልጥ የሚያውቁት በመሆናቸው በተዋረድ ከተኮለኮሉ ብሄርተኞች እና መንደርተኞች መዋቅራቸውን እያጸዱ ካልተጓዙ መንገጫገጩ ይቀጥላል፡፡ በመንገጫገጩም ውስጥ ቢሆን በጣም በደማቁ የሚታይ ለውጥ ግን አለ፡፡



ደበበ እሸቱ (አርቲስት)

# እንዴት ያቅተናል?

አዎን! ለውጥማ አለ፤ሁኔታ ዎችን የማገናዘብ አቅም በማጣት ብቻ መልካሙን መንገድ ተከትለንና ጠብቀን በርጋታ ካሰብንበት መድረስ እንዴት ያቅተናል? ለውጥማ አለ፣የአካሄዳችንን ሥልቱን በአግባቡ ነድፈውልን፤ ቅድመ ችግሩን እነሱ ተወጥተውልን፤ እንቅፋቱ ሳይመታቸውና ለእኛም እንዳይተርፍ በረቀቀ የጥምረት ዘዴ አልፈው፣ አሳልፈውን ፣ ከምንናፍቀው ሕልም ፣ ራእያችን መድረስ እንዴት ያቅተናል?

ያም ሆኖ ለውጥ አለ፤ሠላምን፣ መግባባትን፣ አስተምሮን፤ የአንድነትን ጥቅም አሳይቶን፤ የመ ተሳሰብና የመተጋገዝ ጥቅሙን በተግባር አመላክቶና ውጤቱንም ከወዲሁ በማስረጃ አስረግጦ፣ አረጋግጦልን ሳለ፤ እኛ ካሰብንበት መድረስ እንዴት ያቅተናል? ለውጥማ አለ።

ለዓመታት በጀብደኝነት "ከኛ ሌላ ላሣር" መመርያቸው በማድረግ፤ከእኛ ይልቅ "እኔን" በማስቀደም ለረሃብ፤ ለበሽታ፤ ለእርዛት፤ ለሥደት መዳረግ እንዲበቃ፣ "ሁሉም ዜጋ እኩል ነው፤ ሁሉም በሃገሩ ላይ በአብሮነትና በሠላም ሊመክርና ሊዘክር፣ የዜግነት መብቱ ነውና ከያላችሁበት ተሰባስባችሁ ለሠላማዊ ሃገር ግንባታ እንምከር፤እንጣር፤ ማንም ማንንም አይበልጥም፤ ከማንም ከምንም የምትበልጥ ኢትዮጵያ ነችና፤ በኢትዮጵያዊነት ኮርተንና ተከባብረን የምንሰደድባትን ኢትዮጵያን የምንኖርባት ኢትዮጵያችን እናድርጋት" ስንባል ከዚያ መድረስ እንዴት ያቅተናል?

## ለውጥማ አለ

ትልቁን እንጀራ አብረን እየተሳሰብን በሕብረት እንብላና ለአንድነታችን ማረጋገጫ የሚሆነንን ሠላም ከዳር እስከዳር እንተግብር ስንባል፤ እንጎቻ እንጀራ ላይ እየተሻማን ከምንበላው የሚወድቀው እንዲበዛ እንዴት እንመርጣለን? ያም ሆኖ ለውጥማ አለ።

ትልቅ እንደነበርን ትልቅ እንድንሆን፣ ትልቅ እናስብ፤ ትልቅ ስንሆን ሃገርም ሕዝብም ትልቅ ይሆኑና ወደቀድሞው ማንነታችን ተመልሰን፤ማንነታችንም ይከበር።ሠንደቃችንን ሌሎች ሃገራት ለነፃነታቸው አርማቸው ለማድረግ እንደወደዱት መስከረናልና ያንን ትልቅነት እንመልሰው ስንባል ምን ነክቶን ነው ማቆልቆልን፤ መውደቅን፤ ትንሽነትን፤ የማይጠቅመንን የሙጢኝ ማለትን የመምረጥ ልክፍት የያዘን? ምንስ ነካን?

## እንደዚያም ሆኖ ለውጥማ አለ!

በሀገራችን ተቃዋሚ ይሁኑ ተፎካካሪ ተብለው የሚጠሩትን ፓርቲዎች በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትራችን በትንሹ ከ30 ጊዜ በላይ "ኢትዮጵያ ይህን ሁሉ የምትሸከምበት ትከሻ የላትምና ሰብሰብ ብላችሁ ወደ 4/5 ዝቅ በማለት ተደራጁ" ማለታቸውን ሰምተው፣ ግን አለመስማትን የመረጡ፤ወይም ሰምተውት "ወደ 4/5 ዝቅ ለማለት ስናቅድ የእኔ ፓርቲ እዚያ ውስጥ ለመካተቱ ምን ዋስትና አለ? በሚል የመላ ምት ፍራቻ የቁጥሩን መቀነስ ከመቀበል ይልቅ ጥሪውን ወይም ሃሳቡን ሰምቶ አለመስማትን ምርጫቸው ያደረጉ ይበዛሉ።

እንዲያም ሆኖ ግን ለውጥማ አለ፤ሁሉም ፓርቲዎች የአቋማቸውን ደረጃ ለማወቅና ለህብረተሰቡም ለማሳወቅ ማድረግ ያለባቸው፣ ያሏቸውን የፓርቲ አባላት በሁለት ከፍለው ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል።

1. አንድ ፓርቲ አባላት አሉኝ፣ እነዚህ አባላቶቼም የወርሃዊ ክፍያቸውን በምዝገባ ወቅት በፓርቲው መተዳደርያ ደንብ በፈቃደኝነት ሊከፍሉ የገቡትን ቃል ያለምንም ቀስቃሽና አስታዋሽ የሚፈጽሙት የፓርቲው ቁንጮ አባላት ናቸው። ክፍያውም አቅም ያላቸውንም፣ የሌላቸውንም ማእከል ያደረገ ሆኖ የተመደበ ሊሆን ተገቢ በመሆኑ በዘዴ ለሁሉም መንገድ መተለም ያስፈልጋል። ለዚህም በአብዛኛው በሥራ ላይ የሚውለው በደምወዝ በመቶኛ የሚቀመጥ ነው። ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ ለሌሎች አባላትም እንደየ አቅማቸው ሊከፍሉ የሚችሉበትን ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል።

በዚህ መሠረትም ሁሉም ተፎካካሪ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው ስንት ወርሃዊ ክፍያቸውን የሚያሟሉ አባላት እንዳላቸው በይፋ ለሕዝብ ማሳወቅ ይገባቸዋል።

አልፎ አልፎ እንደሚነገረው ሁሉም ተፎካካሪ ፓርቲዎች አባላት አለን ቢሉም የአባልነት ክፍያን ግን በመጀመርያው የምዝገባ እለት ከከፈሉ በኋላ የማይከፍሉት ይበዛሉ ይባላል። ይህን ማጥራትና አባላት የአባልነት ክፍያን የመክፈል ግዴታቸውን እንዲያከብሩና ድርጅታቸውንም የኢኮኖሚ ጉልበታም ማድረግ ግድ ሊላቸው ይገባል።

## እንዲያም ተብሎ ለውጥማ አለ

በሌላ በኩል ደሞ የፓርቲውን ሥም ብቻ በመያዝ አንድ ሰብሳቢና ቢበዛ 10 አጃቢዎች ይዞ ነው "ተቃዋሚ ፓርቲ ነኝ" ብሎ ቁጥር ውስጥ የገባው ይባላል።የዚህም ማስረጃዬ ፌስ ቡክ ነው።

ይህ ቢጠራና እያንዳንዱ ተቃዋሚ አልያም ተፎካካሪ ፓርቲ ምን ያህሉ አባላቸው የአባልነት ክፍያ ከፍሎ እንደሚገኝ ቢታወቅ፣ በመቶ እየተቆጠረ ያለውን በትንሹ ከ70 እስከ 80% ዝቅ ያደርገውና ከዚያ በመነሳትም ወደ ተፈለገው ቁጥር 4ተፎካካሪ ፓርቲ ማውረድ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ።

ይህን ለማድረግስ የፍቃደኝነት ማጣት ችግር ካልሆነ እንዴት ያቅተናል? የእያንዳንዱ ተፎካካሪ ፓርቲስ መተዳደርያ ደንብ ፓርቲው ቆሜለታለሁ ከሚለው መርህ አኳያ ተጠንቶ ተመክሮበት የተዘጋጀ ነው? ወይስ ከሌሎች ቀደም ካሉ ፓርቲዎች በ"ቁረጥ ለጥፍ" ጥበብ የተዘጋጀ ነው!?

እንደ እኔ አመለካከት ከሆነ በትንሹ ካሉት በጣም ጥቂት ከሚባሉት በቀር "በቁረጥ ለጥፍ" ነው ወደሚለው አደላለሁ።ከዚሁ ከመተዳደርያው ደንብ ሳንወጣ መተዳደርያ ደንባቸው ላይ ኢትዮጵያዊነትን የሚያቀነቅኑትስ ምን ያህሉ ናቸው? ይህን ያልተቀበለ አለያም የተቀበለ እያስመሰሉ ገባ ወጣ የሚጫወቱ ይኖሩ ይሆን? መተዳደርያችንና ለትግል የምናነሳቸው ጭብጦች ተመሳሳይነት ካላቸው፤ ተለያይቶ መቆም ለምን አስፈለገ?

ለውጥማ እርግጥ አለ፤ ከጅምራቸው እኔን ይወክለኛል ብለው ወደ ለዩት ፓርቲ መቀላቀሉ እንዴት አቃታቸው? ለውጥማ..... ኢትዮጵያዊነትን አለመቀበል ለኔ እርግማን ሆኖ ይታየኛል፤ በኢትዮጵያዊነት ማመን ማለት ማንነትን ማወቅ፣ ትልቅነትን መታደል ነው።

አንድን አሜርካዊ ከየት ነህ? ብንለው ከአሜሪካ እንጂ ከዋሽንግተን፣ ኒውዮርክ፣ አትላንታ፣ ላስ ቬጋስ አይልም። ምክንያቱም አሜሪካን አስቀድሞ ከፍ ካለ በኂላ ኒውዮርክ፣ ዋሽንግተን ሲል መሠረቱን አስቀድሞ ውልደቱን አሳውቀ ማለት ነው።ኦሃዮ ቢል ኦሃዮ? ሲሉት አሜሪካ ማለቱ ስለማይቀር አስቀድሞ ትልቁን የማንነቱን መገለጫ ያስቀድማል።!ይሄን ማገናዘብ እንዴት ያቅተናል?!

ምሁራን ስለ ኢትዮጵያ ብዙ ብለዋል፤ አሁንም እኛ እራሳችንን ማወቅና በጥቃቅኑ ምክንያት፤ የሚያለያዩንና የሚያሳንሱን፣ የሚደስኩሩልንን እየተጋትን መደማመጥና ወደ ነበርንበት ትልቅነት መመለሻውን ማየት ተሳነን እንጂ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የባሕል ክምችት የሞላት ሀገር ናት። ይህንን ማወቅና ማመን፣ መለስ ብለን በቀና ልቡና መርምረን ያ ቢከብደን ተመራምረው እውነታውን ያሠፈሩልንን መቀበልና በዚያ ሕብር ሆነን መኩራት እንዴት ያቅተናል?

ለውጥማ ....ኢትዮጵያ ሙዚቃን፣ ሥነ ሥእልን ቅርፅን ለሌላው ዓለም ያስተማረችና ያካፈለች ሃገር መሆኗን፤ ኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ተስማምተው ተግባብተው ተፋቅረው የኖሩባት ሃገር መሆኗን አምነን መቀበል እንዴት ያቅተናል?።

ለውጥማ አዎን አለ፤በቅርቡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ላይ በደረሰው አደጋ ኢትዮጵያዊያንና የተለያዩ ሃገራት ዜጎች ሕይወታቸው አልፏል፤ በዚያም ዓለም ከዳር እስከዳር በደረሰው ሕልፈት አዝኗል፤ ሃዘኑንም ገልያአል። ይህ መጥፎ አጋጣሚ የሁላችንንም ቅስም ሰብሯል፣ ሁሉም ነፍስ ይማር ብሏል። ►

ከጥቂት ቀናት በሁዋላ ግን የመንደሩና የአካባቢው ነዋሪ ያለውን ይዞ፣ የአቅሙን በመቸር አደጋው በተፈፀመበት ሥፍራ ተሰባስቦ የሁሉንም ሟቾች 12 በጠበል ጠዲቅ ፍትሃት አካሂደዋል። ይህን ሲያደርጉ ግን በአንደበታቸውም እንደገለፁት ለሁሉም የአደጋው ሠለባዎች ሰው በመሆናቸው ያደረጉት እንጂ በዘር፣ በብሔር ለይተው አይደለም።ከዚህስ መማር እንዴት ያቅተናል?

## ለውጥማ አለ፤

“ወደ ቤታቸው ሊሄዱ እንጂ መች እንዲህ እማያቁት መንደር ይህ ያጋጥመናል ብለው አሰቡ” ብለው ለማያውቋቸው እራሳቸውን ይዘው እንደ ቤተሰብ አለቀሱላቸው።ሃዘን ተቀመጡላቸው። ቀኑን ቆጥረው አሰቧቸው። ሰው መሆናቸው ከምንም በላይ ነውና ነው፤ በአደጋው የተቀጠፉትን በአንድነት የዘከሩላቸውና ያነቡላቸው። ይህ ነው ኢትዮጵያዊነት፤ ይህ ነው ሰውን በሰውነቱ እንድንመለከተው የሚያደርገን የኢትዮጵያዊነታችን ባህል። ይህን ማገናዘብና ማጣፊያ ባጣ፤ ጊዜው ባለፈበት፣ የሥልጣን ጥም ባናወዛቸው ብቃቱና ቀናነት በጎደላቸው ፖለቲከኛ በሚል አንገት ልብስ ተጠርንፈው ጥላቻን በሚሰብኩ እየተታለልን ያለነው። ይህን መገንዘብ እንዴት ያቅተናል?

## ለውጥማ አለ

ግራ የገባቸው ግራዎች “በአፍ መፍቻ ቋንቋ ብቻ ተናገሩ፣ ተማሩ፣ ተነጋገዱ፣ ቋንቋችሁን ካላወቁ አትግዙት፣ አትሽጡለት” በማለት እነሱ የማያደርጉትን የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ይነዛሉ። ይህን ይበሉ መርዛቸውን ይርጩ እንጂ፤ የነሱማ ልጆች በሃገርም ውስጥ ውድ በተባሉ ት/ቤቶች፣ አልያም ባሕር ማዶ ነው የሚማሩት። ይህ ደግሞ ምስኪኑን ወጣት ከነሱ ልጆች በታች ሆኖ እንዲኖር ያቀዱት መሆኑን መገንዘብ እንዴት ያቅተናል?

## ለውጥማ አዎን አለ

ልጆቻቸውንስ ውጪ ሃገር ልከው ለማስተማርም ሆነ በሃገር ውስጥ በውድ የግል ት/ቤቶች ለማስተማር፤ ውድና ውብ የሆነ ቪላ ባለቤት ለመሆን፣ በውድ ዋጋ የተገዛ ዘመነኛ መኪናስ ለመግዛት ገንዘቡ ከየት ተገኘ? ብለን መጠየቅ መመርመርስ እንዴት ያቅተናል?!

የተወረወረልንን ሁሉ ተቀብለን ከማቀበል በፊት ማን ወረወረው?ለምን ወረወረው? ከየት አግኝቶት? ብለን መመርመር እና አጥርተን ለማወቅ ትእግስቱና ብልሃቱ እንዴት ይጠፋናል?

ይቺ ኢትዮጵያችን እኛ የፈጠርናት፣ የትላንት ሳትሆን ከኛ በጣም ቀድማ የነበረች፣ አሁንም ያለች እኛም ካለፍን በኋላ ለተከታዩ ትውልድ የምትኖር ነችና ክፉ ሳይነካት ከትውልድ ወደ ትውልድ ደግማ ደጋግማ እንድትተላለፍ የፈጠራትና እኛንም የፈጠረን እግዚአብሄር ይጠብቃት ዘንድ በነጋ በጠባ ምኞታችን፤ ልመናችን ይሄው ይሁን። ኢትዮጵያችን ታፍራና ተከብራ ለዘልዓለም ትኑርልን።

የጠላት ይጠላ!!!



ኢዮብ ሳለሞት

# ስርአተ - አልበኞችን ማን ያስታግሳቸዉ !

በርካታ ትውልዶች የመሰእዋትነት ፍሬ ተሻግራ እዚህ የደረሰችውን የታሪክ፤የባህል፤የተፈጥሮ ሃብታም ሀገር ሲሆን ሲሆን እሴት ጨምረን፤ አቅሟን ተጠቅመን ለዜጎች ምቹ የአኗኗር ዘይቤ ፈጥረን ለሚቀጥለው ትውልድ ማሻገር፤ማቀበል ሲገባን ቀጥታ በእልህና ማንአለብኝነት ጠርዝና-ጠርዝ እየተጓተትን ማንም አሸናፊ የማይሆንበትን ይልቁንም ዙሪያችንን ከበው ለሚያንጃብቡ ጆፌ አሞራዎች ታሪካዊ ጠላቶቻችን ሀገራችንንና ህዝቦቻችንን አሳልፎ ለመስጠት እየተሽቀዳደምን እንገኛለን።

አለም አሁን የያዝነው የቁልቁለት ሩጫ መጨረሻው ርሃብና፤እርዛት ፤ስደት፤መፈናቀል እንደሆነ የተለያየ ገጾቹን እየገለጠ የመንን፤ሶርያን፤ደቡብ ሱዳንን ፤ሊቢያን ቢያስነብበንም ምን አይነት ድንዛዜ ውስጥ እንደገባን በማይታወቅበት ሁኔታ ዛሬም ሀገርን ለማፍረስና ለዘመናት በአብሮነት ተገምደው የቆዩትን እሴቶች ለመናድ የማንቆፍረው ድንጋይ የለም ። በአራቱም አቅጣጫዎች ሰርአተ-አልበኞችና ጽንፈኞች የመንግስትን አስተዳደራዊ መዋቅር እንዳሻቸው እየናዱና እየፈነጩ የማህረሰቡን ህይወት እያመሱ የሚገኙበት ወቅት ላይ ደርሰናል ።

መንግሰት፡- በህዘብ ዘንድ ተአማኒነትና ቅቡልነት ባገኘ ምርጫ ተመረጠም ይሁን በአጋጠሚ አንዴ የአስተዳደር መዋቅሩን እመራለሁ ብሎ ተረክቧልና የህዘብን ህይወትና ደህንነት ከስረአተ-አልበኞች መታደግ ይገባዋል ። ጋቢ ለብሶ የሀዘን መግለጫ ከማዥጎድጎድ ፤ አስቀድሞ የስጋት ቀጠናዎችን በመለየት የቅደመ-መከላከል ስልቶችን ቀይሶ ህብረተሰቡን በማሳተፍ ሴራዎችን ማክሸፍ ፤ጉዳቶችን መቀነስ ፤አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት የህዘብን ህይወት መታደግ ሲገባው ከንፈር መምጠጥ ስራው ከሆነ የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም ማለት ይሆናል ። የመከላከያ ሃይል ፤የፌደራል ፖሊስ ሃይል ፤ የክልል ልዩ ሃይል እያለ ስርአተ-አልበኞች አፍንጫቸው ስር ዶልተው ፤ተደራጅተው ፤ታጥቀው ሀገር ሲያምሱ ፈጣን ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ በአንድም በሌላ መልኩ የድርጊቱ ተካፋይ ከመሆን ተነጥሎ አይታይምና መንገስት የፍትህ ተቋማት ውስጥ የተሰገሰጉትን አድርባዮች፤ጽንፈኞችና ስረአተ-አልበኞች መንጠሮ ያውጣ። ከሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች የተውጣጡ የአካባቢያቸውን ሰላምና ደህንነት ከመንግስት ጋር በቅንጅት የሚያረጋግጡ ህዝባዊ ጓድ አዋቅሮ የህዝብን ህይወት ይታደግ።

የሃይማኖት ተቋማት ፤- ሀገሪቱ በጠባብ ፖለቲከኞች እንደቆዳ ተወጥራ ለህልውናዋ አስጊ ደረጃ ስትደርስ ከዚያ ሁሉ የእምነት ተቋም፤አማኝ ፤ተከታይ አንድ ጸሎቱ ሰማያትን ቀዶ በፈጣሪ ዘንድ ተሰምቶ አልቂት፤ጥፋት የሚያስቀር አንድ ሰው ይጥፋ? ቅዳሴው ፤አዛኑ ፤ስብከቱ ለብዙ ዘመናት አልተቋረጠም፤ ምነዉ ፍሬ ጠፋ???? ጥንት ነብያት አስቀደመው በመተንበይ ህዝብን ከርሃብ ታድገዋል ፤ የተፈጥሮ ኡደትን በማዘዝ ጸሃይን በማቆም ድልን አውጀዋል ፤ ነገስታትን ገስጸው ሰርአት አስይዘዋል ፤ ከፈጣሪ ጋር በመሟገት ፤ በመደራደር ይህን ህዝብ ከምታጠፋ እኛን ከህይወት መዝገብ ደምስሰን እስከማለት የደረሰ ህዝባዊ ውግንና ነበራቸው። አሁን ማህበረሰባችን እንዲህ ባለ አሳዛኝ ምስቅልቅል ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ እሱን ታግሶ ነገ ያልፍልኛል ቢልም ዛሬ በህይወቱ የሚወራረዱ ስርአተ-አልበኞች ሲነግሱበት ምነው ደምጻችሁ ጠፋ?? አስተምረን ፤ገስጸን ሰማያዊውን አለም እናወርሳለን የምትሉት ምእመን ዛሬ የምድሩን እንኳን በአግባቡ መኖር አቅቶታል። አንዴ ከተቋዋሚ አንዴ ከገዢዉ ጋር ተጣብቃችሁ በጥቅስ ከምትጠዛጠዙ ፤የአዞ እንባ ከምታነቡ የቄሳርን ለቄሳር ሰጥታችሁ ተጠሪነታችሁ ለምእመናኑ፤ለተከታዩ፤ለአማኙ ብቻ መሆን አለበት ።

የከፍተኛ-ትምህርት ተቋማት ፤- ህብረተሰቡ ካለው ውስን ጥሪት እየቆጠበ ያጋጠመውን ተግዳሮት በሳይንሳዊ ዘዴ ፤በጥናትና ምርምር ውጤቶች፤ በቴክኖሎጂ ትከሻውን ያጎበጡትን ፈተናዎች ማቅለል ሲገባቸው በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆነው ተገኝተዋል። ትላንት ህዝባዊ ውገና ተይዞ አቋም የሚንጸባረቁባቸው (ህዝባዊ-መንገስት ይቋቋም ፤ መሬት ላራሹ ፤ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ..ወ.ዘ.ተ ) ቦታዎች ዛሬ በግለኝነት በናወዙ አጀንዳዎች ተውጠዋል፡ ፡ የዳቦና የሩዝ መጠን አነሰብኝ ፤ እገሌ ነገድ ይውጣ ፤ ..ወ.ዘ.ተ በችግር-ፈቺ አመለካከቶች ፈንታ የዘረኝነት፤የጥላቻ ፤የጎሰኝነት መናኸርያ ሆነዋል። በአራቱም አቅጣጫዎች በግጭት በሚናጡ ስፍራዎች አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ይገኛል፤ ውሱን ለማርገብ ምን ሰራሁ ብሎ የሚጠይቅበት ወቅት ላይ እንገኛለን።

ሰፊው-ህዝብ ፡- ትላንት ሀገርን ለማስቀጠል የሚያስችሉ ብቁ ተቋማት በሌሉበት ከጽንፈኞች ፤ከጠባብ ፖለቲከኞች ጋር ግብግብ ፈጥረህ ፤አብሮነትህን አስቀጥለህ፤ አፍራሽ ቅስቀሳዎችን ጆሮ ዳባ ብለህ በእሴቶችህ ላይ የሚያላግጡትን ጥራዝ-ነጠቅ ሊሂቃንን ቸል ብለህ አንድነትህን አስቀጥለሃል ምስጋና ይገባሃል፡ ፡ እንደተጋትከው መርዘኛ ቅስቀሳ፤ በየቀኑ ጉያህ ውስጥ ገብተው ተፈጥሮአዊ በሆነዉ ቋንቋ፤ባህል፤እምነትህ፤ነገድህ እንደሚጎነትሉህ ቢሆን ውጤቱ ሌላ ነበር። ዛሬም፤ነገም ሀገርን እንደሀገር የማስቀጠል ሃላፊነት ተትከሻህ ላይ ወድቋልና ሳትሸበር፤ሳትደናገጥ አብሮነትህን አጥብቀህ ያዝ !!

# ኑ መንግስትን እና የሕግ የበላይነትን እንፈልግ !



ገበያው ይታየው

በአንድ ሃገር ህግ እና መንግስት እጅግ ተፈላጊ አካላት ናቸው:: ተፈላጊ አካል ደግሞ በፈላጊ አካላት ይፈለጋል:: አንድ ነገር የሚፈለገው አንድም አስፈላጊነቱ የታመነ እና መገኘት ያለበት ነገር ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ አስፈላጊ መሆኑ ታይቶ የተረጋገጠ ነገር ግን የጠፋ ነገር ሲሆን ነው:: አንድ ነገር የሚፈለገው እጅግ አደገኛ እና እጅግ ጎጅ ሆኖ ሲገኝ ነው:: ይህም እጅግ ጎጅ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር በጎጅ ድርጊቱ ተጠቃሚ ሊሆን ስለሚገባ በሰራው ጎጂ ድርጊት ሃላፊነት እና ቅጣት ሊጣልበት ስለሚገባ ይፈለጋል:: አሁን ላይ ሀገራችን እጅግ አብዝታ የምትፈልገው ታይቶ የጠፋ መንግስት የሚባል የሀገር ጠባቂ የዜጎች መከታ የሆነን አካል ነው:: አበው በስነ-ቃላቸው “ገድሎ ማዳን እና አድኖ መግደል” የሚባል ቅኒያዊ አባባሎች አሏቸው::

ገድሎ ማዳን ማለት መጀመሪያ ጎድቶ ወይም አሉታዊ ነገር ወይም ድርጊት አድርጎ በኂላ በአወንታዊ አስተሳሰብ እና ድርጊት መደምደም ወይም መካስ ነው:: ይህ መዳረሻው ደስታ ነው::

በሌላ በኩል አድኖ መግደል ማለት ደግሞ መጀመሪያ ደስታ ሰጭ ድርጊቶች እና ሃሳቦች አድርጎ እና አሳይቶ በኂላ በሚያሳዝን ሃሳብ እና ድርጊት መደምደም ነው:: ይህ ሃሳብ መዳረሻው ሃዘን ነው::ይህ ሃሳብ “መጨረሻዬን አሳምረው” የሚለውን የሀገሬ ሰው ተማጽኖ እንዳልተሰማ ማስቀጠሪያ መንገድ ነው::

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ከመጋቢት 24-2010 ዓ.ም ጀምሮ የፖለቲካ እና የህሊና እስረኞች ሲፈቱ የተወሰኑት አምባገነኖች አድራጊ ፈጣሪነታቸው ሊያበቃ የደረሰ በመሰለ ጊዜ “ፈጣሪ ያህችን ሀገር ሊጎበኛት ነው” የሚሉ ሃሳቦች በአብዛኛው ህዝብ በኩል ይሰማ ነበር:: በዚህም ምክንያት አብዛኛው ህዝብ በደስታ መንግስትን ደግፏል:: መንግስት ለአቅመ መንግስት ይበቃል የሚለው የህዝቡ የተማጽኖ ቃል እየደበዘዘ የዜጎች መፈናቀል፤የደቦ ፍርድ መበራከት፤ “በአካባቢዬ አትምጡብኝ” የሚል ቡድን መብዛት፤ያልተገባውን የመፈለግ እና አሁን ደግሞ የታጠቀ ቡድን ከተማን መውረር ጀመረ:: እነዚህን የመሳሰሉት ሁኔታዎች የሀገራችን ፈተናዎች መሆናቸው ቀጠለ:: በዚህም የተነሳ የሀገራችን ተስፋ ሲደበዝዝ “የተሰለፍኩበትን እግሬን በቆረጠው” የሚል ሃሳብ በህዝቡ በኩል ጎልቶ እየወጣ ነው:: ሕዝቡም የመከዳት ስሜት እየተሰማው ነው:: ይህ ድርጊት አድኖ መግደል የሚለውን ዘይቤ የሚመሳሰል ነው::

የዚህ ሁሉ ድርጊት እና ሁኔታ መገለጫው በሀገራችን የህግ የበላይነት ሳይሆን የጉልበት የበላይነት መስፈን፤ ህግን የሚያስከብር መንግስትም መጥፋት ነው::

መንግስት መንግስት የሚሆነው መንግስታዊ እሳቤ ህዝባዊ መሰረት ሲኖረው ነው:: ይህ የሚሆነው እና እንዲሆን መለኪያ መስፈርቱ ዋናው ምሰሶ የህግ የበላይነት ነው:: የህግ የበላይነት ሲባል አንድ ሀገር በህግ አውጭ በኩል ያወጣችው ህጎች በአስፈጻሚው የመንግስት አካል ሲተገበሩ ነው:: የህግ የበላይነት ሁሉም ዜጎች እና ሕዝቦች ለአንድ ሀገር ህግ መከበር የግል እና የቡድን ድርሻቸውን ግዴታቸውን መወጣት ሲችሉ ነው:: የህግ የበላይነት ትግበራ በዜጎች መካከል እኩልነት ሲረጋገጥ (Assurance of rule of law)፤መንግስት የዜጎችን መብት ሲያከብር (Respecting the rights of the people) መከበሩንም ዜጎች በእለት ትእለት ኑሯቸው በተግባር ሲመሰክሩ፤መንግስት የህዝቦችን መብት ሲከላከል (Assuring obligation of protecting)፤እንዲሁም መብቶችን የማስተዋወቅ እና የማበረታታት ግዴታ(Obligation of promotion and promoting) መሰረታዊ የመንግስታት ግዴታዎች ናቸው::

አሁን ላይ በሃገራችን ህግ የሚያስከብር፤ በመብታቸው ለተጎዱ ዜጎች ከላላ የሚሆን መንግስት እና ግዴታውን የማይወጣ የቡድን እንቅስቃሴ እድገታቸው ተቃራኒ ሆኗል:: መንግስት አይደለም ህግ ሊያከብር እና ህግ ሊያስከብር እራሱ የዜጎችን መብት እየጣሰ ሌላ መንግስት የሚጠብቅ እየመሰለ ነው:: መንግስትን በባትሪ መፈለግ ሳንጀምር መንግስት መንግስት እንዲሆን እንፈልጋለን:: በሌላ በኩል የህገ-ወጥ ቡድኖች ጡንቻ እየጨመረ፤የፈለጋቸውን ነገር ካለ ማንም ከልካይ ሲያደርጉ፤ህዝብ ሲያሣቅቁ፤ሀገር ሲያማቅቁ እየታዩ ነኪ የሌላቸው ሆነዋል:: በዚህም ምክንያት በዚህ ከቀጠልን መንግስት አዘቅዝቆ ያድጋል፤ አምባገነን ቡድን አሽቅቦ ያድጋል::

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው የሀገራችን የህግ የበላይነት መተግበር ፈተና የስም ማጥፋት እና የጥላቻ ንግግር ነው:: በአብዛኛው በፖለቲካው ዙሪያ የሚንቀሰቀሰው የህብረተሰብ ክፍል ፓርቲ መስርቶ፤ አመራር ወይም የድርጅት አባል ሆኖ እንኳ የድርጅቱን ተልዕኮ እየፈጸመ ያለው ድርጅቱ ሌሎችን ፓርቲዎች ሊበልጥ የሚችልበትን የፖለቲካ ርዕዮት ዓለም በመንደፍ ሳይሆን ሌላውን የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲውን አመራር በመሳደብና በማንቋሸሽ ነው:: ብሔርተኛው የዜግነት ፖለቲካ አራማጁን የዜግነት ፖለቲካ አራማጁ ብሔርተኛ ድርጅቶችን እና አመራሮቻቸውን በመስደብ እና በማንቋሸሽ ማንም ብቻውን የማይሸነፍበት ትግል ላይ ነን:: ይህ ፖለቲካችን በሃሳብ የበላይነት ሳይሆን በጉልበት የበላይነት እንዲኮሰምን የሚያደርግ የቁልቁለት መንገድ ነው የተያያዝነው:: አሁን ባለው ሁኔታ የሀገራችንን ህልቁ መሳፍርት ችግሮች ብንዘረዝር አንጨርሳቸውም:: ስለሆነም ካለንበት የችግር አዙሪት ለመውጣት ምን እንስራ “ከማን ምን ይጠበቃል” የሚሉትን እንመልከት

1ኛ. መንግስት የህግ የበላይነትን እንዲያስከብር እንተባበር:: አብዛኞቻችን አሁን ላይ የሀገራችንን ችግሮች ለመፍታት አማራጭ የፖለቲካ ፓርቲ መስርተን ሌላ የተሻለ መንግስት ብንመሰርት የተሻለ ይሆናል ብለን ልናምን እንችላልን:: ይህ አንዱ የመፍትሔ አካል ቢሆንም ቀዳሚው መፍትሔ ግን አይደለም:: ቀዳሚው መፍትሔያችን ሊሆን የሚችለው መንግስት የህግ የበላይነት እንዲያስከብር አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደር አለብን:: የሚከበር ህግ እና ህግ የሚያስከብር መንግስት ከሌለ ህዝብ አይኖርም:: ሀገርም አይኖርም::

2ኛ. ሁሉም ህዝብ ለህግ የበላይነት መከበር ያለ የሌለውን አማራጭ ሊወጣ ይገባል:: የኢትዮጵያ ታሪክ ወደ ኂላ ዞረን ስንመለከት በ2ኛው የጣሊያን ወረራ ጊዜ ቀዳማዊ ሃይለስላሴ ወደ አውሮፓ ሲሰደዱ ህዝብ እራሱንም ሀገርንም እየመራ በተጨማሪም ቂም ይዞ የመጣን የጣሊያንን መንግስት እና ወታደር በአርበኝነት ተፋልሟል:: ሀገሩንም ነጻ አውጥቷል:: ይህ የማንም ታሪክ አይደለም:: የሁላችንም ኢትዮጵያዊያን አባቶች እና እናቶች ታሪክ ነው:: ዛሬ ላይ ዘመኑን ሊመጥን የሚችል መከባበር፤መቻቻል የሰፈነበት፤በቡድን ስሜት የመመራት ድርጊቱ ሊያመጣው የሚችለውን አሉታዊ ውጤት በመገንዘብ ሁላችንም ህግን አክብረን፤ከቻልን አስከብረን ሀገራችንን እንጠብቅ::

3ኛ. የፖለቲካ ፓርቲዎች:: በአሁኑ ሰአት የኢትዮጵን ችግር ለመረዳት ሰው ሆኖ መገኘት ብቻ በቂ ነው:: ኢትዮጵያ ብዙ ህጎች አሏት:: ህጎቹ ሁላችንንም ላያስማሙ ይችላሉ:: ህግ በባህርዩ የብዙሃን ውሳኔ እንጂ የሁሉም የጋራ ስሜት የሚንጻባረቅበት አይደለም:: ህግ የሚከበረው በእያንዳንዳችን መለኪያ ህጋዊ ህግ ሆኖ ሲገኝ ብቻ አይደለም:: ህገ-ወጥ የመሰለን ህግም በህግ አግባብ እስከሚሻሻል ድረስ የሚከበር ህግ መሆኑን መርሳት የለብንም:: ሕግን ልናሻሽል የምንችለው አንድም የህግ የበላይነት የተከበረባት ሀገር፤ የህግ የበላይነትን የሚያከብር የፓርቲ አመራር፤ አባል እና ደጋፊ ማፍራት ስንችል ነው:: ይህ ሲሆን በህጋዊ መንገድ ለምርጫ ተወዳድረን በህዝብ ምርጫ አሸናፊ ሆነን ስንገኝ በምንመሰርተው የህግ አውጭ አማካኝነት በህጉ መሰረት ሲሻሻል ነው:: በሌላ በኩል በለስ ጥሎን ሳናሸንፍ ብንቀር እንኳ መንግስት ከሚመሰርተው ፓርቲ ጋር በሀገር ጉዳይ በመወያየት አሳማኝ የመከራከሪያ እና አዋጭ የሆኑ የወደፊት ትልሞችን በመንገር እንዲያስተካክል በማድረግ ነው:: ከዚያ ውጭ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፤አመራሮቻቸው እና ደጋፊዎቻቸው የጠሉትን ህግ አናከብርም እያሉ የሀገራችንን ፍጥጫ ሊያባብሱ አይገባም:: ስለዚህ ኑ መንግስትን እንቀስቅስ የህግ የበላይነትን እናክብር::

# “የህዳሴውን ግድብ ...

ከገጽ 10 የዞረ

**ከመስራትዎ ባሻገር፤ የጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ የኢኮኖሚ አማካሪ ኮሚቴ አባል ነበሩ፡፡ ለመሆኑ ሕወሓቶች እርስዎ በደርግ ዘመን የነበርዎትን የሥራ ድርሻ እያወቁ ለእዛ ኃላፊነት እንዴት መረጡዎት?**

ኢ/ር አበበ፡- ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ በስራ ላይ እያለሁ ለአማካሪነት የተለያዩ ሰዎች ከየመ/ቤቱ ተመረጡ፡፡ እኔ ከመ/ቤቴ፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ፣ ከግብርና ሚኒስቴር አንድ አንድ ሰው ተደርጎ ከመንግስት ስድስት ሰዎች፤ የግሉ ኢኮኖሚ ተወካይ በሚል አቶ ሮቤርቶ ያኮና የሚባሉ ጣልያናዊ፣ በአጠቃላይ ሰባት ሰዎች ነበርን የጠ/ሚኒስትሩ የኢኮኖሚ አማካሪ የሆንነው፡፡ የእዚህ ኮሚቴ ሰብሳቢ ደግሞ አቶ መለስ ዜናዊ ነበሩ፡፡

የኮሚቴያችን ፀሐፊ የነበረውና በኋላ የፕሬይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ኃላፊ ሆኖ ተሹሞ የሄደው አቶ አሰፋ አብርሃ (የስዬ አብርሃ ወንድም) ነበር፡፡ በኋላ በእሱ አቶ በየነ የኮሚቴው ፀሀፊ ሆኖ ተመርጦ ነበር፣ እርሱም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የፕራይቬታይዜሽን ዋና ኃላፊ ሆኖ ተቀየረ፡፡ የጠ/ሚ/ሩ አማካሪ ኮሚቴ አባል የሆንኩት ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮሚሽን እያለሁ ነው፡፡ በኋላ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ተብሏል፡፡ የብረታ ብረት ኮርፖሬሽንን ጨምሮ አንድ ላይ አጠቃሎ የዋጠ ትልቅ ድርጅት ስለነበር ነው ስያሜው የተቀየረው፡፡

በጊዜው ሀሳባችን ምን ነበር? ይሄ አሁን ሜቴክ የሆነው “ደጀን” ፕሮጀክት ለታንክ ጥገና ያዘጋጀነው ነበር፡፡ አሁን “የመከላከያ ኮሌጅ” የሚሉት ሁሉ መጀመሪያ ያቋቋምነው እኛ ነን፤ በደርግ ጊዜ ነው የተጀመረው፡፡ ምክንያቱም ራሱን ችሎ ከፍተኛ ተቋም እንዲሆን የታሰበ ነበር፡፡ ግን መከላከያ አምራችም፣ ተጠቃሚም እንዳይሆን ተደርጎ ነበር፡፡ በፊት የነበሩት ሰዎች አዋቂዎች ናቸውና የሲቪል መ/ቤቱ ያመርትለታል፣ ያንን ምርት ገዢ ነበር መከላከያ፤ የተጠና አካሄድ ነበር በፊት የሚከተለው፡፡

**ግዮን፡- ደርግ በመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪው አማካይነት ካቋቋማቸው በርካታ ድርጅቶች መሀል አምቦ የሚገኘው ግዙፉ “ሆርማት” ብዙ ዕቅድ ተነድፎለት የተገነባ፣ ግን የታለመው ነገር እውን ሳይሆንለት የቀረ ድርጅት ነው ይባላል፡፡**

ኢ/ር አበበ፡- ትክክል ነው፡፡ ሆርማት ብዙ ዕቅድ ነበረው፡፡ ሆርማት የአውሮፕላን ቦንብ ሁሉ እንዲያመርት ጥናቱን ጨርሰን ነበር፤ ኢትዮጵያ ራሷን እንድትችልና ካስፈለገም ለሌሎች የምትሸጥበት ሁኔታ እንዲፈጠር ታስቦ የተደራጀ መ/ቤት ነበር፡፡ ዲስቶሮትድ የሆነ ኢንፎርሜሽን ይደርሳቸው ስለነበር በአሜሪካኖች በኩል “ኬሚካል ዋርፌር” የሚያመርት አደገኛ ተቋም ነው ተብሎ በደርግ ላይ አደገኛ ችግር ከፈጠሩ ነገሮች መሀል አንዱ የሆርማት ፕሮጀክት ነው፡፡

ግን ሆርማት አሜሪካኖቹ እንደጠረጠሩት ዓይነት አልነበረም፡፡ እኛ እንደውም በኋላ ላይ ስንመካከርና ምን እናድርገው? በሚል ስንነጋገር ትልልቅ የጥይት ቀልሃ የሚያመርተውን የቡታጋዝ ሲሊንደር እንዲያመርት ዲዛይን አድርገነው ነበር፡፡ ድስት መሰል አንዳንድ የሲቪል ዕቃዎችን እንዲያመርት፣ ሁለገብ እንዲሆን አስበን ነበር፡፡ ሲሊንደር ከውጭ ነበር የሚመጣው፡፡ ኢህአዴግም ከደርግ የባሰ ጦረኛ ስለሆነ “የጦር መሳሪያ እንዲያመርት ነው የምንፈልገው” በማለቱ የታሰበው ሁለገብነት መና ቀረ፡፡

ይሄ ግዙፍ ተቋም የታሰበውን ያህል ላለመስራቱ ብዙ ችግር ነበረው፡፡ መጀመሪያ ሆርማት መሀል አገር ላይ የተቋቋመ ፋብሪካ ነው፡፡ አንዳንድ ማሽኖችን ነቅሎ ወደ ሌላ ቦታ የመውሰድ ፍላጎትና እንቅስቃሴ ሁሉ ነበር፤ ያንን ተቃውመናል፡፡ እዚሁ እንዳለ መስራት ይቻላል የሚል አቋም ይዣለሁ፡፡ አስታውሳለሁ አንድ ጊዜ አቶ ወንድወሰን ከበደ የሚባል ም/የገንዘብ ሚኒስትር ነበር፤ በበጀት ጉዳይ ለመነጋገር ስሄድ “አንተ የደርግ ፋብሪካ ለማቋቋም ነው የምትፈልገው” አለኝ፡፡ “እንዴ ደርግ እኮ አሁን የለም፤ የኢህአዴግ ፋብሪካ፣ የሀገር ፋብሪካ ነው፤ ይሄንንም አታውቅም እንዴ?” በሚል ተጣልተን ጠ/ሚኒስትሩ ድረስ ጉዳያችን ሄደ፡፡

በጊዜው ጠ/ሚኒስትር ለነበሩት ለአቶ ታምራት ላይኔ “ይሄ አስተሳሰብ ልክ አይደለም፡፡ ፋብሪካው የደርግ አይደለም፤ የሀገር ሀብት ነው” ብዬ አስረድቻለሁ፡፡ የሚገርመው ሰራተኞችን አላባረርክም ተብዬም ተከስሻለሁ፡፡ 179 ኢንጂነሮችና ቴክኒሽያኖች ናቸው ያሉት፤ እነዚህን ባለሙያዎች “ፋብሪካው ከስሯል፣ እየሰራ ስላልሆነ አባር” ሲሉኝ እኔ ደግሞ “አላባርርም፡፡ አንድ መ/ቤት ከስሯል የሚባለው የግል ድርጅት ሲሆን ነው፡፡ ይሄ የመንግስት ተቋም፣ ሰራተኞቹም የCPA ሠራተኞች ነው፡፡ የCPA ሠራተኛ ከስሯል ተብሎ ሊባረር የሚችለው መንግስት ከስሬያለሁ ሲል ነው፤ መንግስት በዚህ መንገድ በግልፅ ከስሬያለሁ ብሎ ሲናገር ብቻ ነው የማባርረው፡፡” በሚል ተከራከርን፤ በኋላ ግን ኢህአዴጎችም ፕሮጀክቱን ስለፈለጉት፣ እኔም በኃላፊነቴ እንድቀጥል አደረጉ፡፡

**ግዮን፡- የህዳሴው ግድብ ግንባታን ተከትሎ ከጅምሩ “ግድቡ የሚሰራበት ቦታ ትክክል አይደለም፣ ሌላ አማራጭ አለ” በሚል ሀሳብ ከመስጠት ባሻገር የግንባታውን ሂደት ተቃውመው ነበር ይባላል፡፡ እውነት ነው?**

ኢ/ር አበበ፡- ግድብ መሰራቱን አይደለም የተቃወምኩት፤ ሀሳቡን እደግፋለሁ፣ አበረታታለሁ፣ ሀገራዊ ጥቅሙ የጎላ ነውና፡፡ ሆኖም ግድቡ አሁን የተሰራበት ቦታ ትክክል አይደለም፡፡ መሀል ሀገር ላይ ጎጃም ውስጥ፣ በአነስተኛ ወጪ ሊቋቋም ይችል እንደነበር ሀሳቤን በጊዜው በተደረገ ስብሰባ ላይ ገልጫለሁ፡፡ ይህን ያልኩት ከተጨባጭ እውነታ በመነሳት ነው፤ በመሀል ሀገር አካባቢ በርካታ ጎርጆች አሉ፡፡

አሜሪካን ሀገር ኢንጂነሪንግ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ወስደው መጀመሪያ ላይ ያሳዩን ላስቬጋስ አካባቢ ያላቸውን አንድ ትልቅ ግድብ ነው፡፡ እሱ ጎርጅ ላይ ነው የተሰራው፡፡ “ግራንድ ካኔን” የሚባለው ይህን ግድብ፣ ከእኛ ባነሱ ጎርጆች ውስጥ ነው የሰሩት፡፡ የግራንድ ካኔን ግድብ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሜጋ ዋት ያመነጫል፡፡ እኛ አምስት ሺጎ ሜጋ ዋት ለማመንጨት ነው እየሰራን ያለነው፡፡ አምስት ሺጎ ሜጋ ዋት ለማመንጨት የጣናን ሁለት ጊዜ ውሃ የሚይዝ ግድብ መገደብ አያስፈልግም፡፡

በርግጥ ይሄ ጥናት የኢህአዴግ አይደለም፡፡ ደርግም አጥንቶት በአነስተኛ ደረጃ፣ በጣና በለስ እንዲካሄድ ብሎ ነበር፡፡ በጃንሆይ ጊዜ የተጠና ጥናት አሁን ስራ ላይ እንዲውል የተደረገው፡፡ በጃንሆይ ጊዜ ግን አላማ ነበረው፣ ያኔ እንግሊዞችና አሜሪካኖች ስለነበር ያጠኑት ሱዳንና ግብፅን ጭምር እንዲያገለግል ተብሎ የታቀደ ጥናት ነው፡፡ አሁን ግን ጥቅሙ ለኢትዮጵያ ብቻ ነው ከተባለ ግንባታው ስህተት አለው፤ ጣና ከባህርዳር እስከ ጎርጎራ 92 ኪሜ ነው፤ ያን ያህል ኪሎ ሜትር ደለል ለማውጣት የኢትዮጵያ አቅም አይፈቅድም፡፡ ግንባታው እውን እንዲሆን ደለሉን ማስወገድ ግድ ስለሚሆን፣ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ያልተፈለገና ከአቅማቸው በላይ የሆነ ጫና ውስጥ ይወድቃሉ፡፡

ጎርጆችና ብዙ ደለል በሌለበት በመሀል ሀገር እንዳይሰራ የተፈለገበት ምክንያት ምን እንደሆነ ባይገባኝም፤ በተለይ ቀደምት የኢህአዴግ ሹማምንት ይህን አማራጭ የገፉበት የራሳቸው የሆነ ፖለቲካዊ ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል ብዬ እገምታለሁ፡፡ ያም ሆን ይህ ግድቡ አገነባብ ላይ ቅሬታና ጥያቄ ቢኖረኝም፤ የሀገር ሀብት ከመሆኑ አኳያ ከጅምሩ አንስቶ እስካሁን ድረስ ያለማቋረጥ በመግዛት የዜግነት ግዴታዬን እየተወጣሁ ነው፡፡ ወደ ፊትም አጠናክሬ እቀጥልበታለሁ፡፡

**ግዮን፡- “የእንቦጭ አረም” የበላይ ጠባቂ እንደመሆንዎ መጠን አሁን ይህ ጉዳይ ከምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

ኢ/ር አበበ፡- ሲጀመር እምቦጭ በመንግስት የአስተዳደር ድክመት የመጣ ችግር እንጂ የኢትዮጵያና የዓለም ህዝብ ችግር ሆኖ መታየት የለበትም፡፡ ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ ለሀገራቸውና ለወገናቸው የሚጨነቁ፣ ትኩረት የሚሰጡ አመራሮች ቢኖሩን ፤ያለንን ንብረትና ውሃ በትንሽ ገንዘብ፣ በተለይም በሰው ሀይል (በህዝብ ጉልበት) በማስተባበር ችግሩ እንደተከሰተ ወዲያውኑ ማስወገድ የሚቻልበት ዕድል ነበር፡፡

አሁን እኛ እያደረግን ያለነው ይህንኑ ነው፤ ህዝብን በማስተባበር ውጤታማ ስራ ሰርተናል፣ እየሰራንም ነው፡፡ በነገራችን ላይ እምቦጭ የሀገሪቱ ጠቅላላ ችግር በዛ መልክ የዘቀጠ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ከዛ ውጭ ጉዳዩ እንኳን በፌደራል መንግስት ደረጃ ቀርቶ፣ አንድ ካምፓኒ ሊያስወግደው የሚችለው ነገር ነበር፡፡ ግን ማን አሳቢና ተቆርቋሪ ይሁን? አሳሳቢው ነገር ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ወደፊት እምቦጭ ለህዳሴው ግድብም አስጊ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ከወዲሁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

# ጠንቋይና ሐይማኖተኛ ፖለቲከኛ ሊሆኑ አይችሉም

በአለማችን አድገው ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሱ የሁሉንም አገሮች ታሪክ ብናጠና የዕድገታቸው ዋናው ምክንያት ለሣይንስ የሰጡት የተጋነነ ትኩረት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የእነዚህ አገሮችን ታሪክ በዝርዝር ስንመለከት እድገትን ለማምጣት በዋናነት ከሣይንስ ጋር የሚፃረሩ ሐይማኖታዊ ሕጎችን ለመዋጋት ከፍተኛ ስራ መሥራታቸውን ነው፡፡ ጎጂ የሆኑ ባህላዊ ዕምነቶችን መዋጋት እጅግ ፈታኝ ተግባር ቢሆንም ብዙ አገሮች ይህንን ተግባር በተሳካ ሁኔታ በማካሄዳቸው አገራቸውን ወደ ከፍተኛ የስልጣኔ ደረጃ በማድረስ ለአገራቸው ባለውለታ ሆነዋል፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን አብዮት ለማካሄድ ጉዞ ከጀመርን ከአርባ አመታት በላይ ቢሆነንም ውጤታማ በሆነና አገራችንን ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚችል መልኩ ውጤት ማስመዝገብ አልቻልንም፤ ለዚህ ነው የድህነት አዙሪት በአገራችን ሊቆም ያልቻለው፡፡

በጥንቆላ የሚያምኑ ሠዎችም ያለባቸው ችግር ይወገዳል የሚል እምነት ስላላቸው ከፍተኛ ገንዘብና ሐብታቸውን እየገበሩ ወደ አስከፊ ድህነት ይሄዳሉ እንጂ ምንም ዓይነት የተሻለ ነገር አያገኙም፡፡

ሐይማኖታዊ እምነትም ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ሳይንስ ካስቀመጠው የእድገት መስመር በተለየ መልኩ ችግሮች ይወገዳሉ ብለው የሚያምኑ በመሆኑ እንዲህ አይነት ሠዎች በምንም መልኩ ፖለቲካ የደረሰበት ቦታ መድረስ የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም ፖለቲካ መቶ በመቶ ሳይንስ በመሆኑና ፖለቲከኛ የአንድን አገር ሕልውና መለወጥ የሚችለው ሳይንስን መሠረት አድርጎ በመሆኑ የጥንቆላና የሐይማኖት አማኝ የሆነ ሰው በምንም መልኩ የሕዝብ አስተዳዳሪ መሆን አይችልም፡፡

ሐይማኖት የማንኛውም ዜጋ መብት ቢሆንም ይህንን መብት ማንኛውም ሠው መጠቀም የሚችለው በራሱ መንገድ ብቻ ነው፡፡ በዜጎች ላይ በአገር ዕድገት ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር በሚችል መልኩ በምንም መንገድ ተፈፃሚ መሆን የለበትም፡፡

እኔ በዚህ አጭር ፅሁፍ ሁሉንም መተንተን ባልችልም በሐይማኖታዊ ሕጎችና በሳይንስ መካከል ያሉ በሺ የሚቆጠሩ ሕጎችን መጥቀስ ምንም አያዳግትም በመሆኑም እነዚህን ተፃራሪ አስተሳሰቦች ይዞ ፖለቲከኛ ሊሆን አይችልም፡፡


ሐይማኖት ደግሞ ባመዛኙ ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ብሎ የሚታመንበት አስተሳሰብ በመሆኑ በርካታ ሐይማኖተኞች ሐይማኖታቸውን የሚያመልኩት ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት ነው፡፡

ይህ አስተሳሰብ በምንም መልኩ በሳይንስ ቦታ የለውም፡፡ ሳይንስ ምድራዊ ሕይወታችንን በተቻለ መጠን የበለፀገ እንዲሆንና ተፈጥሮን በተሻለ መልኩ መቆጣጠር እንድንችል የሚረዳን መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሐይማኖተኛ ሠው የፖለቲካ ሳይንቲስት ሊሆን አይችልም፡፡

ለምሣሌ አንድ በጥንቆላ የሚያምን ሰው አንድ ችግር ሲገጥመው የእንስሳ ደም በማፍሰስ በአንድ ዴሞክራሲን አላማ አድርጎ የሚንቀሳቀስ አገር የዜጎችን የአስተሳሰብ መብት ማክበር ግዴታ ቢሆንም ሕዝብን የሚያስተዳድር ግለሰብ ግን አስተሳሰቡን አጥርቶ ማንነቱ በማያሻማ መልኩ አሳውቆ መገኘት አለበት፡፡

አንድ ግለሰብ እነዚህን ሶስት የተለያየ ጽንፍ የረገጡ አስተሳሰቦች አቀላቅሎ ሊሄድ አይችልም፤ ለመሄድ ቢሞክርም ለራሱም ለአገሩም ምንም ውጤት ሊያመጣ አይችልም፡
፡

አገራቸውን የሚወዱ መሪዎች በአገራቸው ሕዝቦችና በሌላ አገር ሕዝቦች ሳይቀር እጅግ ዘግናኝ ድርጊት ፈፅመው ለአገራቸው ታሪክ የሰሩ መሪዎች አሉ፡፡ ለምሣሌ በቻይና የባሕል አብዮት ዘመን ሐይማኖታዊ አስተሳሰብን ለማጥፋት ሲባል ወደ 40 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡




ያ ችግር ይወገዳል ብሎ ያምናል፤ ይህንን ግን በምንም መልኩ በሣይንስ ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በመሆኑም እነዚህ በዚህ ፅሁፍ ርዕስ ላይ የጠቀስኩት ሶስቱ አስተሳሰቦች የተለያየ ጽንፍ የያዙ በመሆናቸው ሶስቱንም ወይም ሁለቱን አስተሳሰቦች በአንድ ላይ ማስተናገድ አይቻልም፡፡

አንዳንድ መሪዎች ደግሞ ሌሎች አገር በመሄድ የሌላ አገር ዜጎችን ለባርነት ለጭቆና ዳርገው አገራቸውን ወደ ላቀ ደረጃ አድርሰዋል፡፡ አሜሪካና ሶቭየት ሕብረት ሁለተኛውን አለም ጦርነት ሊያሸንፉ ሲቃረቡ ሁለቱ አገሮች ትኩረታቸውን አድርገው የተንቀሳቀሱት የጀርመንን የጦር ወንጀለኞች ►

ለማሳደድ ሣይሆን የጀርመንን ሳይንቲስቶችና በየመዝገብ ቤቱ የተከማቹ የጥናትና የምርምር ውጤቶችን በማደን ወደ የአገራቸው በማጋዝ ነበር፡፡ ይህ ተግባራቸው ባሁኑ ወቅት ለፈጠሩት ታላቅነት ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

እዚህ ላይ ልንገነዘነበው የሚገባ ቁምነገር አንድ አገር በከፍተኛ ፍጥነት ለማደግ የራስዋን ሳይንቲስት ብቻ ሳይሆን የሌላ አገር ሳይንቲስት ለማግኘት እንኳን ምን ያህል ተግታ መሥራት እንዳለባት ነው፡፡

እኛ የምናውቃቸው ከኃይለ ሥላሴ እስከ ዶ/ር ዐቢይ ያሉ መሪዎች እንኳን የውጭ ተወላጅ ሳይንቲስት ይቅርና ያገራቸውን ሳይንቲስቶች ከሰው ቆጥረዋቸው አያውቁም፤ የሚቀናቸው ልመናና ወደ ውጭ የሰው ሀብት ላይ ማንጋጠጥ ነው፡፡

ያገራችንን እጅግ በርካታ አቅም አሟጦ መጠቀም ይቅርና በዝቀተኛ ደረጃ እንኳን በአገራችን አቅም ለመንቀሳቀስ (ለመጠቀም የሚደረገው የመንግስት ጥረት እጅግ የሚያሳዝን ነው፡፡

ይባስ ተብሎ ያላቸው የጀርባ ማንነት ሳይጠና በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎች ሁሉ ለከፍተኛ ሹመት እንደሚታጩ ለመታዘብ ችለናል፡፡ ይህ ምን ያህል ዝርክርክነት እንዳለ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየን በጠቅላይ ሚንስትር ጽህፈት ቤት በአገሪቱ ያሉ ታላላቅ ምሁራንን እንኳን የያዘ ሰነድ አለመኖሩን ነው፡፡

በማንኛውም የስራ ዘርፍ ትክክለኛውን ሰው ለትክክኛ ቦታ መመደብ ካልተቻለ፤ ያ ዘርፍ ምንም አትራፊ ቢሆን ተገቢውን ሰው ማግኘት ካልቻለ ምንም ውጤት ማየት አይቻልም፡፡ በተለይ አገራችን በከፍተኛ የእዳ ጫና ላይ ባለችበት ወቅት ከዚህ አስከፊ ሁኔታ ለመውጣት ያለንን አቅም አሟጠን በተገቢው ፍጥነት መጓዝ ካልቻልን ድሕነትን ልንዋጋ ቀርቶ ወደ አስከፊ ባርነት ውስጥ ነው የምንገባው፡፡

እነ ናይጄሪያ በድሕነት የሚኖሩት ሐብት አጥተው ሳይሆን ሐብታቸውን በአግባቡ እና ብቃት ባለው ሰው ማስተዳደር ባለመቻላቸው ነው፡፡ እኛ ከታሪክ የምንማረው መቼ ነው? ለምንድነው ታሪካዊ ስሕተት የምንደግመው? ብዙ አገሮች ብዙ መስዋዕትነት ከፍለው ያለፏቸውን ስህተቶች እኛ በጠራራ ፀሐይ እየደገምናቸው ነው፡፡

ብዙ ፀሐፊያን ኢትዮጵያ ታላቅ መሪ እንዳገኘች በአድናቆት ሲፅፉ ለማንበብ ችያለሁ፤ እኔ ግን በእርግጠኝነት መናገር የምፈልገው አሁንም ከሕወሓት ዘመን በባሰ መልኩ ወደ ገደል እየገባን ነው፡፡

ሕወሓቶች የሚዘርፏትን አገር እንደ አገር ለማቆየት ብዙ ስራ ሰርተዋል፡፡ አሁን ያለው አመራር ርዕዮቱ፣ አላማው፣ እቅዱ፣ ምንም የታወቀ ነገር የለውም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዶ/ር ዐቢይ መንግስት ዛሬ ይህን ይሰራል፣ ነገ ያንን፣ ከነወዲያ ያንን ይሰራል ተብሎ የተነገረው ነገር የለም፡፡ ሕዝብ ደግሞ የመንግስትን ፖሊሲ አውቆና ተገንዝቦ ለውጤታማነቱ አብሮ መሥራት ካልቻለ ውጤት ማየት አይቻልም፤ የአገር ልማት በመሪና በተመሪ የጋራ ድካም ብቻ የሚፈጠር ውጤት ነው፡፡

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ያለፈው ሥርዓት የተወሰኑ ባለስልጣናት ተወገዱ እንጂ የሥርዓቱ ችግሮች ከነ ሰንኮፋቸው ተወግደው ማየት አልተቻለም፡፡ በተለይ ወሳኝ ስልጣን ያላቸው የመካከለኛና ዝቅተኛ ባለስልጣናት አሁንም ቦታቸው ላይ ናቸው፡፡ በሕዝቡ ላይም ዋነኛ ምሬት ሲፈጥሩ የነበሩት ሐይሎች እነዚሁ መካከለኛና ዝቅተኛ ባለስልጣናት ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የሚያስፈልጋት አብዮተኛ፣ ነጋዴ፣ ሳይንቲስት ብዙ ከመናገር ይልቅ ብዙ ማዳመጥን የሚመርጥ ጥበበኛ መሪ ነው፡፡ እንግሊዞች አለምን ወረው ባህላቸውንና ቋንቋቸውን ማስፋፋት የቻሉት በዋናነት የነጋዴ ባህርይ ስለነበራቸው ነው፡፡ የእንግሊዝ ሳይንቲስቶችን ብናያቸው ምንም እንኳን እንደ ሪቻርድ ዳርዊን የመሣሠሉ በሰው ዘር አመጣጥ ላይ ብዙ የተጠበቡ ሣይንቲስቶች ቢኖሩዋቸውም እነ ጀምስ ዋት፣ አሌክሳንደር ግራሐም፣ አይዛክ ኒውተንን የመሣሠሉ የነጋዴዎችን ሥራ ለማቀላጠፍ የተጠበቡ በርካታ ሳይንቲስቶችን አፍርተዋል፡፡

በአጠቃላይ በፍልስፍና ብዙ መጠበብ ይቻላል፤ ዋናው ነገር ግን ሐብት መፍጠር የሚያስችል መንገድ የመረጠ መሪ ብቻ ነው አገሩን ከድህነት አውጥቶ ወደ ላቀ ቦታ ማድረስ የቻለው፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን ባለፉት 27 ዓመታት ስናስተናግደው የነበረ የዘውግ ፖለቲካ ለድህነት እንጅ ሐብት ለመፍጠር ምንም የጠቀመን ነገር የለም፡፡ አንድ ጉዳይ ደግሞ ለዚህ ያህል ረጅም አመት ያለ ውጤት ይዞ መጓዝ በጣም ያሳዝናል፡፡

> እነ ናይጄሪያ በድሕነት የሚኖሩት ሐብት አጥተው ሳይሆን ሐብታቸውን በአግባቡ እና ብቃት ባለው ሰው ማስተዳደር ባለመቻላቸው ነው፡፡ እኛ ከታሪክ የምንማረው መቼ ነው? ለምንድነው ታሪካዊ ስሕተት የምንደግመው? ብዙ አገሮች ብዙ መስዋዕትነት ከፍለው ያለፏቸውን ስህተቶች እኛ በጠራራ ፀሐይ እየደገምናቸው ነው

ዶ/ር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ሲመጡ ከፍተኛ የሚባል ሕዝባዊ ወኔ የተላበሰ መነቃቃት ተፈጥሮ ነበር፤ ነገር ግን አሁን ሁሉም ነገር እየደበዘዘ ተስፋ ወደ መቁረጡ እያዘነበለ ነው፡፡ ዶ/ሩ ያንን ሕዝባዊ መነሣሣት ፈጣን እርምጃዎችን በተከታታይ ለመውሰድ እንደ ግብዓት መጠቀም ይችሉ ነበር፡፡ በአለም ላይ የተካሄዱ ሁሉም አብዮቶች ከፍተኛ የሚባል ሕዝባዊ አቅምን ተጠቅመው ነው ወደ ውጤት የደረሱት፤ የለዘዘና የተለሳለሰ አካሄድ ሕዝብን ያስኮርፋል፡፡

ወደተነሳሁበት ዋናው ርዕስ ልመለስና ጥንቆላ በተለይ ባላደጉ አገሮች የብዙ ዜጎችን አእምሮ መቆጣጣር የቻለና አገሮች ደግሞ እያደጉ ሲሄዱና የትምህርት ተደራሽነት እየሰፋ ሲሄድ ተቀባይነቱ በዚያው ልክ እየደበዘዘ ነው የሄደው፡፡

ሐይማኖት ደግሞ አሁን በለፀጉ በሚባሉ አገሮች ውስጥም ያለ ቢሆንም ተቀባይነቱ በተለይ በአዲሱ ትውልድ በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሰ ለመሄዱ ብዙ መመራመር አያስፈልግም፡፡ እኔ በተማርኩበት የቀድሞዋ ምስራቅ ጀርመን የዕምነት ተቋማት ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ የበአላት ማድመቂያ ብቻና አንዳንዶቹ ደግሞ እጅግ ተውበው የተሰሩ በመሆናቸው እንደ ሙዚየም ብቻ ነበር ሲያገለግሉ የነበረው፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን ወደ ሥልጣኔ ጉዞ ያልጀመርን መሆኑ አንድ ማሳያ አሁንም ለእምነት ተቋማት ከአቅማችን በላይ ገንዘብ እያወጣን በመገንባት ላይ እንገኛለን፤ በተጨማሪም ከፍተኛ የመሬት ብክነት እየፈጠርን ነው፡፡ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለዕምነት ተቋማት የዋለው የመሬት ይዞታ ለትምህርት ተቋማት ከዋለው ይዞታ ጋር ሲነፃፀር ለእምነት ተቋማት ሥራ ላይ የዋለው ቦታ በእጅጉ ይበልጣል፡፡ አዲሱ ትውልድ ቪላ ቤት ውስጥ እጅግ ተጣበው ነው የሚማሩት ይህ ደግሞ የሚቀጥለው አገር ተረካቢ ትውልድ ሊኖረው የሚገባን ማንነት ላይ እጅግ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ ላገሩ የሚቆረቆር መሪ በዋናነት ተግቶ መሥራት ያለበት በሚቀጥለው ትውልድ ላይ ነው፡፡

በተጨማሪም ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ የእምነት ተቋማት ከፍተኛ የሚባል የድምፅ ብክለት በመፍጠር ዜጎች በሰላም ተኝተው እንዳያድሩ በማድረግ በተለይ ደግሞ ቱሪስቶች በየሆቴሉ ፀጥታ አግኝተው ቱሪዝም እንዳያድግ ከፍተና እንቅፋት እየሆኑ ነው፡፡ ዶ/ር አቢይ ይችን እንኳን የደምፅ ብክለትን በማስቀረት ቢተባበሩን ባለውለታችን ይሆኑ ነበር፡፡ በባዶ ሜዳ የበጎ አድራጎት ተግባር በመስራት ደግ ሰው ለመመስሰል ወይም መመፃደቅ ምንም አገራዊ ፋይዳ የለውም፡፡ ለአገር ብልፅግና ለትውልድ የሚያበረክተው ምንም ፋይዳ የለም፡፡ ጥንቁልና እና ሐይማኖታዊ አስተሳሰብ በምንም መልኩ ቤተ መንግስት መግባት የለበትም፤ የኋላ ቀርነት ምልክት ነው፤ እኛ ኢትዮጵያውያን የምንፈልገው ሳይንቲስት መሪ ነው፡፡

# ዳግም ጥሪ ከጌዴዖ

## <<ፓርክ ውስጥ እንዳለ እንስሳ ነው የጎበኙን >>

የጌድኦ ተወላጆች አሁንም ጩኸታችንን የሚሰማን አላገኘንም፡፡ ችግሮቻችንም እየተባባሱ መጥተዋል፤ በተደጋገሚ ያቀረብነውም ጥያቄ ተቀባይነት ከማጣቱ ባሻገር በየዕለቱ ህፃናት ልጆቻችንና አቅመ ደካሞች በሞት እየተለዩን ነው ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት የወገን ድረሱልን ጥሪ መልዕክታቸው ላይ ተናግረዋል፡፡

በጉጂ ኦሮሞዎች ጠያቂነትና ፀብ አጫሪነት ከመሬታችን ልቀቁ የተባሉትና የተለያየ በደል የደረሰባቸው የጌዶኦ ዞን ነዋሪዎች ላለፉት ሦስት ወራት ከይዞታቸው ተፈናቅለው እጅግ አስከፊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ ከዚህ ቀደም በወጡ ህትመቶቻችን ላይ ማስነበባችን ይታወሳል፡፡ ይህው ችግር መፍትሄ ከማግኘት ይልቅ ወደተባባሰ ደረጃ እንደደረሰና የተፈናቃዮችም ቁጥር ከ600 ሺ በላይ እንደሆነ መንግስት አሳውቋል፡፡

በቂ መጠለያ፣ የምግብና የህክምና አቅርቦት ባለመኖሩም ተፈናቃዮቹ በየዕለቱ በበሽታ ከመጠቃታቸው ባሻገር በተለይ ህፃናት ሁኔታውን መቋቋም ባለመቻላቸው ህይወታቸው እየተቀጠፈ ነው ሲሉ የችግሩ ተቋዳሽ የሆኑት የጌዶኦ ነዋሪዎች ይገልፃሉ፡፡

‹‹የዝናቡ ሁኔታ በጣም እየከፋ በመምጣቱ ከዚህ በኋላ በጤናና በተስፋ እንቆያለን ማለት ያስቸግራል፤ ህፃናትና አረጋውያን የሚላስና የሚቀመስ ከማጣታቸው በተጨማሪ በቂ የሆነ ከዝናብ የሚያስጥል ሸራ እንኳን ማግኘት ባለመቻሉ ችግሩን መቋቋም አቅቶናል›› የሚሉት ተፈናቃዮች ለጥያቄያችን መልስ ይሰጡናል ብለን ያሰብናቸውና ከመንግስት ተወክለው ወደ እኛ የመጡት ሠዎች (ባለስልጣናት) በፓርክ ውስጥ እንዳለ ብርቅ እንስሳ ጎብኝተው ከመመለስ ያለፈ ነገር ሊያደርጉልን አልቻሉም ብለዋል፡፡

‹‹ጥያቄዎቻችንን ይመለከታቸዋል ለምንላቸው የክልልና የዞን አስተዳደሮች ያቀረብን ቢሆንም ያለውን ሁኔታ ከማስተባበል ውጭ የዕለት ደራሽ ዕርዳታ የምናገኝበትን ዘዴ ለመፍጠርና እኛን ለመርዳት ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ በተለይ ጉዳዩ ይመለከተዋል ለሚባለው ለአደጋና ሥጋት ዝግጁነት መ/ቤት እንኳ ከአምስት ጊዜ በላይ የድረሱልን ጥሪ አሰምተን ምላሽ ግን ተነፍገናል፡፡” ሲሉም ያብራራሉ፡፡

በተጨማሪም አሁን ተጠልለውበት ባለው ጣቢያ ውስጥ በቂ የሚባል ህክምና ማግኘት እንዳልቻሉ የሚናገሩት ተፈናቃዮች ‹‹ እየታመመ ያለው ሠውና የህክምና አቅርቦቱ ፈፅሞ የማይመጣጠን በመሆኑ ከሞት ሊታደገን አልቻለም፤ የተሻለ ህክምና ካልተገኘም የወገኖቻችን እልቂት አሠቃቂ ይሆናል›› በማለት ያክሉበታል፡፡ በመጠለያነት የተሰጣቸው ቦታ ብቻ ሳይሆን



አሁን በተፈጠረው የሞት መደራረብ የተነሳ የቀብር ቦታም እንደጠበባቸው በከፍተኛ ሰቆቃ ይናገራሉ፡፡

በኦሮምያ ክልል ሀላፊዎች ይህ የመፈናቀል አደጋ የተከሠተው በማህበራዊ ድረ-ገፅ በተበተኑ የሀሠት ፕሮፓጋንዳዎች ነው፤ ጨርሶም ተፈናቃይ የሚባል ነገር የለም እየተባለ የሚነገርለት ይህ አሳዛኝ ክስተት በእርግጥም የመንግስት ዓይንና ልብን ሊስብ ያልቻለበት ሁኔታ አስገራሚ ሆኖ አልፏል፡፡

‹‹ለመንግስት ማቅረብና መጠየቅ ያለብንን ሁሉ አድርገናል፤ ከዚህ በኋላ ወዴት አቤት ማለት እንዳለብን አናውቅም›› የሚሉት ተፈናቃዮች ከመንግስት አካላት ይልቅ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎችና በውጭ የሚኖሩ በጎ አድራጊዎች ዕርዳታና ድጋፍ ህይወታችንን ለማቆየት ብንችልም ለዘለቄታው ግን ያለው የህልውናችን ጉዳይ አጠያያቂ ሆኗል በማለት ይናገራሉ፡፡

ሌላው ቀርቶ በበጎ አድራጊዎች በችሮታ የተሰጡን ከዝናምና ከፀሐይ የምንጠለልባቸውን ሸራዎች እንኳ እየተቀማንና እየተዘረፍን ሲሆን፤ ተዉ የሚል ከልካይና ተከላካይ ማግኘት አልቻልንም፤ አሁንም ትንኮሳና ዛቻው እንዲሁም ማስፈራሪያው አልቀዘቀዘም በማለት የሚከተለውን ያክሉበታል፡፡

‹‹የሠፈርንበት ቦታ እጅጉን ረግራጋማና በምንጭ የተሞላ አካባቢ በመሆኑ ከስርም ከላይም በውሃ ተከበን ነው ያለነው፡፡ ይሄ ደግሞ የበለጠ ህፃናትንና አቅመ ደካሞችን ጉዳት ላይ እያጣላቸው ነው፤ በዚሁ ከቀጠልን ደግሞ የሁላችንም ህይወት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡››


ይህንን የመፈናቀል ችግር ገሚሱ የለም አልተደረገም እያለ ሲሞግት፤ ገሚሱ ደግሞ መፍትሄ ለመስጠትም የተንቀሳቀሰበት ሁኔታ እንደነበረ የታዘብን ሲሆን፤ የሁለቱም ብሄር የክልል መንግስታትና የሁለቱም ብሄር የአገር ሽማግሌዎችና አባ ገዳዎች በባህላቸው መሠረት በጎንደሮ ሥርዓት አቅጣጫዎች በማስቀመጥ ችግሩን ለመፍታት የተደረገው ጥረት ሁሉ ገደል እንደገባና አሁን ጉዳዩ ወደላይ ከመሄድና መፍትሄ ከማግኘት ይልቅ እዚያው ተድበስብሶ መቅረቱንና ተስፋ መቁረጣቸውን የሚናገሩት ተፈናቃዮች የፌደራል መንግስት ጉዳዩን ትኩረት ሠጥቶ በመከታተል በሌሎች ቦታዎች እንደተደረገው ሁሉ ወደቀዬአችንን መመለስ እስክንችል ድረስ የተሻለ መጠለያ፣ ምግብና ህክምና እንዲሁም አልባሳት የምናገኝበትን ሁኔታ ሊያመቻችልን ይገባል ብለዋል፡፡

‹‹እኛ ጌዶኦዎች ከጉጂ ኦሮሞዎች ጋር ለበርካታ አመታት በአንድነት የኖርን፤ በክፉ በደግም ያልተለያየን እንደነበርን ይታወቃል፡፡ አሁን የተከሰተው መፈናቀል ምክንያቱ ስር የሰደደ የዘረኝነት መንፈስ የተጠናወታቸው የኦሮምያ ክልል የበታች ባለስልጣናት የሚያደርጉት ክፉ ድርጊት ነው፡፡ ይህንንም አሁንም ድረስ ያለዕፍረት ቀጥለውበታል›› ሲሉ ይወቅሳሉ፡፡

በማን አለብኝነት ስሜት ስለተፈጠረ ወንጀልም እንዲህ ሲሉ ያብራራሉ ‹‹ለግልና ለቤተሰብ ጉዳይ ወደ ቀርጫ ከተማ የተጓዘውና በምግብ ቤት በመመገብ ላይ የነበረውን የጌዶኦ ተወላጅ አቶ ገመቹ ሆሮን የጉጂ ኦሮሞ ተወላጅ የሆነ ግለሰብ ወደተቀመጠበት በመሄድ “ከዚህ በፊት ዘጠኝ ገድያለሁ፤ አንተ ደግሞ አስረኛ ትሆናለህ” በማለት በጩቤ እንደወጋውና ተጎጂው አሁን ድረስ በሆስፒታል ተኝቶ ህክምና እየተደረገለት መሆኑን በቁጭት ተናግረዋል፡፡

ከመፈናቀልና ከእንግልቱ ባሻገር እየተደረገብን ያለው ትንኮሳ ሊቆም ካልቻለ ኢትዮጵያዊ ነን ብለን ለመናገር የምንችልበት አንደበት የለንም፡፡ ቢቻል ለሁሉም ነገር መፍትሄ ተፈልጎለት ወደ ቀዬአችን የምንመለስበት ወይም ባለንበት ቦታ ደህንነታችን የሚጠበቅበትን መንገድ መንግስት ማመቻቸት አለበት ሲሉም በድጋሚ አሳስበዋል፡፡

# ከፖለቲካው በፊት ሠላም ይቅደም



ከሸዋፈራሁ ኩራቱ ዶ/ር
አሜሪካ

## የኢትዮጵያ ህግና– ፍትህ

ኢትዮጵያ አገራችን የብዙ ወለፈንዲዎች (Paradoxes) አገር ናት:: ከእነዚህ ወለፈንዲዎችም አንዱ ፍትህና ህግ በኢትዮጵያ ያላቸው ቦታ ነው:: የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ በፊት እንደ ገለጽኩት በአንድ በኩል ህግ አክባሪ ነው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፍትህ የተነፈገ ሕዝብ ነው:: እንዴት ፍትህ የተነፈገ ሕዝብ ህግ አክባሪ ይሆናል? ይህ ለመረዳት የሚቸግር ወለፈንዲ ነው:: ለኢትዮጵያዊያን በህግ-አምላክ ማለት ትልቅ ትርጉም ያለው ሀረግ ነው:: ከዚህ ፅሑፌ በፊት ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ህግ አክባሪነት፣ ለህግ ያላቸውንም ቦታ ገልጨዋለሁ:: ህግን ከአምላክ ጋር ጨምሮ የሚያከብር አገር ህዝብ በአለም ላይ የለም:: የህግ አምላክ ማክበር ከአምላክ ጋር እኩል ነበር:: የህግ አምላክ ማክበር ተገዥዎችን በህጉ ተፈፃሚነት ላይ እምነት እንዲኖር ያደርጋል:: የመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉትም ቢሆኑ ለህግና ለዳኝነት ስልጣን አክብሮት እንዲሰጡ የህግ አምላክ በትንሹም ቢሆን ያገለግል ነበር:: ከእውነተኛ ፍትህ አኳያ ሲታይ የቀድሞ ሥርዓቶች ጉድለት ቢኖራቸውም የፍርድ ቤት ሥነ-ሥርዓትና የፍርድ ችሎትን መዘባበቻ አላደረጉም:: ምክንያቱም ፍትህን ከመለኮታዊ ስልጣን ጋር ስለሚያያይዙ ነው::

ይህ እውነታ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍትህ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ እምነት እንዲኖረውና እንዲያድርበት አድርጓል::አንድ የተበደለ ሰው በአንድ ዳኛ ዘንድ ቀርቦ ተፈርዶበት እንደሆነ፣ በሚቀጥለዉ ደረጃ ላይ ያለው ዳኛ ዘንድ ፍትህን ፍለጋ ይጓዛል:: እዚያም ባይሆንለት ወደ ሚቀጥለው ይሄዳል:: በሶስተኛ ደረጃ ባይሳካለት ጠቅላይ ችሎት ንጉሠ-ነገሥቱ ዘንድ ይቀርባል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ እያለ ፍትህን ፍለጋ የሚተጋ ሕዝብ ነው:: እንደዚህ አይነት ባህል አሁን ላይ አይገኝም:: እንደዚህ አይነቱ በቀላሉ የሚገነባ ባህልና ህግ አክባሪነት ለወደፊቱም አናገኝም::

አሳዛኙ ጉዳይ በዚህ ህግ አክባሪ ሕዝብ አናት ላይ የቆናጠጡት ጨቋኝ ገዥዎች የሕዝቡን ህግ አክባሪነት በሚመጥን መጠን ህግን አክብረው የሚያስከብሩ አለመሆናቸው ነው:: በህግ አጠባበቅ ረገድ ኢትዮጵያ እየተጓዘችበት ያለው የቁልቁል ጉዞ አሳፋሪ ነው:: ኢትዮጵያ ከአንድ የገዥ መዳፍ ወደ ሌላው ገዥ በተሸጋገረች ቁጥር ፍትህ ከበፊቱ በባሰ እየተደፈጠጠ መቀጠሉ በአይናችን እያየነው ያለ ሃቅ ነው:: አንዳንድ ምሳሌ እንመልከት፡- በአጼ ኃይለ-ስላሴ ኢፍትሃዊነት ያስመረራቸው ወገኖች ሥርዓቱን ታገሉት፣ በትግሉ አሸንፎ የመጣው ግን ከበፊቱ የባሰው ደርግ ሆነ:: የደርግ ሥርዓት ያስመረራቸው ደግሞ ታገሉት፤ አሸንፎ የመጣው ግን ከደርግ የባሰው ወያኔ ሆነ:: አሁን ደግሞ ወያኔን በውስጡ ሆኖ የታገሉት የወያኔ ልጆችና አባሎቻቸው ዋና ዋና የጠገቡትን ወያኔዎችን ከሕዝብ ጋር ሆነው ታግለው ጣሉት:: እነዚህኞቹ ወያኔን ወደ ጥግ አስያዙ እንጂ ጨርሰው አላስወገዱትም:: አንዱ ሌላውን እስኪ ንካኝ እየተባባሉ፣ ፍትህ ወደየት እንደሚሄድ አልታወቀም::

ከማርክሳዊ - ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም መምጣት ጋር ፍትህ ከሰማየ ሰማያት ወርዳ መሬት ላይ ተፈጠፈጠች፡፡ ፍትህ ሰዎችን ሁሉ በእኩል ማየቷ ቀረና መደባዊ፣ ጎሳዊ፣ ዘውጋዊ ሆነች፡፡ በዚህ አዲሱ ዕይታ መሠረት የጭቁኑ መደብ ፍትህ እና የጨቋኙ መደብ ፍትህ ለየቅል ብቻ ሳይሆን ተቃራኒ ሆነው ተገኙ፡፡ ከወያኔ መምጣት ጋር ደግሞ ፍትህ መሬት ላይ መንደባለሏ በዝቶ ጉድጓድ ተቆፍሮ ጉድጓድ ውስጥ ተቀበረች . . .

በባለፈዉ ፅሑፌ ላይ የወርቃማውን የፍትህ ዘመን ጉዳይ አንስቼው ነበር:: ለጥቂቶቹ ወደ ሥልጣን ኮርቻ ላይ መፈናጠጥ ምክንያቱ የፀሐዩ መንግሥት ወርቃማ የፍትህ ዘመን ነው:: ለብዙዎቹ ቢጨልምም ለእነሱ ብርሃን ነው:: ለዚህ ነበር በስደት ላይ ሆኜ የአቶ መለስ ዜናዊን መንግሥት ‹በማፍያ ቡድንነትና በወንበዴ ድርጅትነት› በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን በአለም አቀፉ የህግ ባለሞያዎች ማህበር አማካይነት ለመጀመሪያ ጊዜ ጄኔቫ ባለው ቢሮ ክስ የመሰረትኩት:: ለክሱ መልስ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ይዞ የመጣው ደግሞ የቀድሞ ጓደኛዬ አሁን በሕይወት የሌለው የጊዜው ባለሥልጣን የዓቃቤ ህጉ ም/ሚኒስትር የነበረው አቶ መስፍን ግርማ ነበር:: ከአቶ መስፍን ጋር አብረው የመጡት የሶማሌው ተወላጅ በጊዜው በመሃል አውሮፓ ቤልጂየም የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ጴጥሮስ የሚባሉ ሰው ናቸው:: አቶ መስፍን በልቶ ያልጠገበ፣ ሥልጣኑንም በደምብ ያላጣጣመ፣ ከደደቢት ከመጡት የበለጠ ለደደቢት ልጆች ታማኝ ለመሆን በመሯሯጥ ላይ የነበረበት ጊዜ እንደነበረ

እረዳለሁ:: በጊዜዉ ምንም እንኳን እንደ መስፍን አይነቱን በመንግሥት ገንዘብና አቅም የተሞላውን ልኡክ መሟገት ቀላል ባይሆንም፣ በአለም አቀፉ የህግ ባለሞያዎች አስጨናቂ ክርክር (Argument) ተደርጎ ኮሚሽኑ ውሳኔውን በአድራሻችን እንደሚልክልን ተነገረን:: ከስድስት ወራት ጊዜ በኋላ በቃሉ መሰረት ኮሚሽኑ ውሳኔውን ልኮልኛል:: ውሳኔው የሚያስደስት ሳይሆን የሚያሳዝን ነበር:: ‹‹የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የሚሠራው ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ስለሆነ ግንኙነታችን ከግለሰብና ከድርጅት ጋር ሳይሆን ከመንግሥታት ጋር ነው:: ስለዚህ ችግር ቢኖር እንኳን ለመንግሥት እንዲያመለክቱ፤ ለዕውቀት ~~እንዲረዳ ይህንን የተባበሩት መንግሥታት~~ የሰብአዊ መብት ቻርተር መፅሐፍ አያይዘን ልከናል›› የሚል ነው:: አቶ መስፍን ግርማ ከክርክራችን መልስ ውጭ አግኝቶኝ አቶ ሸዋፈራሁ አንተ፣ ፕሮፌሰር አሥራት ወ/የስ እና ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት ብቻ ናችሁ የመንግሥትን ስም የምታጠፉት፤ የኢትዮጵያ

መንግሥት እንደሆነ አለም የሚያውቀው የለየለት ዲሞክራቲክ መንግሥት ነው:: ህግና ፍትህም እንደ ድሮ በድርጅት ትዕዛዝ የሚሠራ አይደለም:: በተለይ አንተ ገና ወጣት ነህ፤ ለምን ይህንን መንግሥት ትኮንናለህ? ብሎ ወቀሳ ሰንዝሮ ነበር:: አቶ መስፍን የአሰበ ተፈሪ ልጅ ነው:: አባቱ የቀድሞ ኮሎኔል ሲሆኑ እናቱ ወ/ሮ አሰገደች የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበር ሊ/መንበርና የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበሩና ታላቅ ሴት እንደነበሩ አስታውሳለሁ:: ስለነፍጠኛነት እሱ ከኔ ይቀድማል:: አብረውት የነበሩት አምባሳደር ጴጥሮስ ግን በትህትናና በዲፕሎማሲ አነጋገር እርስ በርሳችን መወነጃጀላችን አይጠቅምም፤ ከቻሉ እባክዎ ቢሮዬ እንሂድና እንወያይ፣ እርስዎንም ካገርዎ የሚያሸሽ ነገር የለም ብለውኝ ተለያየን:: ከብዙ አመታት በኋላ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት አግኝቻቸዋለሁ:: ወርቃማው የፍትህ ዘመን ከአገር አልፎ አለምን ሲያስጮኽ እንደነበረ እነሱም የሰሙት አሁን ነው::

ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ የፍትህ እሳቤያችን ራሱ እያሽቆለቆለ መምጣቱ ነው:: ቀደም ሲል ከላይ እንደተገለጸው ፍትህ መለኮታዊ ጸጋ ተደርጎ ይወሰድ ነበር፣ መቀመጫዋም ከአማልክት ጎን ነበር:: ለምሳሌ በህግ አምላክ ሲባልም የአማልክት መቀመጫ ነው ተብሎ ወደሚታሰበው ሰማይ እየታየ ነበር:: ከማርክሳዊ-ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም መምጣት ጋር ፍትህ ከሰማየ ሰማያት ወርዳ መሬት ላይ ተፈጠፈጠች:: ፍትህ ሰዎችን ሁሉ በእኩል ማየቷ ቀረና መደባዊ፣ ጎሳዊ፣ ዘውጋዊ ሆነች:: በዚህ አዲሱ ዕይታ መሠረት የጭቁኑ መደብ ፍትህ እና የጨቋኙ መደብ ፍትህ ለየቅል ብቻ ሳይሆን ተቃራኒ ሆነው ተገኙ:: ከወያኔ መምጣት ጋር ደግሞ ፍትህ መሬት ላይ መንደባለሏ በዝቶ ጉድጓድ ተቆፍሮ ጉድጓድ ውስጥ ተቀበረች:: በአዲሱ ወያኔ አመጣሽ ዕይታ እያንዳንዱ ዘር (ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ህዝብ) በየራሱ ጉድጓድ ውስጥ እየቆፈረ የቀበራት የየራሱ ፍትህ አለው:: ለምሳሌ የትግራይ ፍትህና የአማራው ፍትህ አይተዋወቁም:: የኦሮሞው፣ የወላይታው፣ የጉራጌው፣ የሶማሌው፣ የሲዳማው፣ የአፋሩ፣ የጋሞው፣ የካንባታው፣ ... እያንዳንዳቸዉ የየራሳቸው ፍትህ አላቸው:: በአንዱ ዘንድ ፍትሃዊ የሆነ ሌላው ጋር ኢፍትሃዊም ሊሆንም ላይሆንም ይችላል:: እንደመደብ ትንተና እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም:: በዚህም ምክንያት ነው ማኅበረሰባችን ብኽርታ በበዛበት ሁኔታ ላይ የሚገኘው:: በአንድ ቋንቋ እየተነጋገርን መስማማት የቸገረንም በዚህ የፍትህ እሳቤ መዛባት ጭምር ነው::

የአገር ጉዳይን ከግል ጉዳይ ጋር ማያያዝ፣ ግለሰባዊ አስተሳሰብን ወደ አገራዊ መንገድ ላይ ማምጣት ለራሱም ለአገርም አደጋ አለው:: አንዳንዶቹ ፖለቲካን ከቂምና ጥላቻ ጋር አያይዘው ይዋኛሉ:: ፖለቲካ ከግለሰብ ጥላቻ ጋር የተያያዘ ከሆነ ከጅምሩ መንገድ ላይ መቆም አለበት:: ግለሰብን የሚጠሉት ሰዎች ፖለቲካን መሥራት በፍፁም አይችሉም:: ምክንያቱም ድንገት ፖለቲካው ቢሳካና ሥልጣን ቢያገኙ የጠሉትን ዘውግ ለመግደል በልባቸዉ አስበው ስለሚሆን ነው:: ስለዚህ ፍትህን ከወዲሁ ለማጨለም የሚጓዡትን ህዝቡ በቶሎ የማን ወገን ነው? ከየት ነው የመጣው? የተመሰረተው መቼ ነው? ማን ይደግፈዋል? ምን ያህል አባል አለው? የሚለውን አስቀድሞ መነጋገርና ከመንገድ ላይ ማስቀረት፣ ወይም ማሳለፍ አለበት:: ያለበለዚያ ፍትህ እንደተቀበረ ይቀራል::

## ምልከታ አሁን–እና ለወደፊት

ይህ ሁሉ የሚያመለክተዉ (1) አገራችን የምትገኝበትን አሳሳቢ ደረጃ (2) እኛ (ማለትም በዚህ ዘመን ያለነው ኢትዮጵያዊያን) ላይ የወደቀውን የኃላፊነት ክብደት ነው:: ዜጎች ፍትህ የማግኘት ተስፋቸው ሲሟጠጥ በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ላይ የነበራቸው ተስፋ ይጨልማል:: ታግለን ሥርዓቱን ወደ መልካምነት ልንቀይረው እንችላለን የሚለው እምነት ካልዳበረ ለሀገር፣ ለወገን ለመጪው ትውልድ ይተዉትና እያንዳንዱ ሰው እኔ ምን አገባኝ፣ ምን አቀበጠኝ እያለ ጭቆናውን ችለው ለመኖር ሊመርጡ ይችላሉ:: ይህ እንዳይመጣ መወሰን ያለብን በየግላችን ነው:: ከፖለቲካው በፊት መቅደም ያለበት ጉዳይ አንፃራዊ ሰላም ነው:: ዲሞክራሲን የማይፈልግ የለም:: እንደ ኢትዮጵያ ባሉት አገራት ላይ ዲሞክራሲ ቢመጣ እንኳን ይፈርሳል:: ዲሞክራሲ ላይ ከመሥራት በፍትህና በሰላም ላይ መሠራት አለበት:: ሠላም የፍትህ አካል ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ የቆየና የተደበቀ በደል መኖሩን ሰዎች ይከድኑታል:: የተከደነውን እውነት አውጥቶ አክሞ ማዳንና በመጀመሪያ ዘላቂ ሰላም ማምጣት ለፍትህ፣ ለዲሞክራሲም ነፍስ ይሰጣል:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ በየጊዜው የሚተረከው ዲሞክራሲ ትውልድን ይገድላል እንጂ አያጸናም:: በነገራችን ላይ ዲሞክራሲ ማለት የምርጫ ሥርዓት ህግ ማለት ብቻ አይደለም:: በምርጫ ሥርዓት ህግ ውስጥ ያለው ጠንካራ እምነትና መብት ማለት ነው:: በእኛ አገር የተናጋው የሰላም መሠረት ነው:: የሠላም መሠረቱ ተናግቶ፣ የፍትህ መንገዱ ተዘግቶ፣ ዲሞክራሲን እናሳያለን ማለት ናፖሊዮን ከአውሮፓ እየተነሳ አፍሪካን እንደወረረ ይቆጠራል:: መልሶ ማፈግፈጉ አይቀርም:: ስለዚህ በሰላምና ዕርቅ ጉዳይ ላይ የመንግሥትም፣ የፖለቲካ ድርጅት አባልና መሪዎችም፣ በወንጀል የሚጠረጠሩ ግለሰቦችም መግባትና መሳተፍ የለበትም:: መንግሥት ድጋፍ ከማድረግ ዉጭ ሪፖርት መቀበል የለበትም:: ብሄራዊ ዕርቅና ሰላም በራሱ በጉዳዩ ባለቤት በሕዝብና በገለልተኛ ግለሰቦች ብቻ መካሄድ አለበት:: በዓለም ላይ የተሳካ ብሔራዊ ዕርቅና ሰላም የተካሄደባት አገር ሩዋንዳ ብቻ ነች:: ይሄም ሊሆን የቻለው በራሱ በህዝብና ከህዝቡ መካከል የተመረጡ ገለልተኛ ግለሰቦች እና የሞያ ድርጅቶች፣ ብቻ ዕርቁን ስላካሄዱት ነው:: በላይቤሪያ የተካሄደው፣ ሊካሄድ የተጀመረው የብሄራዊ ዕርቅ ኮሚሽን እስከ አሁን ድረስ እያወዛገበ ያለውና ተጀምሮ ያልተሳካው ኮሚሽኑ በመንግሥት የተሾመ መንግሥታዊ ብሄራዊ ዕርቅ ኮሚሽን ስለሆነ ነው::

የደቡብ አፍርካ የብሄራዊ ዕርቅና ሰላም ኮሚሽን በጊዜው በኔልሰን ማንዴላ ወደ ፊት ከመምጣት ጋር ተያይዞና ሊቀመንበሩም ዴዝሞን ቱቱ በመሆናቸው ሊሳካ ቢችልም ሙሉ በሙሉ የተሳካ ዕርቅ ግን አይደለም:: በፊት ከነበረው ይሻላል ቢባል እንጂ እውነተኛ የሰላም ዕርቅ አይደለም:: ስለዚህ 50% ተሳክቷል:: በእኛ አገር በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ከእነዚህ ከሶስቱ አንዱ ይሆናል:: በተለይም የላይቤሪያን አይነት ሁኔታ ይገጥመናል:: በዶ/ር አቢይ የተሾሙና የተመረጡት የኮሚሽኑ አባላት ራሳቸው ግማሹ በኮሚሽኑ በህግ የሚጠየቁ፣ በአብዛኛው ደግሞ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ናቸው:: ማን ማንን ይመረምራል? ማን ማንን ይጠይቃል? በህግ ከሚጠየቁት ውስጥ ራሱ አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት አንዱ ነው:: የቀድሞ የኢህአዴግ አባላትና መሪዎች በዚህ ኮሚሽን ውስጥ አሉ:: እነዚህ ግለሰቦችና ድርጅቶች በኮሚሽኑ ምርመራ ወቅት የሚጠየቁ የሚመረመሩ ናቸው:: እንዴት ሆኖ ብሄራዊ ዕርቅና ሰላም ይሆናል? (ዶ/ር አቢይ አህመድ ነገሮችን ያበረዱ እየመሰላቸው ብል ይቀላል) እንደዚህ አይነቱን እውነት እየጣሱ ከሄዱ ውድቀት ይቀድማቸዋል:: ስለዚህ ኮሚሽኑ ሥራ መጀመር የለበትም የሚል እምነት አለኝ::

ፍትህን ለማምጣት ከፍትህ ፊት የምንቆም ዜጎች እንዲህ አይነት ወሳኝ የግል ውሳኔ የምንሰጥ ከሆነ መሰባሰብና ተግባሮቻችንን ማቀናጀት ይኖርብናል:: እንዲህ ካደረግን በአገራችን የተንሰራፋውን ኢፍትሃዊነትን መዋጋት ቻልን ማለት ነው:: ለውጡን መደገፍ ተገቢ ነው:: ለውጡ የሚውጥ ማዕበል ከሆነ ግን መርከብ ማዘጋጀት የእኛ ድርሻ ነው:: ስለዚህ በለውጡ ሰበብ ዝም ተብሎ እሺ፣ እሺ ማለቱና ሌላው ቀርቶ የብሄራዊ ዕርቅና ሰላም ጉዳይ ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እየሄደ ዝም ብሎ መመልከቱ ሁሉንም የኢትዮጵያ ህዝብ ይጎዳል:: ምክንያቱን በደንብ ላረጋግጥ:: ሰላም የፍትህ አካል ነው:: ሞያንና ሞያተኛን ይፈልጋል:: ህግ፣ ፍትህ፣ ሰላም፣ የሰላም ሰዎች ይከበሩ:: ይህ ለውጥ እንዲመጣ ብዙ ዋጋ የከፍልን ሰዎች አለን፤ ሁሉም በየፊናው በአቅሙ ደግፏል:: አንዳንድ ጮሌዎችን የገጠማቸው በለስ ነው:: አንዳንዶቹ ገና በተስፋ አሉ፤ ከዚህ ቀጥሎ ያለው አብይ ጥያቄ ለውጡ እንዴት ይመራ ነው:: ዶ/ር አቢይ አህመድ ለአንድ አመት ጠቅላይ ሚኒስትራችሁ ነኝ ብለውናል:: ያስማማል፤ ጥሩ:: ግን እርሳቸው የሚሰጡንን ጉርሻም ይሁን ሌላ ዝም በሉና ተቀበሉ ቢሉንሳ? አሜን ብሎ መቀበል ከሆነ ኮሚሽናቸውንም አምኖ የተቀበረውን ፍትህ አዳፍነን እንሂድ:: ያለበለዚያ እርሳቸው የሚሉትን ዲሞክራሲ ከወዲሁ ያሳዩንና ኮሚሽኑን ለፍትህ ሲባል ያፍርሱት::

በፍትህ እጦት ሳቢያ በየእሥር ቤቶች እየተሰቃዩ የነበሩ ወገኖቻችንን ለምስክርነት ማቅረብ ከተፈለገ ከአንድ ሚሊዮን በላይ እናቀርባለን:: ለወንድሞቻችን፣ ለእህቶቻችን፣ ከየቤታቸው ተለቅመው ለታሰሩት፣ ከማሳው ለተፈናቀለው ገበሬ፣ አደገኛ የባህር ጉዞ በማድረግ ለተሰደዱ ወገኖቻችን፣ ለራሳችንና ለመጪው ትውልድ የሚጠቅመው ከሁሉም በፊት ሰላም ነው:: ፍትህ ነው:: ስለዚህ ፍትህን ከተቀበረችበት ጉድጓድ በቶሎ ካላወጣናት አገር አይኖርም የሚል እምነት አለኝ:: እኛም ሰዎች ሆነን አንቀጥልም:: በዚህ ኃላፊነትና አስተዋይነት ስሜት ነው የፍትህ ግንዛቤያችንን መገንባት የሚኖርብን:: ቸር ያቆየን!!

# ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

## የኤጀንሲው ስም - አልደያርስ በውጭ ሀገር ስራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ

የኤጀንሲው ፍቃድ ቁጥር - PEA/336/2019

ኤጀንሲው ፍቃድ ያገኘበት ሀገር - ሳውዲ አረቢያ

1. የተገኘው ክፍት የስራ መደብ: **የቤት ውስጥ አያያዝ**
    a. የሚፈለገው ብዛት - 1000
    b. ተፈላጊ ችሎታ
        I. ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
        II. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያላት
        III. እድሜ ከ21-45
        IV. ፆታ- ሴት
    c. መነሻ ደመወዝ - 1000 ሪያል
    d. የቅጥር ቆይታ ጊዜ - 2 ዓመት
    e. ስራው የተገኘበት ቦታ- ሳውዲ አረቢያ : ሪያድ እና ደማም ከተማ
    f. ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች
        I. ስልክ አቅርቦት ይመቻቻል
        II. ደመወዝ በየወሩ ይከፈላል

2. የተገኘው ክፍት የስራ መደብ : **የቤት ውስጥ ሹፌር**
    a. የሚፈለገው ብዛት - 200
    b. ተፈላጊ ችሎታ
        I. ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
        II. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያለው (አለም አቀፍ መንጃ ፍቃድ ያለው)
        III. እድሜ ከ23-40
        IV. ፆታ- ወንድ
    c. መነሻ ደመወዝ - 1500 ሪያል
    d. የቅጥር ቆይታ ጊዜ - 2 ዓመት
    e. ስራው የተገኘበት ሀገር- ሳውዲ አረቢያ፡ ሪያድ እና ደማም ከተማ
    f. ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች
        I. ስልክ አቅርቦት ይመቻቻል
        II. ደመወዝ በየወሩ ይከፈላል

3. የተገኘው ክፍት የስራ መደብ : **የቤት ውስጥ እንክብካቤ (ነርስ )**
    a. የሚፈለገው ብዛት - 200
    b. ተፈላጊ ችሎታ
        I. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያለው
        II. እድሜ ከ21-45
        III. ፆታ- ሴት/ ወንድ
    c. መነሻ ደመወዝ - 1500 ሪያል
    d. የቅጥር ቆይታ ጊዜ - 2 ዓመት
    e. ስራው የተገኘበት ሀገር- ሳውዲ አረቢያ፡ ሪያድ እና ደማም ከተማ
    f. ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች
        I. ስልክ አቅርቦት ይመቻቻል
        II. ደመወዝ በየወሩ ይከፈላል

- **ወቅቱ ያላለፈበት የቀበሌ መታወቂያ ያለው/ያላት**
- **ኤጀንሲው የሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎት ሰራተኛው ምንም አይነት የአገልግሎት ክፍያ የማያስከፍል መሆኑን እንገልፃለን፡፡**
- **አመልካቾች ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ጊዜያት በኤጀንሲው ቢሮ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃችሁን ዋናውንና ፎቶ ኮፒውን በመያዝ በግንባር ቀርበው መመዝገብ ይችላሉ**
    - **አድራሻ :- ጎጃም በረንዳ ልዩ ስሙ አራት መንታ ወይም ፅጌሬዳ ሆስፒታል መግቢያ ወረዳ 02 ከበብ ፊትለፊት የጋሚስ የንግድ ማዕከል 2ኛ ፎቅ ጎራ ይበሉ**

**ስልክ ቁጥር፡ 0909-27-24-27 ወይም 0978-64-71-71**
**ኢሜይል - aldeyars@gmail.com**

# ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ በሳውዲ አረቢያ

## የኤጀንሲው ስም፡- አማር እንድሪስ በውጭ ሀገር ስራና ሰራተና አገናኝ ኤጀንሲ

**የኤጅንሲው የፍቃድ ቁጥር PEA /429/2011__ኤጀንሲው ፍቃድ ያገኘበት ሀገር ሳውዲ አረቢያ**

| የተገኘው ክፍት የስራ መደብ | ፆታ | የሚፈለገው ብዛት | መነሻ ደሞዝ | ተፈላጊ ችሎታ |
|---|---|---|---|---|
| የቤት አያያዝ | ሴት | 900 | 1000 ሳውዲ ሪያል | 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀች፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላት |
| የቤተሰብ ሹፌር | ወንድ | 300 | 1000 ሳውዲ ሪያል | 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀች፣አለም አቀፍ መንጃፍቃድ ያለው |

### በሁሉም የስራ መደቦች ላይ ለሚመዘገቡ ሰራተኞች ማሳሰቢያ

- እድሜ ከ 22- 45
- የቅጥር ቆይታ 2 (ሁለት) **አመት**
- ስራው የተገኘበት ሀገር **ሳውዲ አረቢያ**
- የስልክ አቅርቦት ይመቻቻል
- ደሞዝ በየወሩ ይከፈላል
- አመልካቾች ወቅቱ ያላለፈበት የቀበሌ መታወቂያ ያለው/ያላት መሆን አለባቸው።
- ኤጀንሲው ለሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎት ሰራተኛውን ምንም አይነት የአገልግሎት ክፍያ አያስከፍልም
- አመልካቾች ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ጊዜያት በኤጀንሲው ቢሮ የት/ት ማስረጃና የስራ ልምዳቸውን ዋናውና ፎቶ ኮፒው በመያዝ በግንባር ቀርበው መመዝገብ ይችላሉ።

**አድራሻ፡-** አዲስ አበባ ዓለም ባንክ ትሮፒካል ካፌ ፊት ለፊት ዩናታን ህንፃ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 301
**ስልክ ቁጥር፡-** +251921418941 +2519838111 / 0118343631
Email:- amarzm007@gmail.com

# ግዮን መጽሔት

## በየሳምንቱ ቅዳሜ ከእጅዎ ትደርሳለች።

ቢጨመር ፣ ቢሻሻል የሚሉትን ከወዲሁ ይጠቁሙን!



+251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 122333

**ምርትና አገልግሎትዎን ያስተዋውቁ!**

www.facebook.com/enqu2013
Facebook
Gihon-meg Fekadu

ኢ-ሜይል:
enqu2013@gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com